# ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ

«እስመ ኦሪት በሙሴ ተውህበት ለነ፤ ጸጋሰ ወጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ኮነ ለነ።»
«ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና ጽድቅ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን» ፤ዮሐ.1፥17።

መምህር ተከሥተ ጫኔ
በሚኪ ወግዳል
ታኅሣሥ 2006ዓ.ም
አሜሪካ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
©All Right Reserved 2014

የሽፋን ሥዕል በገሊላ ፈለቀ

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖርዎት ወይም ማሠራጨት ቢፈልጉ በአድራሻችን ያግኙን።
✆ 091 164 29 16 አዲስ አበባ
✉ 41028 አዲስ አበባ
Email- tekeste.chane@yahoo.com
United States of America

ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ

## ማውጫ

ርእስ ገጽ

ምስጋና ........ 5
መቅድም ........ 7
መግቢያ ........ 8
ምዕራፍ አንድ ሕግ ........ 10
1.1 ሕግ ምንድን ነው? ........ 10
1.2 ዓላማ ያለው ሕዝብ ........ 12
1.3 የቃል ኪዳን ቃላት ........ 12
1.4 ኀጢአት በሕግ ይታወቃል ........ 14
1.5 ሕጉ ተፈጻሚ ባይሆን ........ 16
1.6 ሕጉ ለሚከተሉት ሁኔታዎች ያገለግል ነበር ........ 18
1.7 ሕግ ሁሉ እኩል ዋጋ አለው ........ 18
1.8 አንድም ጻድቅ የለም ........ 19
1.9 ፊደል ይገድላል ........ 21
1.10 ሕግ ባያጸድቅም እንኳ አልተሻረም ........ 23
1.11 በአሕዛብና በአይሁድ መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ........ 24
1.12 ቀርበው የነበሩት ........ 26
1.13 ርቀው የነበሩት ........ 27
ምዕራፍ ሁለት ትምህርተ ድኅነት ........ 28
2.1. መዳን (ድኅነት) ማለት ምን ማለት ነው ........ 28
2.2. የዘለዓለም ሕይወት ........ 29
2.3. ሕይወት ተገለጠ ........ 29
2.4. ለምን ተገለጠ? ........ 30
2.5. ስለ ዘላለም ሕይወት የአባቶች ምስክርነት ........ 33
2.6. የእግዚአብሔር ቊጣ ........ 33
2.7. ፍጥረታችን ........ 34
2.8. የኀጢአት አገባብ ........ 34
2.9. ኀጢአት ምንድን ነው? ........ 35
2.10. ኀጢአት እንዴት ገባ? ........ 35
2.11. እግዚአብሔር ተቈጣ ........ 37

........ 37
2.12. የቀጣው ቃል........ 38
2.13. ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ይታያል?........ 38
2.14. የሰው ልብ በእግዚአብሔር ፊት ምን ይመስላል?........ 40
2.15. የሰው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ሲታይ........ 42
2.16. ታዲያ ሰው እንዴት ሊድን ይችላል?........ 43
2.17. ለአብርሃምና ለዘሩ የተነገረው የተስፋ ቃል........ 44
2.18. የተስፋው ቃል ለይስሐቅ ተነገረ........ 46
2.19. የተስፋው ቃል ለያዕቆብ ተነገረ........ 47
2.20. ይህ ዘር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው........ 48
2.21 ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ነው ያዳነን?........ 49
2.22. የእንስሳት መሥዋዕት ኃጢአትን ማስወገድ አለመቻሉ........ 50
2.23. ታዲያ እግዚአብሔር በምን ደስ ሊለው ይችላል?........ 51
2.24. ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በግ ተባለ?........ 52
2.25. ቤዛ ብዙኃን........ 53
2.26. ከቀጣው እንድናለን........
2.27. የእግዚአብሔር ዳኝነት (የእግዚአብሔር ፍርድ) ፍጹም........ 54
ነው።........ 54
2.28. የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም ነው።........ 55
2.29. መዳን በሌላ በማንም የለም........ 57
2.30. በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ቤዛነት በኩል........ 59


## ምዕራፍ ሦስት ጽድቅ


ምዕራፍ ሦስት ጽድቅ........ 59
3.1. ጽድቅ ምንድን ነው?........ 61
3.2. የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ........ 62
3.3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ልጅነቱ ሲታይ........ 64
3.4. ሕግን ሊፈጽም መጣሁ........ 65
3.5. ሕግ በሁለት መንገድ ይፈጸማል........ 66
3.6 የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል........ 67
3.7. ሥራችን ሳይሆን እምነታችን ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረልን........ 68
3.8. በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ........ 70
3.9. ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል........ 72
3.10. እግዚአብሔር ጽድቁን ማሳየት ይፈልጋል........ 72
3.11. በፍቅር የሚሠራ እምነት........ 75
3.12. አራቱ የእግዚአብሔር የፍርድ መንገዶች........ 84
3.13. ማጠቃለያ........




## ምስጋና

ከልጅነቴ ጀምሮ መንገድ እየመራ ላሳደገኝና ከስምንት ዓመቴ ጀምሮ ከእናት ከአባቴ ስለይ፣ አባትም እናትም ሆኖ ለተቀበለኝ፣ የኔን አስቸጋሪ ጠባይ ታግሦ ለተሸከመኝ፣ ብቻዬን ስሆን ላልተለየኝ፣ ሁሉም ሲሸሽ ከእኔ ጋር አንድ ብቻውን ቆሞ ለቀረው እውነተኛ ወዳጄ፣ ተስፋንና ራእይን ለሞላብኝ ለአባቴና ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን አሜን!

ከፊደል ጀምሮ በዜማ፣ በቅኔ፣ በአቋቋምና በዝማሬ መዋስዕት ቤት የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ያስተማሩኝን የገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን መምህራኖቼን፣ በመጽሐፍ ቅዱስና በሥነ ምግባር ትምህርት የረዱኝን የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህራንንና ሌሎች በወንጌል አገልግሎት የተሰማሩ አገልጋይ ወንድሞቼን አመሰግናለሁ፤ እንዲሁም በምክርና በርዳታ ካጠገቤ ያልተለየኝን በኢትዮጵያ የሚገኘውን ሊቀ ትጉኃን ኪዳነ ማርያምን እና ይህን መጽሐፍ በማረም የተሳተፉትን መምህራን ወንድሞች በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻም በሰሜን አሜሪካ በቻርለት ከተማ የሚገኘውን ወንድሜን መላከ ሕይወት መሪጌታ ሠናይ ስንሻውን አመሰግናለሁ።

**መታሰቢያነቱ**

በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የኤቲክስና የፍልስፍና አስተማሪ ለነበሩት ለዶክተር የማነ ገብረ ማርያምና የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት መምህር ለሆኑት ለመምህር ተኸመ ዘሪሁን ይሁንልኝ።

**ስጦታ**

## መቅድም

ይህ መጽሐፍ በሦስት ታላላቅ ምዕራፎች የተከፈለ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ ስለ ሕግ እናጠናለን፤ የሕግን ኃያልነትና በመጨረሻም ሕግ የሚያመጣውን ሞት፣ ኀጢአትን በማለፍ አፈጻጸም፣ ሕግ የሚያመጣውን የሕሊና ወቀሳና ቅጣት እንማራለን። ሕግ በሙሴ እማኝነት ተሰጥቶ ነበር፤ ነገር ግን ሰው ሊፈጽመውና ሊኖርበት ባለመቻሉ፣ ሊያድን አልቻለም፤ ስለዚህ፣ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ሞግዚት ሆኖ ማገልገሉን እንማራለን።

በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የጸጋን ኃይልና ነጻ አውጭነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሕግ ፍርድ ከኀጢአት ሞት በመዳን በመንፈሳዊ ነጻነት በዘለዓለም ሕይወት የምንመላለስበትን የደሙን ዋጋ እንማራለን። ነጻ ስጦታ ሕግን መፈጸም ያልተቻለው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ከፍርድ ነጻ መሆኑን የሚያውጅበት የመስቀሉ ሥራ በዚህ ክፍል ተገልጧል።

በሦስተኛው ምዕራፍ ጽድቅን እናማራለን። በክርስቶስ ጸጋ ከኀጢአትና ከሕግ ነጻ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት ያለ ፍርሀት በፍቅር የምንመላለስበት ሕይወት ነው። ጽድቅ በሰው መንገድ ሳይሆን፣ በራሱ በእግዚአብሔር መንገድ የሚገኝ የእምነት ሥራ ነው፤ የሰው ጽድቅ እንደ መርገም ጨርቅ በመሆኑ፣ ንጹሕ የሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰው አስፈላጊ ሆኗል። ስለዚህ ኀጢአተኞች ሁሉ ከሞት የሚተርፉበት የጽድቅ ተስፋ በሦስተኛው ምዕራፍ በመጠኑ ተገልጧል። እነዚህ ሦስት ቃላት ማለት ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ይገልጡልናል ብዬ ስላመንሁ፣ የዚህ መጽሐፍ ርእስ እንዲሆኑ መርጫለሁ።

በሕግ ሞትን፤ በጸጋ ድነትን፤ በጽድቅ ሕይወትን ለማሳየት ሞክሬአለሁ። በጽሑፉ የተላለፈውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ እንድትረዱልኝና ተጠቃሚ እንድትሆኑ የእምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሆን ጸሎቴ ነው።

ተከሥተ ሜ ኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ወንጌል።





## መግቢያ

እኛ ሰዎች የማንወደው ነገር ግን ሁልጊዜ የምናደርገው ምንድር ነው? ቢባል ኀጢአት ነው፤ ኀጢአት በውስጣችን እየኖረ ደስታችንን ወስዶብን እየረበሸን ይኖራል፤ በዚህ ምክንያት መንፈሳችን እየወቀሠን የምንሠቃይ፣ በጸሎታችን ጊዜ የምንሸማቀቅ፣ ሰይጣን ደግሞ በኀጢአታችን እየከሰሰ ሰላማችንን የነሳን፣ ብዙዎች ነን። ሁላችንም እግዚአብሔርን እንፈልጋለን፤ ነገር ግን እርሱን ለማግኘት የምንሄድበት መንገድ እጅግ አድካሚ በመሆኑ፣ በቶሎ ተስፋ እንቈርጣለን። እግዚአብሔር ግን በእኛ አስተሳሰብ ሳይሆን በራሱ መንገድ ተገልጦ አጠገባችን ቆሟል።

በኀጢአታችን ምክንያት ነፍሳችን ዕረፍትን ስላላገኘች ሁልጊዜ እግዚአብሔርን መፈለጓ በጎ ጎኗ ሲሆን፣ እርሱ የተገለጠበትን መንገድ አለማወቋ ግን፣ ሁልጊዜ ስትጨነቅ እንድትኖር ያደርጋታል። ሰው በሞት ቍጥር «የእኔ እጣ ፈንታ ምን ይሆን?» ፤ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት አቆም ይሆን? እያልን፣ ራሳችንን የምንጠይቅ ብዙዎች ነን። «አድራሻዬ የት ነው? ሲኦል ይሆን ገነት?» እያልን መጨረሻችንን ያላረጋገጥንም አለን፤ እንዲህ ዐይነት ችግር ውስጥ የገባነው ጽድቅን በራሳችን መንገድ ለማግኘት ስለምንፈልግ ነው።

አንዳንዶቻችን ደግሞ እኔ እጅግ ኀጢአተኛ ነኝ፤ እግዚአብሔር እኔን ማየት አይፈልግም፤ በሚል የሰይጣን ድምፅ ተገፋፍተን ተስፋ የቈረጥን፣ ጨርሰን ከቤተ ክርስቲያን የጠፋን፣ ከእግዚአብሔር መሸሽ አማራጭ የሚመስለን ሰዎች ነን።

የኀጢአታችን ሸክም ሲከብደን፣ ከኀጢአታችን ያመለጥን መስሎን፣ ከሰይጣን ክስ ነጻ ለመውጣት «እግዚአብሔር የለም» በሚል ስሜት እረፍት ለማግኘት የምንሞክርም አንጠፋም።

በሃይማኖት አባቶች በማመካኘት ከኀጢአታችን ነጻ የምንሆን የሚመስለን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ላለመስማት ጆሮአችንን የደፈንን፣ ወይም «ትክክለኛውን ሃይማኖት ስለማናውቀው ሃይማኖት አያስፈልገንም» በማለት ራሳችንን የምናታልል አለን።

ከኀጢአታችን ክብደት የተነሣ፣ የሚያዝናኑ እና የሚያስቁ ስብከቶችን እንጂ፣ ስለ ኀጢአት ነውርነት፣ ስለ ዘለዓለማዊ ፍርድ፤ ስለ ንስሓ፣ ተግሣጽን እና ወቀሣን የያዙ ስብከቶችን መስማት የማንፈልግ እጅግ ብዙዎች ነን።

ብዙዎቻችን ደግሞ ትክክለኛውን ነጻ የሚያወጣውን የእግዚአብሔርን ቃል ባለማግኘታችን፣ ከኀጢአታችን ለማምለጥ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆኑ ወይም የተሳሳቱ መንፈሳውያን እንቅስቃሴዎችን የምናደርግ፣ በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎችም የኀጢአት ስርየትን ለማግኘት የምንሞክር፣ ነገር ግን እንቅስቃሴዎቻችን እውነት ስለ ሌለባቸው፣ እርካታ እና ደጋግመን ብናደርጋቸውም እውነተኛ ነጻነት ስለ አላገኘን እስከ አሁን መንፈሳዊ ዕረፍት አይሰጡንም፤ በኀጢአታችን የምንኖር ሆነን ሳለ፣ ድረስ የምንቅበዘበዝ እና እግዚአብሔርን የምናመልክ ሰዎች ነን።

በሌላ በኩል "ኢየሱስ አድኖናል፤ ኀጢአት ብንሠራም መዳናችንን አይከለክለንም፤ ኢየሱስ ነጻ ስላወጣን በኀጢአታችን አንጠየቅም" በሚል የስሕተት ትምህርት ከንስሓ ዕርቀን የኀጢአት ባሪያዎች ሆነናል። «የክርስቶስ ተከታዮች ነን» እያልን ከቅድስና የራቅን፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መዝናኛ ንግግር የምናዳምጥ ምስኪኖች አለን። በመጽሐፍ «የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኀጢአትን ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኀጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ» የሚለውን ቃል የረሳነው ብዙዎች ነን፤ ዕብ.10፥26-27።

ከላይ የዘረዘርናቸውን ነገሮች የመሳሰሉት ምክንያቶች ሁሉ ኀጢአት የፈጠረብን ጭንቀቶች ናቸው። እነዚህ ምክንያቶች የበለጠ ኀጢአተኛ ያደርጉናል እንጂ እውነተኛ የሕሊና ዕረፍት ወይም የነፍስ ዐርነትን ሊሰጡን አይችሉም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛውን የኀጢአት ነጻነት የምንጐናጸፈው በምን እንደ ሆነ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ተናግሯል። እንዲህ ሲል፤ «እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም ዐርነት ያወጣችኋል» ፤ ዮሐ. 8፥31። «ኀጢአትን ስለ ባርነት ግንዛቤ ላልነበራቸው የአብርሃም ልጆች ሲናገር፣ «ኀጢአትን የሚያደርግ የኀጢአት ባሪያ ነው። እንግዲህ ልጁ ዐርነት ቢያወጣችሁ ዐርነት ትወጣላችሁ» አላቸው፤ ቍ. 34-37።

ኢየሱስ ክርስቶስ በርግጥ አሁን በሕይወታችን አስሮ ከያዘን ኀጢአት ነጻ ያወጣናል፤ ለኀጢአታችን ምክንያት በማቅረብ፣ ለአእምሮአችን እየነገርነው ጊዜያዊ ዕረፍት ያገኘን ቢመስለንም፣ ነፍሳችን ግን አሁንም ጩኸቷን አላቋረጠችም። በነጻነት ወደሚያኖረው የወልደ እግዚአብሔር ክብር ለመድረስ እውነቱን ማወቅ የግድ ነውና፣ እነሆ እውነቱ!!!





# ምዕራፍ አንድ
# ሕግ

## 1.1. ሕግ ምንድን ነው?

*«ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበር፥ ጸጋና ጽድቅ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆኗል፤* ዮሐ. 1፥17።

### ሕግ ተቀባዩ ሙሴ

ሙሴ ከሌዊ ዘር የተወለደ፣ እስራኤላዊ ሰው ነው፤ ከዕብራውያን ዘር የሚወለዱ ወንዶች ሁሉ እንዲገደሉ ወይም በባሕር እንዲጣሉ፣ በታወጀበት ዘመን ተወለደ፤ በተወለደ በሦስተኛው ወር ወደ ባሕር ተጣለ፤ እግዚአብሔር ግን የተንኰለኞችን ጥበብ ከንቱ በማድረግ፣ ሙሴን ከጥፋት አዳነው። የፈርዖን ሴት ልጅ ወደ ባሕር ስትወርድ በሳጥን ሆኖ አገኘችው፤ ልጅም ይሆናት ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥት አስገባችው። በፈርዖን ቤት ለሙሴ ሞግዚት ሲፈለግ እናቱ እንደ ሞግዚት ሆና እንድታሳድገው ተጠራች፤ ዘፀ. 2፥1-10።

ይህ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። ሙሴ ወዲያው እንደ ተወለደ ወደ ባሕር አልተጣለም፤ የፈርዖን ልጅ ወደ ባሕር የምትመጣበትን እና ሙሴ የሚጣልበትን ጊዜ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ሦስት ወር በሥውር እንዲቀመጥ አደረገ። ሌላ ሰው አግኝቶ ሊወስደው ይችል ነበር፤ ነገር ግን፣ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዲያድግ፣ ሁሉንም እንዲያስተውል፣ በእስራኤልና በግብጻውያን መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት እንዲመለከት የፈርዖን ልጅ እንድትወስደው ተደረገ።

በሙሴ የአስተዳደግ ታሪክ ውስጥ ሌላም የእግዚአብሔርን ጥበብ እናስተውላለን። ሙሴ በግብጻውያን እጅ አድጎ ቢሆን ኖሮ፣ የግብጻውያንን አማልክት በመለማመድ፤ ከዕብራውያን ተስፋ ሩቅ ሆኖ በቀረ ነበር። እግዚአብሔር ግን እናቱን በምሥጢር እናቱ መሆኗ ሳይታወቅ ሞግዚት ሆና እንድትቀጠር አደረገ፤ ዘፀ.2፥8። እርሷም የእናትነት ፍቅሯን እየሰጠችና ጡቷን እያጠባች አሳደገች፣ ሙሴ የእናቱን ጡት እየጠባ፣ የአብርሃምን፣ የይስሐቅንና የያዕቆብን ተስፋ እየተማረ አደገ፤ በሌላ በኩል የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ ስለሚታወቅ፣ ለንጉሥ ልጅ በሚገባ ክብር በንክብካቤ ኖረ፤ ኑሮው በፈርዖን ቤተ መንግሥት፣ አስተዳደጉ በክብር ይሁን እንጂ፤ ልቡ ከጐስቋላ ወገኖቹ ከዕብራውያን ጋር፣ እምነቱ አንድ አምላክ፣ ተስፋው የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ ተስፋ ነበር። ይህም ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«ሙሴ ከተወለደ በኋላ፣ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት፤ የንጉሡንም ዐዋጅ አልፈሩም። ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና። የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ የግብጽን አገር የተወ በእምነት ነበር፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና»፤ ዕብ. 11፥23-27። ተብሎ ተጽፎለታል።

በቤተ መንግሥት በክብር ያደገ ሰው፣ ወደ ታች ወርዶ መከራ ለመቀበል የሚፈቅድ ምን ዐይነት ሰው ነው? በፈርዖን ዘንድ ያለ እግባብ በግፍ የሚሰበሰብ ብዙ ገንዘብ አለ፤ ሙሴ የዚያ ገንዘብ ባለቤት መሆን ይችላል፤ በዚህ ዐይነት ብልጽግና የሚገኘው ደስታ ግን ጊዜያዊ መሆኑን ተገነዘበ፤ ብዙ ገንዘብ ይዞ የሚጨነቅ፣ መብላት አቅቶት የሚራብ አለ፤ ብዙ ገንዘብ በሰው ፊት ክብርን ይሰጣል እንጂ፣ ጤናንና ሰላምን፣ እንዲሁም ደስታን እንደማይሰጥ ብዙ ሀብታሞች ይመሰክራሉ። ሙሴ የእምነት ሰው ነው። በብልጽግና ስም እየተከበሩ ደስታን ዐጥቶ ከመኖር ይልቅ በክርስቶስ ስም መነቀፍንና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን ምርጫው አደረገ። እንዲህ ዐይነቱ ውሳኔ የእምነት ሰዎች የሚወስኑት ውሳኔ ነው።

ሙሴ በእምነቱ ያየውን ተስፋ ለማግኘት ግብጽን ለቆ ወጣ፤ በማያውቀው አገር የበግ እረኛ ሆኖ ተቀጠረ፤ በሐሰት የብዙ ሕዝብ አለቃ ከመሆን እውነትን ይዞ የበግ እረኛ መሆን ሕሊናን የሚያሳርፍ ነገር ነው። ባለ ተስፋውን ሕዝብ በዚያም ሳለ ተስፋ ያደረገው አምላክ ተገለጠለት፤ እግዚአብሔር ከግብጽ እንዲያወጣ ታላቅ ኃላፊነት ተሰጠው። እርሱ የሚሾመውም በሀብትና በእምነታቸው የተፈተኑትን ያምናቸዋል፤ በጥበብ የከበሩትን ሳይሆን በሕሊናቸው የበለጸጉትን ነው «አሁንም ና፤ ወደ ፈርዖን ሕዝቤን የእሥራኤልን ልጆች ከግብጽ ታወጣ ዘንድ፣ እልክሃለሁ» አለው፤ ዘፀ. 3፥10 ።

ነጻ ለማውጣት፣ አስቀድሞ ነጻ መውጣት ያስፈልጋል፤ ሙሴ ሌሎችን ከባርነቱ ነጻ ለማውጣት አስቀድሞ ከግብጽ ወጣ፤ ከዚያ ከኀጢአትና ከባዕድ ነገሮች ነጻ መውጣት ተማለሰ። እኛም አስቀድመን ነጻ ለማውጣት እንላካለን። እግዚአብሔር ነጻ እለብን ከዚያም አውጭ አያደርግም። እርሱ ተልእኳቸውን በትክክል ያልወጡትን ነጻ





የሚፈጽሙትን አስቀድሞ በልዩ ልዩ መንገድ እየፈተነ ያሳድጋል። ሙሴም ከተፈተኑት አንዱ ነው። በከፍታዎች ማለት በግብጽ ሀብት፣ በሥልጣን፣ ከሰው በሚገኝ ክብር፣ በዝቅታዎች ደግሞ በስደት፣ በውሃ ጥም፣ በበግ ጠባቂነት በብቸኝነት ተፈትኗል። ሙሴ ከእነዚህ ሁሉ ምድራውያን ጣጣዎች ነጻ የወጣ ነበር፤ እንዲህ እንዲሆን ያደረገው፣ በክርስቶስ ያለው እምነት ነው፤ የእግዚአብሔር ሰው ብርቱ የሚሆነው በእምነት ነው፤ ዘፀ. 3፥1-12።

## 1.2. ዐላማ ያለው ሕዝብ

እስራኤል ተብለው የሚታወቁት ሕዝብ በአራት ስሞች ይጠራሉ።
በዘር ዕብራውያን ይባላሉ፤ የኤቦር ልጆች በመሆናቸው። [ዕብራዊ] ዘፍ. 10፥21፤
በመንግሥታቸው ስም አይሁድ ይባላሉ። [ይሁዳ] ዘፍ. 49፥8-11፤
በራእያቸው ወይም በዐላማቸው እስራኤል ይባላሉ፤[እስራኤል] ዘፍ.32፥28፤
በሀገራቸው ስም ደግሞ ጽዮናውያን ይባላሉ፤[ጽዮን]1ሳሙ.5፥7፤መዝ.74፥2፣

እስራኤል ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ነው። የእግዚአብሔርን ህልውና፣ ፍርዱንና አገዛዙን ለመግለጥ የተመረጠ፣ ለዓለም ተልእኮ ያለው ሕዝብ ነው፤ የዓለም ሐዋርያ የሆነው ይህ ሕዝብ «የካህናት መንግሥት» ተብሎ ይጠራል። አንድ መንግሥት በሙሉ ካህን የሆነበት የሰማይን አምላክ መንግሥት የሚወክል ሲሆን፣ ለዓለም ሁሉ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበውን የተሸከመ ዘር ነበር። እግዚአብሔር ለዓለም ያለው ዐላማ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የጽድቅና የዘለዓለም መንግሥት መመሥረትና ዓለምን በእርሱ መጠቅለል ነው፤ ኤፌ.1፥10።

«አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፣ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፤ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤ እናንተም የካህናት መንግሥት፣ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ»፤ ዘፀ. 19፥5-6፤ ዘሌ. 20፥26። ስለዚህ እስራኤል የተባለው ሕዝብ የካህናት መንግሥት፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተቋቋመ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ተቋም ነው።

## 1.3. በሙሴ በኩል የተሰጡ የቃል ኪዳኑ ቃላት

እግዚአብሔር ርስቱ ለሚለው ሕዝብ ከአሕዛብ የሚለይበትን ሕግና ሥርዐት በሙሴ በኩል ሰጠ፤ ለሕዝቡ የተሰጡት ጠቅላላ ሕጎች

ስድስት መቶ ዐሥር ሲሆኑ፣ የቃል ኪዳኑ ቃላት ግን አሥር ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ኪዳን ያደረገው በእነዚህ ዐሥር ቃላት መካከለኛነት ነው። ስለዚህ የብሉይ ኪዳን መሠረት እነዚህ ዐሥር ቃላት ናቸው ዝርዝራቸው በፀአት ም. 20፥1-17 ይገኛል።

«እግዚአብሔርም ሙሴን በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌያለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው።... በጽላቶቹም አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ» ይላል፤ ዘፀ. 34፥27-28።

ሕጎቹ ሲሰጡ በታላቅ ክብር ነው፤ እግዚአብሔር በተራራው ላይ ተገልጦ፣ እነዚህን ቃላት በድምፁ ሲናገር፣ ሕዝቡ ሁሉ ሰምተዋል። በዚያ ቀን ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ የሚነድ እሳት፣ እጅግ የበረታ ቀንደ መለከት፤ የመሬት መናወጥ፣ መብረቅ እና ነጎድጓድ፣ ጢስና ከባድ ደመና ታይቷል፤ ዘፀ. 19፥7-20። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጡ ናቸው።

የቃል ኪዳን ቃሎች እጅግ ጽኑ ከመሆናቸው የተነሣ፣ በድንጋይ ጽላት ተጽፈው በታቦት ውስጥ ተቀመጡ፤ ዘፀ. 32፥15፤ 40፥20። የኀጢአት ስርየት በሚደረግበት ጊዜ ደም የሚፈሰው በእነዚህ የቃል ኪዳን ቃሎች ላይ ነበር። የቃል ኪዳን ቃሎችን የሚከድን የስርየት መክደኛ የሚባል ክዳን በታቦቱ ላይ አለ፤ ደሙ የሚፈሰው በዚያ ላይ ነው፤ ዘሌ. 16፥14። ቃላቱ እስከ ደም ድረስ ዋጋ የሚያስከፍሉ መሆናቸውን እንማራለን። እግዚአብሔር በደመና አምሳል ክብሩን የሚገልጠውም ዐሥሩን ቃላት በከደነው የስርየት መክደኛ ላይ ነበር።

«እኔ በስርየቱ መክደኛ ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁ»፤ ዘሌ. 16፥2። እግዚአብሔር በቃሉ ቃል ኪዳን ያደርጋል፤ ቃሉ ለከንቱ የተነገረ ባለመሆኑ፣ ሁልጊዜ በቃሉ ላይ ትኩረት ያደርጋል። በዚህ ምክንያት ክብሩንና መገኘቱን የሚገልጠው ዐሥሩ ቃሎቹ ባሉበት ታቦት ላይ ነበር፤ ቃሎቹን ካላከበርን «እግዚአብሔርን አከብራለሁ» ብንል ውሸተኞች እንሆናለን። ቃሎቹ የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ ታላቅነት፣ ቅዱስነት፣ ደግነትና ሥልጣን ያመለክታሉ። ከዚህ የተነሣ የእሥራኤልን ልጆች የሕይወት ዋጋ ሲያስከፍሉ ኖረዋል። ሕጎቹ ቅዱሳት ናቸውና፣ ሁሉም የእግዚአብሔርን ቅዱስነት ያመለክታሉ።

ሌሎች ስድስት መቶ ሕጎች የመጡት በነዚህ ዐሥር የቃል ኪዳን ቃላት ላይ ተመሥርተው ነው። ለምሳሌ የአስተዳደር ሕጎች፣ የአመጋገብ ሕጎች፣ የንጽሕና ሕጎች፣ የጋብቻ ሕጎች፣ የሥራ ሕጎች፣ የክህነት ሕጎች፣





የመሥዋዕት አቀራረብ ሕጎች፣ የዐሥራት፣ የመባና የስጦታ ሕጎች... ወዘተ ናቸው። እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ቃሎች ብሎ የሚጠራቸው ግን ዐሥሩን ቃላት ብቻ ነው።

ቃል ኪዳኑ «ብሉይ ኪዳን» በመባል ይታወቃል ይህም በሙሴ ተቀባይነት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገ ውል ነው። ውሉ [ኪዳኑ] በእንስሳት ደም ተመረቀ «ሙሴም ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ»፤ ዘፀ. 24፥8፤ ዕብ. 9፥18።

ሐዋርያው ዮሐንስ «ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበር» በማለት ያስታወሰው ከዚህ በላይ ባጭሩ ያየነውን ታሪክ ነው።

## 1.4. ኀጢአት በሕግ ይታወቃል፤ ሮሜ 3፥20።

ሕግ በሙሴ አማካኝነት ከመሰጠቱ በፊት፣ ሁለት በሰው ላይ የሚኖሩ ነገር ግን በግልጥ ያልታወቁ ነገሮች ነበሩ፤ እነርሱም አንደኛው ኀጢአት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሞት ነው። በአንድ ሰው ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ኀጢአትና በርሱም ምክንያት በሰው ላይ የተላለፈው የሞት ፍርድ ተረስቶ ነበር። በጥቂት የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ [በሕገ ልቡና] እንጂ፣ ኀጢአት በዓለም ላይ መኖሩ አይታወቅም ነበር። ኀጢአት ከአዳም ጀምሮ በሰው ዘር ሁሉ ያለ መርገም ነው፤ ነገር ግን ኀጢአት፣ "ኀጢአት" መሆኑ አይታወቅም ነበር። ምናልባት ባህልና ልማድ ሆኖ ተግባብቶ ሳይታወቅ ይኖር ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል።

«ስለዚህ ምክንያት ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኀጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኀጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኀጢአት አይቈጠርም፤ ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኀጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ»፤ ሮሜ 5፥12-14።

ኀጢአት፤ «ኀጢአት» ቢሆንም ካለመታወቁ የተነሣ፣ ኀጢአት ሆኖ አይቈጠርም ነበር። ሙሴ ሕግን እስኪቀበል ድረስ ኀጢአት ባለመቈጠሩ ሞት ነግሦ ኖረ። ማለት በእያንዳንዱ ኀጢአተኛ ላይ የሞት ፍርድ ነበር፤ ችግሩ ግን፣ አለመታወቁ ነው። አንዳንድ ጊዜ በጅምላ የሚፈጅ ወረርሽኝ በዓለም ላይ በተደጋጋሚ ሲከሠት ይታያል፤ እናም የበሽታው ዐይነትና መድኀኒቱ እስኪገኝ ድረስ ብዙ ሰው ያልቃል።

የአንድን በሽታ መድኀኒት ለማግኘት መጀመሪያ የበሽታውን ዐይነት ማወቅ የግድ ነው።

ሕግም ሥራው ይኸው ነው። ሕግ የዓለምን በሽታ ገለጠው፤ በዓለም ላይ ሰውን የሚፈጅ ኀጢአት የሚባል በሽታ አለ፤ ይህን የሚገልጥልን ሕግ ነው፤ እናም በሽተኛው ሁሉ መድኀኒት አግኝቶ መዳን አለበት። አሁን በሕግ ምክንያት በሽታው ተግኝቷል፤ መድኀኒቱም ተግኝቷል እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕግ በሽታን ያሳውቃል እንጂ መድኀኒት አይሆንምና ክርስቶስን ማግኘት የበሽታው ተጠቂ የሆኑ ሁሉ ግዴታ ነው፤ አለበለዚያ መዳን አይቻልም።

ሕግ በደብረ ሲና ተራራ ላይ ሲሰጥ ኀጢአትና ሞት ተገለጡ፤ ሕግን ከተራራው የሰሙ ሰዎች ኀጢአተኞችና ሞታቸውን የሚጠብቁ ነበሩ። «ኢታምልክ» ተብሎ ከመነገሩ በፊት ባዕድ አምልኮ በዓለም ላይ ነበር፤ ስርቆት፣ ዝሙት፣ ግድያ፣ ምኞት፣ ቤሐሰት መመስከር ነበሩ፤ ነገር ግን ኀጢአት ሞትን የሚያስከትል መሆኑ ተረስቶ ነበር። የኀጢአት መገለጥ ማለት እያንዳንዱ ሰው ሕጉን ሲሰማ በውስጡ ያለውን ኀጢአትና እየፈጸመ ያለውን ርኩሰት ይገነዘባል ማለት ነው።

ኀጢአት በሕግ ሲገለጥ እንዴት እንደ ሆነ ለመረዳት አንድ ምሳሌ እንመልከት፤ አንድ ቤት፣ መስኮት ወይም ቀዳዳ [የተከፈተ ስፍራ] ቢኖረው ፀሐይ በርሱ በኩል በምትዞር ጊዜ ጨረር ወደ ቤት ይገባል፤ በጨረሩ ውስጥ ትኩር ብለን ብንመለከት ጥቃቅን አቧራ መሰል ብናኞችን እንመለከታለን። ጨረሩ ወደ ቤት ከመግባቱ በፊት እነዚህን ብናኞች ማየት አንችልም ነበር። አሁን ግን በጨረሩ ምክንያት ብናኞችን ማየት ቻልን። «ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበር»፤ ይላል፤ ሮሜ 7፥8።

ሕግም እንዲሁ ነው፤ ሕግ ከመምጣቱ ወይም ሕግን ከመስማታችን በፊት ምኞት፣ ዝሙት፣ ስርቆት ወዘተ ኀጢአት መሆኑን አናውቅም ነበር። ኀጢአት መሆኑን ልባችን ቢነግረን እንኳ መንፈሳዊ ሞትን የሚያስከትል መሆኑን አናውቅም ነበር። በዚህ ምክንያት ሞት ነግሦብን ኖረ። አሁን ግን ሕግ በደብረ ሲና ሲሰጥ ኀጢአት እንዳለብንና ሞትም እንደሚገዛን ተገነዘብን። በሕግ ጨረርነት የተበወረውን ኀጢአታችንን ዐወቅነው፤ ታዲያ ጨረሩ አቧራውን እንደማያስወግደው ሁሉ ሕግም ኀጢአትንና ሞትን አያስወግድም። ኀጢአትንና ሞትን የሚያስወግደው ሌላ መሆኑን ይጠቊመናል እንጂ። «ሕግ ወደ ክርስቶስ





የሚያመጣ ሞግዚታችን ነው» የተባለውን ስናነብ ሕግ መድኀኒት ክርስቶስን የሚጠቊመን እንደ ሆነ እንረዳለን። ኀጢአትን የሚያስወግደው እርሱ ነውና።

ስለ ሕግና ስለ ኀጢአት ይበልጥ ለመረዳት ሌላ ምሳሌ እናንሣ፤ ማንኛችንም በጠዋት ተነሥተን ወይም ሰው ወደሚሰበሰብበት ሰርግ፣ ልቅሶና ማኅበር ለመሄድ በምናስብ ጊዜ ሰውነታችንን፣ ጥርሳችንንና ፊታችንን በመስታወት መፈተሽ የግድ ነው። ወደ መስታወቱ በምንቀርብበት ጊዜ መስታወቱ በሰውነታችን ላይ ያለውን እድፍ ያሳየናል እንጂ አያስወግድልንም፤ ማድረግ ያለብን በውሃ መታጠብ ነው፤ እድፋችንን የሚያስወግድልን ውሃው ነው። መስታወቱ ወደ ውሃ ይመራናል።

ሕግም እንዲሁ ነው እንደ መስታወቱ በሐሳባችን፣ በንግግራችን፣ በሥራችን ያደረግነውን ስሕተትና በደል ያሳየናል፤ በእንደዚህ ዐይነት ነውር ሆነን ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር ከመላእክቱና ከቅዱሳኑ ጋር ኅብረት ማድረግ እንደማንችልም በሕሊናችን ያስገነዝበናል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የምንፈልግ ከሆነ ነውራችንን ማስወገድ አለብን፤ ኅብረቱን ካልፈለግነው ግን በዚያው ከነነውራችን መኖር እንችላለን፤ የሚጠብቀን ግን ሞት ነው ሕግ ነውራችንን በግልጥ ያሳየናል እንጂ፣ ነውራችንን አያስወግድልንም። ነውራችንን የሚያስወግደው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ኢየሱስ «የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ነውና፤ ስለዚህ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚመራ መስታወታችን ነው።

## 1.5. ሕጉ ተፈጻሚ ባይሆን

«የሞት መውጊያ ኀጢአት ነው፤ የኀጢአትም ኃይል ሕግ ነው» ሞት በሰው ላይ የሚነግሠው በመጀመሪያ ሰውን በኀጢአት ከወጋ በኋላ ነው፤ የተወጋ ሰው ይሞታል፤ ኀጢአት ብርቱ መውጊያ ነው፣ ኀጢአት ለመውጋት የሚያስችለውን ኃይል የሚያገኘው ግን ከሕግ ነው። ኀጢአትን ኀጢአት የሚያደርገው ሕጉ ነውና። ይህን ሐሳብ የበለጠ ግልጥ ለማድረግ አንድን ምሳሌ እንውሰድ፤ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ የተለመደ አንድ ባህል አለ፤ እርሱም «ጠለፋ» ይባላል። ጠለፋ ለጋብቻ የደረሰችን ሴት ልጅ ያለፈቃዷና እናት አባቷንም ሳያስፈቅዱ በተዘናጋችበት ወቅት አስገድዶ መውሰድና መድፈር፣ ከዚያም ሚስት አድርጎ መኖር ነው። ስለ እርሷ የሚከላከል ሰው ቢያጋጥም እንኳ፣ ከፍተኛ የሆነ ድብደባ ይደርስበታል። ነገሩ በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ

ለወላጆቿ ከማግሊ ተልኮ አርቅ ይፈጸማል። ይህ በኅብረተ ሰቡ ዘንድ እንደ ልማድ የሚታይ ሲሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ግን አጸያፊ ኀጢአት ነው። እንዲህ ዓይነት ልማዶች ዛሬም ዐልፈው ዐልፈው በተሰያዩ አካባቢዎች ይታያሉ። ኅብረተ ሰቡ እንደ ልማድ እንጂ እንደ ኀጢአት ወይም እንደ ወንጀል አይመለከታቸውም።

ዛሬ ግን ሕገ መንግሥቱ እንደነዚህ ያሉ ጎጂ ልማዶችን ወንጀል መሆናቸውን ያጸደቀ ሲሆን ከ15 እስከ 25 ዓመታት ድረስ በእሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል መሆኑንም ዐብሮ ደንግጓል። አሁን እንደ ልማድ ተቈጥሮ የነበረው ኀጢአት በጸደቀው ሕግ ምክንያት ወንጀል ሆነ፤ ይሆን ወንጀል እንደ ልማድ ቈጥረው ዛሬም በሚፈጽሙት ላይ ሞትን አመጣ፤ ሕጉ ለወንጀሉ ኃይልን ሰጠው፤ ስለዚህ ልማድ መሆኑ ይቀርና ከዚህ ቀን ጀምሮ ወንጀል ይሆናል። ሕጉ ለኀጢአት ኃይልን ስለ ሰጠው ኀጢአት ኀጢአተኛውን ማስገደል ይችላል። ሕግ ያልወጣለት ኀጢአት ልማድ ሆኖ ይቀጥላል እንጂ፤ ኀጢአተኛውን ሊያስቀጣ አይችልም፤ ስለዚህ፤ ወንጀለኛውን ለመቅጣት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሊወጣለት ይገባል፤ በዚህ ሁኔታ ነው ኀጢአት ኃይል አግኝቶ ወንጀለኛውን ሊወጋ የሚችለው። «የሞት መውጊያ ኀጢአት ነው የኀጢአት ኃይል ሕግ ነው» የሚለውን ቃል ከዚህ በላይ በቀረበው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

እንዲሁም ሕግ በደብረ ሲና ከተሰጠ ጀምሮ በሰዎች ይዘወተር የነበረው ኀጢአት ኃይልን አገኘ። ለምሳሌ አታመንዝር የሚለው ሕግ የነበረው ኀጢአት ኃይልን አገኘ። ለምሳሌ አታመንዝር የሚለው ሕግ ብቻውን ያለ ሥልጣን አይደለም ሞትንም የሚያስከትል ትእዛዝ ነው እንጂ። «ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ቢያመነዝር፣ አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ» ዘሌ. 20፥9 የሚል አፈጻጸም ያለው ሕግ ነው። ከዚያ በፊት ግን ሰዎች ቢያመነዝሩም አፈጻጸም ያለው ሕግ ነው። ከዚያ በፊት ግን ሰዎች ቢያመነዝሩም «ይገደሉ» የሚል የሕግ አፈጻጸም አልታወጀባቸውም ነበር። ማመንዘር ኀጢአት ቢሆንም «አታመንዝር» የሚለው ሕግ እስኪመጣ ድረስ ግን አመንዝራዎችን ለማስገደል ኃይል አልነበረውም። ኃይል ማለት ሥልጣን ማለት ነው፤ አንድ ሰው ባለሥልጣን ሆኖ እንዲያገለግል ሥልጣን የሚሰጠው ሕግ ነው። ኀጢአትም ሰውን ለማስገደል ሥልጣን የሚያገኘው በሕግ ነው።

ሕጉ በተቀበሉት ሰዎች ተፈጻሚ ባይሆን፤ በሞት ያስቀጣል፤ በጽላቱ ላይ የተጻፉት ሕጎችም አገልግሎታቸው ይኸው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ «ለሕይወት የተሰጠችውን ትእዛዝ እርሷን ለሞት ሆና አገኘኋት» ያለው የሕጉን አገልግሎት ለማሳየት ነው፤ ሮሜ 7፥10።





## 1.6. ሕጉ ለሚከተሉት ሁኔታዎች ያገለግል ነበር

- አንደኛ የእግዚአብሔርን ቅዱስነትና ጻድቅነት በመግለጥ፤
- ሁለተኛ ኀጢአትን በመግለጥ ወይም ስሕተቱንና ትክክለኛውን በማሳየት፤
- ሦስተኛ ለሰው ግብረ ገብንና ሥነ ምግባርን በማስተማር፤
- አራተኛ የንጹሓንን መብት በማስከበርና ኀጢአተኛውን በማስቀጣት፤

ሆኖም ሕግ ካለው ሥልጣንና ክብር የተነሣ፤ የበለጠ ሲያገለግል የኖረው ሞትን ነው፤ በሰው ደካማነት ምክንያት ሕጉ በሚጠይቀው ልክ የታዘዘው አልተገኘም፤ ስለዚህ ሕግ ሰውን ሲያስገድል እንጂ ሲያድን አልታየም፤ ሥልጣኑና ክብሩ በሞት አገልግሎት የታወቀ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ የሕግን ሁኔታ ሲገልጥ «ያ በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ» ይላል፤ 2ቆሮ. 3፥7። ሕግ ሰውን ሲኰንን የኖረበት ምክንያት ሰው ሕግን መፈጸም የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይል ስላልነበረው ነው። በኀጢአት የተበከለው ማንነቱ ወደ ኀጢአት የሚያዘነብል ነው። ሰው የጽድቅ ዝንባሌ ያለውን ዐዲስ ሕይወት በክርስቶስ እስከሚያገኝ ድረስ፤ ሕግን በመፈጸም ከሕግ ነጻ መውጣት አልቻለም። ከሕግ ነጻ የምንወጣው ሕግን በመፈጸም ብቻ ነው፤ ነገር ግን ሕግን በፍጹምነት በመፈጸም በነጻነት የኖረ ማንም የለም። በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን እንጂ፤ ገላ. 5፥1።

## 1.7. ሕግ ሁሉ እኩል ዋጋ አለው

የአታመንዝርና የአትግደል ዋጋቸው እኩል ነው። የተመኘው ካመነዘረው በአሠራር እንጂ በክፍያ አይለያዩም፤ ሁለቱም የሚያገኙት ሞትን ነው። «ምኞት ፀንሳ ኀጢአትን ትወልዳለች ኀጢአትም ከደጎች በኋላ ሞትን ትወልዳለች»፤ ያዕ. 1፥15። አንድኛ ተባለ በድንጋዩ ላይ የተጻፉት ሕጎች ሁሉ ባይፈጸሙ ቢቀሩ ሞትን ይወልዳሉ። ስለዚህ፤ ባለመፈጸሙ ምክንያት የሕግ ውጤት ሞት ስለ ሆነ ሕግ ሁሉ ዋጋው እኩል ሆነ።

«ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል በሁሉም በደለኛ ይሆናል»፤ ያዕ. 2፥10። በሰው አእምሮ ሲታሰብ ትልቅና ትንሽ ስሕተት አለ፤ በእግዚአብሔር ፊት ግን ኀጢአት ሁሉ ቅጣት አለው።

የሰው ሁለንተና በኀጢአት የተበከለ ነው። ይህ ማለት አእምሮው፣ ስሜቱ እና ፈቃዱ ተበክለዋል ማለት ነው። ሰው በሰው ፊት ሲታይ መልካም የሠራ፣ ጻድቅ እንኳን የለሽ ይመስላል። ሰውን ጻድቅ እና

ኀጥእ፣ በጣም የጸደቀ፣ በጣም የተኰነነ፣ እያልን በሁለት ጎራ ልንመድብ እንችላለን፤ ነገር ግን «ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል» 1ሳሙ.16፥7 ተብሎ እንደ ተጻፈ የእኛ አመዳደብ ፍጹም የተሳሳተ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእኛን አመዳደብ በመሰረዝ «አንድም ጻድቅ የለም» በማለት ይደመድማል ሮሜ 3፥11። ሰው በመልካምነቱ «ጻድቅ» ቢባልም «ኀጢአት የሌለበት ነው» ማለት ግን አይደለም። ስለዚህ ነው ጻድቃን ራሳቸው «ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ነው፤ እነሆ በዐመፃ ተፀነስሁ እናቴም በኀጢአት ወለደችኝ» ያሉት፤ ኢሳ. 64፥6፤ መዝ. 51፥5።

ሕግ ኀጢተኛ መሆናችንን ይነግረናል እንጂ ከኀጢአታችን አያድነንም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በሰጠው ሕግ በኩል ሲመለከተን፤ ከሕግ በታች ወይም ከፍርድ በታች እንገኛለን፡፡

«አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ፣ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ፣ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኀጢአት በሕግ ይታወቃልና» ይላል፤ ሮሜ 3፥19-20።

## 1.8. አንድም ጻድቅ የለም፤ ሮሜ 3፥10

ጻድቅ ማለት «በእግዚአብሔር ፊት ሕግን ሁሉ አንድም ሳይቀንስ የፈጸመ፣ እግዚአብሔርን በብቃት ደስ ያሰኘ፣ ነውር የማይገኝበት፣ አንድም ቀን ያልበደለ» ማለት ነው። ይህ በእግዚአብሔር ሕግ ፊት ነው። በሌላ በኩል መልካም የሠሩ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እውነተኛ የቅድስና ኑሮ የኖሩ ቅዱሳን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ይባላሉ፤ ምንም ስሕተት የለባቸውም ማለት ግን አይደለም። ጻድቃን ለምሳሌ የመጥምቁ ዮሐንስ አባትና እናት ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ጻድቃን ነበሩ «ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ» በማለት ሉቃስ የመሰከረላቸው ቢሆን ዝቅ ብሎ ደግሞ ዘካርያስ ከእግዚአብሔር የተነገረውን ባለማመኑ ዲዳ ሆኖ እንዲቆይ እንደ ተፈረደበት ይናገራል። ይህም የዘካርያስ ጽድቅ ፍጹምነት የጐደለው መሆኑን ያመለክታል።

ስለዚህ የእያንዳንዱ ሥጋ ለባሽ ጉዳይ በሕግ ቢመረመር ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት ዝም ይላል፤ ስለ ጽድቅ እግዚአብሔርን የሚከራከርና ይገባኛል ኀጢአተኛ አይደለሁም ብሎ በፊቱ የሚቆም ሰው አይገኝም። አይሁድም ሕግ ቢኖራቸውና እግዚአብሔርን ቢያመልኩም ሕግን





ስላልፈጸሙ በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅ አልቻሉም ። አሕዛብም ሕግ ሳይኖራቸው ቢኖሩም ነገር ግን ሕሊናቸው ከፉና በጎውን ይመሰክርላቸው ነበር፤ ኀጢአትን ሠርተዋልና መጽደቅ አይችሉም፤ ሮሜ 2፥12-15። በዚህ ምክንያት አፍ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘጋል፤ ሮሜ 3፥19። ሕግ ያለውም አልጸደቀበትም ሕግ የሌለውም አልጸደቀም ስለዚህ ሁሉ ተሳስተዋልና ሌላ የጽድቅ መንገድ ያስፈልጋል።

በዮሐንስ ወንጌል ም 8፥3-11 የምናነበው፣ በእግዚአብሔር ፊት ያለ ኀጢአት ንጹሕ ሆኖ መቆም እንደማይቻል ነው፤ በጸጋው ካልሆነ ማንም አይቆምም። «ጻፎችና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደርሱ አመጡ» ይላል ሲጀምር። ጻፎችና ፈሪሳውያን ሕግን የተማሩና የሚያስተምሩ እንዲስተማሩት ሆኖ ያላገኙትን ሰው ደግሞ በድንጋይ የሚወግሩ ናቸው። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ጽድቃቸው በውጭ በሰው ፊት ብቻ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ግን ኀጢአተኞችን ለመውገር የሚያበቃ ጽድቅ ቀርቶ ሕግን እንዲያስተምሩ የሚያስችል ብቃት እንኳ አልነበራቸውም። ነገር ግን በሰው ሥርዐት በትምህርት ቤት የተመረቁ ናቸውና እራሳቸው ሕግን ሳይፈጽሙ ሕግን በሰው ሞት ያስፈጽሙ ነበር። «ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን» አሉ ቍ 5። እነዚህ ሰዎች የሙሴን ትእዛዝ ለመፈጸም ድንጋይ አንሥተዋል፤ ይህም በፊደል ተጽፎ ስላነበቡት እንጂ በሕይወታቸው ስለ ተለማመዱት አይደለም። በዚህ አካሄዳቸው ጌታን በሁለት መንገድ ፈተኑት፤ አንደኛ «አትወገር» ቢል «የሙሴን ሕግ ሻረ» ብለው ለመክሰስ ያመቻቸዋል፤ ሁለተኛ «ትወገር» ቢል «ኀጢአተኞችን ላድን መጣሁ» ያለው ይኸው ኀጢአተኞችን ያስወግራል በማለት ሊከሱት ነው። ጌታ ግን ሕግን እነሱ በተረዱት መንገድ ሳይሆን እርሱ በሚያውቀው መንገድ ነገራቸው «ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» አላቸው። አሁን ጌታ ሕግን አልሻረም «ይውገራት» ነው ያለውና። ነገር ግን የሚወግራት ኀጢአት የሌለበትና ሕግን የፈጸመ እንጂ ሕግን የተማረ ወይም ያነበበ አይደለም። ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ፊት ሕግን ፈጽመው ጻድቃን ቢሆኑ ኖሮ «ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት» የሚል ቃል አይጨመርባቸውም ነበር። ነገር ግን ሕግን የተማሩና ያነበቡ እንጂ ሕግን የፈጸሙ ስላልነበሩ፤ በጌታ ፊት ድንጋያቸውን ጥለው ሸሹ። ጌታ ድንጋይ ያስጥላል፡፡

ይህችን በምንዝር የተያዘችውን ሴት ከውግረት ያዳናት ሁሉም ኀጢአተኛ ሆኖ መገኘቱ ብቻ ነው፤ አንድ ጻድቅ ቢገኝ ኖሮ አትተርፍም

ነበር። ነገር ግን አንድም ጻድቅ አልተገኘም። ጌታ የፈረደብሽ የለምን? ሲላት «አንድ ስንኳ» ነበር ያለችው። «ልዩነት የለምና ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጎድሏቸዋል» የተባለው በዚህ ምክንያት ነው፤ ሮሜ 3፥22።

## 1.9. ፊደል ይገድላል፤ 2ቆሮ. 3፥6።

ፊደል የተባለው ሕግ ነው፤ ሥራውም መግደል ነው፤ ፈሪሳውያን «ሙሴ እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን» ያሉት ሕጉ ግደሉ ብሎ ስለ ሚያዝዝ ነው፤ ሕጉ በዘሌ. 20፥9-10 ላይ «አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ» ብሏል። ሕጉ ቅዱስ ስለ ሆነ የቅድስና ዋጋን ያስከፍላል። ሕግ በሁለት መንገድ ይፈጸማል።

1ኛ <u>በሕይወት በመፈጸም፤</u> አድርግ የተባለውን በማድረግ፣ «አታድርግ» የተባለውን ባለማድረግ ይፈጸማል። ይህን ግን በብቃት ያደረገ ሥጋ ለባሽ አልተገኘም።

2ኛ <u>በሞትና በቅጣት በመፈጸም፤</u> ሕግ በሕይወት ካልተፈጸመ በሞትና በግርፋት በእስራት በመሳሰለው ሁሉ ይፈጸማል። ይህን ሲፈጽሙ የኖሩት ሥጋዊ ሕግ የተሰጣቸው እስራኤል ዘሥጋ ሲሆኑ አሕዛብም በኀጢአታቸው ሲሞቱ ኖረዋል። ሕይወት ያጠፋ ሰው ሕይወቱ እንዲጠፋ፤ ዐይንን የጐዳ ሰው ዐይኑ እንዲጐዳ፤ ጥርስን የጐዳ ሰው ጥርሱ እንዲጐዳ፤ እጅን የጐዳ ሰው እጁ እንዲጐዳ፤ እግርን የጐዳ ሰው እግሩ እንዲጐዳ፤ ያቃጠለ እንዲቃጠል፤ ያቈሰለ እንዲቈስል፤ የገረፈ እንዲገረፍ ሕግ ያዝዛል። የሕግ አገልግሎት ይኸው ነው፤ ዘፀ. 21፥23-25። እንዲህ ዐይነቱ የሕግ አሠራር ጽድቅን ስለማያመጣ ለሰዎች ሕይወትን አልሰጠም። ዛሬም የብሉይ ኪዳን አገልጋዮች በመሞትና በመግደል ላይ ይገኛሉ። ደም በመመለስ፣ ክፉውን በክፉ በመመለስ የሚያገለግሉ ሁሉ በክርስቶስ ያልዳኑት ናቸው። ከዚህ ከሞት አገልግሎት እንዴት ነጻ መሆን ይቻላል?

**መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፤ 2ቆሮ. 3፥6።**

«እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለሐዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል»፤ 2ቆሮ. 3፥6።

ጌታ «ጽድቃችሁ ከጻሐፍትና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» እንዳለ (ማቴ.5፥20)፤ አገልግሎታችን





የሕይወት አገልግሎት መሆን አለበት፤ የፈሪሳውያን አገልግሎት በመግደል ሲሆን እኛ ግን በማዳን እናገለግላለን። እንዲገደሉ የሚያደርጋቸው የነርሱ ጠባይ ሳይሆን፣ የሕጉ ጠባይ ነው። የነርሱ ጠባይማ መሞት የሚገባው ክፉ እንጂ መግደል የሚገባው ንጹሕ አይደለም። መግደል የሚገባው ቅዱሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። «በቀል የእኔ ነው» ያለው ለዚህ ነው፤ ሌላ ሰው ለመበቀል የቅድስና ብቃት ስሌለው ነው።

ሕጉ ይቀጣል እንጂ ሕይወትን አይለውጥም። በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው፤ ብሉይ ኪዳን ይቀጣል፤ ሐዲስ ኪዳን ግን ይለውጣል፤ ማለት ሞት የሚያመጣውን ጠባይ ከመሠረቱ ያስወግደዋል። ብሉይ ኪዳን ትኩረት የሚያደርገው አሠራሩ ወይም ድርጊቱ ላይ ሲሆን፣ ሐዲስ ኪዳን ግን ችግሩን ወይም ድርጊቱን ከመጣው ባሕርይና ጠባይ ላይ ነው። ድርጊቱን በመቅጣትና የድርጊቱን ምንጭ በማስወገድ መካከል ልዩነት አለ። አሁን ነገር ተለውጧል። ሕግ በክርስቶስ መንፈስ በሰው ልብ ላይ ስለ ተጻፈ የዳነ ሰው ጠባይ ሆኗል፤ የችግሩ ምንጭ ተወገዷል። ስለዚህ በክርስቶስ እምነት ዳግም የተወለደ እና ዐዲስ ፍጥረት የሆነ ሰው ሊገድል ቀርቶ ሊጠላ አይችልም። የክርስቶስ መንፈስ ሕይወትን ስለ ሰጠው የመግደል ሳይሆን የማፍቀር፣ የመጥላት ሳይሆን የመውደድ፣ የመርገም ሳይሆን የመመረቅ፣ የማሳደድ ሳይሆን የመጸለይ ጠባይ ሰጥቶታል፤ በዚህ ምክንያት ሕግ በሕይወቱ ይፈጸማል። የሐዲስ ኪዳን አገልጋይ መሆን ማለት እንዲህ ነው።

ጌታ «አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል» አለ ምክንያቱም ሰዎች «አትግደል» ሲባል ሰሙ እንጂ አልፈጸሙትም። «እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቈጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ክፉውን አትቃወሙ ቀኝህን ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን አዙርለት... ጠላታችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ.. ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ» አለ፤ ማቴ. 5፥38-45። ይህ ትምህርት በሕይወታችን ሊፈጸም የሚችለው ከጸጋ በታች ከሕግ በላይ መሆን ስንችል ብቻ ነው፤ ሮሜ 6፥14። በክርስቶስ ከማመናችን የተነሣ ሕግን መፈጸም እንችላለን። ክርስቶስን ካላመንን ግን ሕግ የሞት አገልግሎት እንጂ የሕይወት አገልግሎት መሆን አይችልምና። «ግደል፣ ጥላ ዐይን በዐይን ጥርስ በጥርስ ወዘተ» ከሚለው ሕግ ነጻ ከሆንን አገልግሎታችን የሕይወት ይሆናል። ጽድቃችን ከፈሪሳውያን የሚበልጠው በዚህ የሐዲስ ኪዳን አገልግሎት ስናገለግል ብቻ ነው። እንዲህ ዐይነቱን የአገልግሎት ብቃት የሚሰጠን ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ማለት

በመንፈሳዊ ሕይወት እንጂ በሥጋ ሕይወት የማይሞከር ነው፡፡ «የሐዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን»፤ 2ቆሮ. 3፥6 እንዲል፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ ከፍተኛ ለሆነ ሥነ ምግባር ያበቃናል። ድሮ እንሳደብና እንራገም ነበር፤ ዛሬ ግን እንመርቃለን፤ ድሮ እናሳድድ ነበር፣ ዛሬ ግን እንሰደዳለን፤ ይህ አስደናቂ ብቃት ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አድርጎ ነው ያዳነን። ስለዚህ ይህ ብቃት የእኛ አይደለም። የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ብቃት ነው እንጂ። ምስጋናውና ክብሩ ለእርሱ ብቻ ነው።

## 1.10. ሕግ ባያጸድቅም እንኳ አልተሻረም

«እኔ ሕግና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ፤ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፤ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል»፤ ማቴ. 5፥17-19።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ከሁሉ ካነሡት ትእዛዛት» የሚላቸው ዐሠርቱ ትእዛዛትን ነው፤ እነዚህ ሕጎች እንኳን ሊሻሩ የበለጠ በአማኞች ልብ ተጽፈዋል። «ሕጌን በልቡናቸው እጽፈዋለሁ በልባቸውም አኖረዋለሁ» ብሏል፤ ኤር. 31፥33፣ ዕብ. 8፥10። እነዚህ ሕጎች ሁሉ እስኪፈጸሙ ማለት እግዚአብሔር ሰዎችን በክርስቶስ ወደ እርሱ እስኪሰበስብና ሰማይና ምድር እስኪያልፉ ድረስ ጸንተው ይኖራሉ። ሰውን ኀጢአተኝነቱን እየገለጡ ወደ ክርስቶስ የሚያመጡት ዛሬም ወደ መዳን ላልደረሱ ኀጢአተኞች እንደ ሞግዚት እያገለገሉ ወደ ክርስቶስ የሚያመጡት እነዚህ ሕጎች ናቸው። እነዚህ ሕጎች ቢሻሩ ኖሮ ሰው ኀጢአተኛ ሆኖ ለሞት መቅረቡን አይገነዘብም ነበር። ነገር ግን፣ ሁሉ ገና ስላልተፈጸመ ማለት የሚድነው ስላልዳነ ዛሬም እነዚህ ሕጎች ባላመኑት ላይ ሞትን ያገለግላሉ። በክርስቶስ አምነው ወደ ጽድቅ ባልገቡ ሰዎች ላይ ሕግና የሕግ ሞት ይሠራሉ።

ዛሬም ሕግ፣ ባላመኑትና ከጽድቅ ሥራ ውጭ በሆኑት ላይ ሁሉ ሥልጣን አለው፤ ንስሐ በማይገቡና ኀጢአታቸውን በክርስቶስ ደም ባላነጹት ላይ ሁሉ ሥልጣን አለው። ይህ ማለት ሕጉ ይፈርድባቸዋል፣ እንደ ሕጉ ይሞታሉ ማለት ነው።





«ነገር ግን ሰው እንደሚገባ ቢሠራበት ሕግ መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን፤ ይኸውም፣ ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፣ ለዐመፀኞችና ለኀጢአተኞች፣ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኩሳን፣ አባትንና እናትን ለሚሰድቡ፣ ለነፍሰ ገዳዮችና ለሴሰኞች፣ ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፣ በሰዎች ለሚነግዱ፣ ለውሸተኞችም በውሸትም ለሚምሉ፣ ... ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሠራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሠራ ሲያውቅ ነው»፤ 1ጢሞ. 1፥8-11። «እንግዲህ ሕግን እንሽራለንን? አይደለም እናጸናለን እንጂ» ብሏል፤ ሮሜ 3፥31፡፡

ሕግ «አያጸድቅም» ማለት «ተሽሯል» ማለት አይደለም። ታዲያ ካላጸደቀ ለምን ያገለግላል? ለሚል ጠያቂ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚት ነው ብለን እንመልሳለን፡፡ ሞግዚትነቱ ወደ ክርስቶስ ገና ላልደረሱትና ከሞት ነጻ ላልሆኑት ሁሉ ነው፤ ለዳኑ ክርስቲያኖች ግን መንፈስ ሆኖ ጠባይ ሆኗቸዋል። ሕግ ለኀጢአተኛው ኀጢአቱን በመግለጥ «መዳን አለብህ አለበለዚያ ትሞታለህ» በማለት ይመክራል። የመዳኛ መንገዱ ግን ሞት ነው፤ ከሕግ ነጻ የሚሆነው ዋጋውን ሲቀበል ብቻ ነው፤ ሕግ ዋጋ ሳይከፈለው በነጻ አይለቅም፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣን ኀጢአተኛ ሕግ አይገድልም፤ ምክንያቱም፣ የኢየሱስ ሞት ለኀጢአት ዋጋ ነውና፤ ሕግ ዋጋውን በክርስቶስ ሞት አግኝቷል፤ ስለዚህ በክርስቶስ ካመኑት ላይ ጥያቄ የለውም። ሐዋርያው «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» ብሏል፡፡ በጳውሎስ ላይ የነበረው የሕግ ጥያቄ በክርስቶስ ሞት መልስ ማግኘቱን ለመናገር ነው። ጳውሎስ በክርስቶስ ሞቷል፤ ስለዚህ በርሱ የሚኖረው ክርስቶስ እንጂ ኀጢአት፣ አይደለም። ታዲያ ሕግን ወደ ጳውሎስ ምን አመጣው? ክርስቶስ የሚኖርበት ኀጢአት አይኖርበትምና። «ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሠውሯል» (ቈላ. 3፥2) የሚለው ቃል ሁሉንም ግልጽ ያደርግልናል። ሕይወታችን በክርስቶስ ከተሰወረ የሕግ ፍርድ አያገኘውም። ምክንያቱም በመስቀሉ ላይ ፍርዱን በክርስቶስ ሆኖ ተቀብሏልና በአንድ ጉዳይ ሁለተኛ ቅጣት የለም። ጳውሎስ «በሕግ በኩል ለሕግ ሞቻለሁ» ብሏል፤ ገላ. 2፥19። ይህን ምስጢር ጽድቅ በሚለው ርእሳችን ላይ እናብራራለን።

## 1.11. በአሕዛብና በአይሁድ መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ

ከዐሠርቱ ትእዛዛት ውጭ የሆኑ ሕጎች በክርስቶስ ደም መሻራቸውን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ምክንያቱም፣ ሕዝብና

አሕዛብን ለይተው አንድ እንዳይሆኑ ዕንቅፋት ሆነው ስለ ኖሩ በግዴታ በክርስቶስ አስታራቂነት እንዲፈርሱ ተደርገዋል።

«እርሱ ሰላማችን ነውና፣ ሁለቱን ያዋሐደ በዐዋጅ የተነገሩትንም የትዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን ዐዲስ ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ፣ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው — በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና»፤ ኤፌ. 2፥14-18።

በዐዋጅ የተነገሩት የትእዛዛት ሕጎች ውስጥ ለምሳሌ ያህል:-

<u>የመተዳደሪያ ሕጎች፦</u>

የዳኝነትን፣ የአስተዳደር፣ የፍርድ ቤትን፣ የርስትና የካሣን ጉዳይ ወዘተ የሚመለከቱ ናቸው፤ ዘጸ. 21፥12-ም22፥1-25።

<u>ማኅበራዊ ሕጎች፦</u>

የአመጋገብ፣ ዘሌ. 11፥1-47፣ የንጽሕና፣ ዘሌ. 12፥1-ም 15፤ የጋብቻ፣ ዘሌ. 20፥11-21፤ ዘዐ. 22፥16-17፤ የሥራና የኑሮ ሁኔታ፣ ዘሌ. 25፥1-17 ...ወዘተ የመሳሰሉት ሕጎች ናቸው።

<u>የመሥዋዕት ሕጎች፦</u>

የክህነትና የክህናት፣ የመሥዋዕት፣ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የተደነገጉ ሥነ ሥርዓቶችና መመሪያዎች ሁሉ ናቸው፤ ዘዐ. 28፥1-ም 30፥38።

<u>የበዓላት አከባበር ሕጎች፦</u>

የሰንበት ዘዐ.20፥8-11 የፋሲካ፣ ዘዐ. 12፥21-48፤ ዘሌ. 23፥5፣ የበዓለ መከር፣ ዘዐ. 34፥22፤ ዘዳ. 16፥13፣ በዓለ አስተስርዮ፣ ዘሌ. 16፥1-34፣ የዳስ በዓል፣ ዘሌ. 23፥34፤ አከባበርን የሚመለከቱ ሕጎች ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ «አካለ ጎደሎ፣ ዲቃላ እንዲሁም ሞዓባዊና አሞናዊ ወደ ጉባኤያችሁ አይግባ»፤ ዘዳ.23፥1-4። የሚልና ይህን የመሳሰሉ ሕጎች ነበሩ። ለዚህ ምልክት እንዲሆን በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ዙሪያ፣ ለመጻተኞች እና ለእንግዶች የሚሆን መስገጃ ከቤተ መቅደሱ ፈቀቅ ብሎ ተሠርቶ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳል። ኢሳይያስም በትንቢቱ ጃንደረቦችና መጻተኞች የሚሰግዱበት መጠለያ ዘሩባቤል ባሠራው ቤተ መቅደስ ቅጥር ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚሰጣቸው ይጠቍማል።

«ወደ እግዚአብሔርም የተጠጋ መጻተኛ:- በእውነት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ይለየኛል አይበል፤ ጃንደረባም:- እነሆ፣ እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ አይበል:: እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ





የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ፣ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና:- በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ:: ያገለግሉት ዘንድ፣ የእግዚአብሔርንም ስም ይወድዱ ዘንድ፣ ባሪያዎቹም ይሆኑ ዘንድ፣ ወደ እግዚአብሔር የሚጠጉትንም መጻተኞች፣ እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ፣ ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ፤ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፤ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና...» ይላል፤ ኢሳ.56፥3-8። ይህ ትንቢት ለጊዜው፣ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣ ከእስራኤል ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጡ አሕዛብ እግዚአብሔር ከሕዝቡ እንደማይለያቸው፣ በተቀደሰው የጸሎት ቤት መታሰቢያ እንደሚሰጣቸው የሚያመለክት ሲሆን፣ ፍጻሜው ግን አሕዛብ ሁሉ በክርስቶስ አምነው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባታቸውን የሚያመለክት ነው።

ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ በሆነው የብሉይ ኪዳኑ ቤተ መቅደስ ቅጥር ውስጥ አሕዛብ ወይም መጻተኞች የሚሰግዱበት የተለየ ሰፍራ እንደ ነበር እንገነዘባለን። ሲሰግዱ እንዳይገናኙም በመካከላቸው ግድግዳ ነበር፤ ሕዝብና አሕዛብን የሚለይ ነው፤ ይህ ግድግዳ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የኀጢአት መጋረጃ የሚወክል ነው። ሐዋርያው የጥል ግድግዳ እያለ በምሳሌነት የሚጠቅሰው ለጊዜው በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የሚለየውን ግድግዳ ሲሆን፣ ማሳየት የፈለገው ግን በዐዋጅ የተነገሩትን ትእዛዛት ነው፤ ይህ ግድግዳ እንዲሠራ ያደረጉት ትእዛዛቱ ናቸውና፤ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ይሆኑ ዘንድ እነዚህ ትእዛዛት የግድ መወገድ ነበረባቸው።

## 1.12. <u>ቀርበው የነበሩት፣ ኤፌ. 2፥17::</u>

አይሁድ ከአሕዛብ ተለይተው ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ ይችሉ ነበር፤ ግን ቀረቡ እንጂ አልገቡም። በቤተ መቅደሱ ዙሪያ መስገድ ይችሉ ነበር፤ የእግዚአብሔር ክብር ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግባት ግን አይችሉም። ነገር ግን በክርስቶስ ሥራ ምክንያት ሁለቱም በአንድ መንፈስ ወደ አብ ገቡ። የልዩነት ትእዛዛት በመሻራቸው የጥል ግድግዳው ፈረሰ፤ አይሁድ እና አሕዛብም በክርስቶስ አንድ ሆኑ። የገቡበት በታ አንድ ነው፤ የገቡትም በየራሳቸው ሥራ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ሥራ ነው፤ ስለዚህ በእነርሱ መካከል ልዩነት የለም። በመንፈስ የሆነው የክርስቶስ ሥራ

እንጂ ሕግ አያስገባም። «በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና» እንዲል፤ ኤፌ. 2፥18።

### 1.13. ርቀው የነበሩት፣ ኤፌ. 2፥13፡፡

አሕዛብ ደግሞ፣ በዐዋጅ በተነገሩት ትእዛዛት ምክንያት፣ ከአይሁድ ጋር አይቀላቀሉም። ያመኑ ቢሆኑ እንኳ፣ እንደ መጻተኛ ራቅ ብለው ይሰግዱ ነበር፤ ስማቸውም «መጻተኛ» ነው፤ ይህን የአይሁድና የአሕዛብን መራራቅ ያመጡትን ሕጎች በመሻር፣ ኢየሱስ ሁለቱን አንድ አደረጋቸው፤ «መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለናንተ ሰላምን፣ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን፣ የምስራች ብሎ ሰበከ» ይላል፤ ኤፌ. 2፥17። እርሱ ሰላማችን ነው። በዐዋጅ የታዘዘው ሕግ ጠብንና መራራቅን አመጣ እንጂ፣ ሰላምን አላመጣም፤ ክርስቶስ ግን በመካከል ገብቶ የሁለቱ ሰላም ሆነ። ስለዚህ ክርስቶስ በመካከል ሆኖ የሕግን ቦታ ከያዘ፣ የልዩነት ሕግ ቦታ የለውምና፣ ዘወር ቢል ይሻለዋል።

እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፤ ከአብርሃም ዘር ያልሆኑ ሌላ ወገኖች በእስራኤል አምላክ አምነው ሲመጡ «እንግዳና መጻተኛ» ይባሉ ነበር፤ በሕጉ መሠረት የእግዚአብሔር ርስት ከሆነው ከእስራኤል ጋር አይቀላቀሉምም ነበር።

ጃንደረቦችን፣ ዲቃላዎችን፣ በሽተኞችን የሚያገሉ፤ አሕዛብን ማለት ከኢትዮጵያ፣ ከአውሮፓ፣ ከኤሽያ የመጡትን አማኞች እንግዳና መጻተኛ የሚያደርጉ ሕጎች በክርስቶስ ደም ተሽረዋል፤ ስለዚህ አሕዛብ ከሕዝቡ ጋር ባላገሮች ወራሾች ናቸው፤ የእግዚአብሔርም ቤተ ሰብአ ናቸው፤ ሕጉ ባይሻር ግን ባላገርና ወራሽ መሆን አይቻልም ነበር። «ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም»፤ ኤፌ. 2፥19። ዛሬ በእግዚአብሔር መንግሥት እንግዳና መጻተኛ የለም፤ የሚያለያዩ ሕጎች በኢየሱስ ክርስቶስ ተሽረዋል። ሁሉም በእርሱ መካከለኛነት ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል። ሁሉ በእርሱ ሆኗል፤ የሆነውም ለእርሱ ነው፤ እርሱ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን፡፡ አሜን!





## ምዕራፍ ሁለት
## ትምህርተ ድኅነ

### 2.1. መዳን (ድኅነ) ማለት ምን ማለት ነው?

ከዚህ ቀጥለን ከሕግና ከኀጢአት ነጻ የሆንንበትን የእግዚአብሔርን አሠራር፣ እንዲሁም የዳንንበትን ጸጋ እንማራለን።

**ጸጋ**

**"ጸጋው በእምነት አድኗችኋል"፤ ኤፌ. 2፥8፡፡**

በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም፤ ዮሐ. 3፥36።

**መዳን**

መዳን የሚለውን ቃል በሦስት ትርጕም ልናየው እንችላለን፡፡

1. **<u>መትረፍ</u>** ማለት ነው። ሊሞት ሲጠበቅ የነበረ በሽተኛ ሳይሞት ቢቀር፣ ተረፈ ይባላል፤ «ዳነ» ለማለት ነው፤ በዓለም ላይ ከሚገኝ ኀጢአት ነጻ መሆን፣ ወይም በክፉ ከመያዝ መዳንን ያመለክታል።
2. **<u>ማምለጥ</u>** ማለት ነው፡፡ በጠላት ተከቦ፣ ወይም በእደጋ ውስጥ የነበረ ሰው ከዚህ ሁኔታ ሲወጣ፣ «አመለጠ» ይባላል። ሊገለጥ ካለው የዘላለም ፍርድ ማምለጥን ያመለክታል።
3. **<u>መጽደቅ</u>** ማለት ነው የኀጢአት ስርየትን እና የኀጢአት መወገድን የሚያመለክት ሲሆን የሕይወት ለውጥ ማድረግን፣ ዐዲስ ሕይወት ማግኘትን እና በእግዚአብሔር ፊት ብቁ ሆኖ መታየትን የሚያሳይ ነው።

ስለዚህ፣ «መዳን» የሚለው ቃል፣ መትረፍ፣ ማምለጥ እና መጽደቅ የሚል ትርጕም አለው።

በዚህ መሠረት ከላይ ያየነውን ጥቅስ መነሻ በማድረግ የመዳንን ትምህርት እንማራለን።

በዚህ ቃል ውስጥ 1ኛ. የዘለዓለም ሕይወት አለው [ይድናል]
2ኛ. የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል
[ይፈረድበታል]የሚሉትን እንመለከታለን።

## 2.2. የዘለዓለም ሕይወት

የዘለዓለም ሕይወት ማለት፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንመርምር። ሰማይና በውስጡ ያለው ፍጥረት፣ የሚታየውና የማይታየው ሁሉ እንዲሁም ምድርና በውስጡ ያለው ሁሉ ከመገለጡ በፊት ብቻውን የሚኖር አንድ ሕይወት ነበር፤ ይህ ሕይወት ብቻውን የኖረበት ዘመን ምን ያህል እንደ ሆነ አይታወቅም፤ ነገር ግን፣ «ዘለዓለም» በመባል ይታወቃል። ወደ ኋላ መጀመሪያ የለውም፤ ወደ ፊትም መጨረሻ የለውም፤ ስለዚህ የዘለዓለም ሕይወት ማለት «ሰማይና ምድር ከመገኘቱ በፊት የነበረ፣ ያለና የሚኖር ሕይወት» ማለት ነው፤ ይህ ሕይወት የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው፤ ኤፌ. 4፥18። ሰማይና ምድርን አሁን የምንኖርበትን ሕይወት ወደ መኖር ያመጣ ይህ ሕይወት ነው፤ ነገር ግን ከሰውና ከፍጥረት ሁሉ ተሠውሮ ማንም ሳያየው ይኖር ነበር።

«ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጧል» ይላል፤ ቆላ. 1፥26።

## 2.3. ሕይወት ተገለጠ

ይህ ተሰውሮ የነበረው ሕይወት በሰው ተፈጥሮ ፍጹም ሰው በመሆን ተገለጠ፤ ሕይወት ተገለጠ ማለት ሊታይና ሊዳሰስ በሚያስችል ሁኔታ በሰው መካከል ተገኘ ማለት ነው፤ ይህን እውነት በዮሐንስ መልእክት መረዳት እንችላለን፦

«ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፤ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን»፤ 1ዮሐ. 1፥1-3።

ይህ ሕይወት ከሁሉም በፊት የነበረው የአብ ቃል፣ በኋላም ከድንግል ማርያም ነፍስና ሥጋን ተዋሕዶ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ» ይላል ዮሐ. 1፥1፡14። እርሱ በዘለዓለም ውስጥ የነበረና ዓለምን የፈጠረ፣ እንዲሁም የዘለዓለም ሕይወት ነው፤ ይህ ሕይወት ሲነገርና ሲሰበክ የኖረ ነው፤ ዘመኑ ሲፈጸም ግን፤ ለመታየት፣ ለመዳሰስ በቃ፣ እጅግ አስደናቂ ምሥጢር ነው። እግዚአብሔር ሰው ሊዳስሰው በሚችል ሁኔታ ተገልጧል። ከዘለዓለም





ያሰበውን የርሱን ጸጋም ለሰው በመስጠት፣ ሞትን በመሻር፣ በግልጥ ታይቷል። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህን ሲመሰክር፦

«ያዳነን፣ በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና ፤ ይህም ጸጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፤ አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቷል። እርሱ ሞትን ሽሯልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል» ይላል፤ 2ጢሞ. 1፥9-11።

## 2.4. ለምን ተገለጠ?

የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆኖ ሊገለጥ የወደደበት ምክንያት ለመታየት ወይም ለመዳሰስ ብሎ ሳይሆን፣ የርሱን ሕይወት ሊያካፍለን በመውደዱ ነው። ሐዋርያት እንዲናገሩ የታዘዙት ይህንን ምሥጢር ነው። ሰው የዘላለም ሕይወትን በማግኘት ከሚጠፋው ዓለም እንዲድን ጥሪ አስተላልፈዋል። እግዚአብሔር ሳይገለጥ፣ ሕይወቱን ሊያካፍለን አይችልምን? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ይችላል ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔርን የዘላለም ሕይወት መካፈል የምንችለው፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት ስናደርግ ብቻ ነው። ሰው በኃጢአት የቆሸሸ በመሆኑ በኢየሱስ ሥጋ በኩል ካልሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ አይችልም፤ ስለዚህ፣ ሥጋችንንና ነፍሳችንን በመልበስ አማኑኤል ሆነ፡፡ ትርጉሙ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው። እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስችለንን ሕይወት ሁሉ ሰጥቶናል፤ «የመለኮቱ ኃይል፣ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፣ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን... ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን» የሚለው የጴጥሮስ መልእክት ይህን የሚያረጋግጥ ነው፤ 2ጴጥ. 1፥3-4።

ሐዋርያው ዮሐንስ «የምናወራው የዘላለምን ሕይወት ነው» ብሏል ለምን የዘለዓለምን ሕይወት እንደሚያወራ ሲያስረዳ ደግሞ፦ «እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን፤ ኅብረታችንም ከአባት ጋር፣ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው» ብሏል፤ 1ዮሐ. 1፥3።

በዚህ ቃል መሠረት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወት ያላቸው ሁሉ፣ ከሥላሴ ጋር ኅብረት አላቸው፤ የሥላሴ ኅብረት

የሚገኘው የዘለዓለምን ሕይወት በመካፈል ስለ ሆነ፣ ሰው ይህን ሕይወት እንዲያገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ይህ ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ «እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለ ሆነ፣ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን»፤ ኤፌ. 2፥5።

አሁን የምንኖርበት ተፈጥሯዊ ሕይወት የሰማይና የምድር ሥርዐት ጭምር አንድ ቀን ይጠፋል። የዘላለም ሕይወት ግን፣ የእግዚአብሔር ሕይወት ስለ ሆነ አይጠፋም፤ ይህን ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኙት ሁሉ ከሰማይና ከምድር ጋር ዐብረው አይጠፉም፤ ምክንያቱም ከዘለዓለማዊው ከሥላሴ ጋር ኅብረት አላቸውና ከርሱ ጋር ዐብረው በሕይወት ይኖራሉ።

ሆኖም ወደዚህ ዘለዓለማዊ ኅብረት ለመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ግዴታ ነው። ይህ የእግዚአብሔር የፍቅር ግብዣ ነው፤ ማንም ሰው ግብዣውን ያለመቀበል መብት አለው፤ ነገር ግን የዘላለም ሕይወት አግኝቶ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረው አይችልም።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና»፤ ዮሐ. 3፥16።

እግዚአሐቤር ሰው እንዲጠፋ አይፈልግም፤ በመሆኑም ሕይወቱን በልጁ በኩል በመስቀል ላይ አካፍሏል፤ ይህን ሕይወት መቀበል የእያንዳንዱ ሰው ፈቃድና ውሳኔ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸለየበት ዋና ጉዳይ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ከሥላሴ ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው፣ ለዘለዓለም እንዳይጠፉና ከፋው እንዳይነካቸው ነው። ይህን ከዮሐ. 17፥1-26 እንመልከት፡-

«ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህ የሰጠኸኝን እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው ... ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ»፤ ዮሐ. 17፥11፥20-23። እግዚአብሔር በእኛ በመኖሩ የማይጠፋ ሕይወት





አለን፤ እኛ በእርሱ ሕይወት እንኖራለን። «የዘላለም ሕይወት» የሚለው ቃል «ሁልጊዜ» የሚል ትርጉም ብቻ ያለው ሳይሆን «ቋሚ መኖሪያ» የሚልም ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቈላስይስ 3፥3 ላይ፣ በክርስቶስ ሕይወታችን እንዴት እንደ ተሰወረ ወይም ከጥፋት እንዳመለጠ ሲናገር «ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯልና» ይላል።

«አንተ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ እኔም ባንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ» እንዳለ ጌታ የዘላለም ሕይወት ሥላሴ በእኛ፣ እኛ በሥላሴ መገኘት ማለት ነው፤ ይህም የተከናወነው በክርስቶስ ነው።

የአንድነታችን መሠረት ሥላሴ ሲሆን፣ እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው፤ እኛ በአንድነት ፍጹማን እንድንሆን ተጠርተናል፡፡ ይህም አንድነት የሚከናወነው በክርስቶስ ሥጋ በተሰጠን ክብር ምክንያት ነው፤ እግዚአብሔር ለእኛ ክብርን ባይሰጠን ሥጋችንን ሊዋሐድና ከእኛ ጋር ኅብረት ሊያደርግ አይችልም ነበር።

ዛሬ እኛ በሥላሴ ኅብረት ማለት በቀደሙት አባቶች፣ በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በሰማዕታት፣ በጻድቃን ነፍሳት፣ እንዲሁም በመላእክት ኅብረት ውስጥ እንገኛለን። ይህንንም ከዕብራውያን መልእክት እንመልከት፡-

«ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊትም ኢየሩሳሌም፣ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፣ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹማን ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፣ የዐዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፣ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል»፤ ዕብ. 12፥22-24። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኅብረቶች በእግዚአብሔር ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ለዘላለም የማይፈርሱ ኅብረቶች ናቸው፤ እኛም የእግዚአብሔርን ሕይወት በክርስቶስ በመካፈላችን ወደዚህ ኅብረት ለመድረስ ችለናል።

## 2.5. ስለ ዘላለም ሕይወት የአባቶች ምስክርነት

«ዘዚአነ ሞተ ነሥአ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ» «የኛን ሞት ወስዶ የርሱን ሕይወት ሰጠን» [ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ]

«ወአስተወሐድከ መላእክተ ምስለ ደቂቀ እጓለ እመሕያው፤ ወዐረቀ ማእከሌሆሙ እስመ ብከ ኮነ ዕርቅ ወሰላም» ትርጉም «መላእክትንና የሰው ልጆችን አንድ አደረግህ፤ በመካከላቸውም አስታረቅህ፣ ሰላምና ዕርቅ ባንተ ሆኗልና፡፡»

«ወሙታንሂ ሐይዉ ሶበ አእመሩከ፤ እስመ ሕያው ለበስከ አልባሰ ሞት ወወረድከ ኀበ ሙታን። ወሶበ ነፍሐት ነፋሰ መዐዛ መንፈስከ ላዕሌሆሙ ሐይዉ» ትርጉም «ሙታን ባወቁህ ጊዜ ሕያዋን ሆኑ፤ አንተ ሕያው የሆንህ የሞትን ልብስ ለብሰሃልና። ወደ ሙታንም ወረድህ፤ ነፍስህ የመንፈስህን መዐዛ በሙታን ላይ እፍ ባለችባቸው ጊዜ ሕያዋን ሆኑ» ሰምዖን ዐምዳዊ፡፡ እንግዲህ የዘላለም ሕይወት ማለት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከሥላሴ ያገኘነው ሕይወት ማለት እንደ ሆነ እንገነዘባለን።

## 2.6. የእግዚአብሔር ቍጣ

«የእግዚአብሔር ቍጣ በርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም»፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስና እውነተኛ በመሆኑ እውነትና ቅድስና ያለበት ሥራ ደስ የሚያሰኘውን ያህል ክፉ ነገር፣ ርኩሰትና ሐሰት የሆነ ነገር ደግሞ እጅግ ያስቈጣዋል። እርሱ ምንጊዜም ትክክል ስለ ሆነ፣ የሐሰትን ሥራ ሊወድና በዚያ ደስ ሊለው አይችልም። ባሕርዩ ብቻ አይደለም፤ ጠባዩ ከሐሰት ጋር የሚስማማ አይደለም። ሰው እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመወሰኑ በፊት፣ የእግዚአብሔርን ጠባይ ማወቅ አለበት፤ እግዚአብሔር ምክንያት እየፈለገ ሰውን ለመቅጣት የሚያስብ ሳይሆን ጠባዩ ቅዱስና እውነት ስለ ሆነ ኀጢአትን እጅግ የሚጸየፍ አምላክ ነው። ስለዚህ ከእውነተኛነቱ የተነሣ ይቈጣል።

የሰው ዘር እግዚአብሔር የተቈጣው ዘር ነው። ይህንንም ከመጀመሪያው የሰው ታሪክ ጠባይና አስተሳሰብ ተነሥተን የቍጣውን ምክንያት ለመረዳት እንሞክራለን።

«እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቍጣ ልጆች ነበርን» ይላል፤ ኤፌ. 2፥3።

## 2.7. ፍጥረታችን

ፍጥረታችን የተባለው አዳም ነው፤ የመጀመሪያው ዘር እርሱ ነበርና። ኀጢአት ወደዚህ የመጀመሪያው ዘር በመግባቱ እግዚአብሔር ተቈጣው። በዚህ ምክንያት ከአዳም የተወለደ ሁሉ፣ ተፈጥሮዉን እንደ





ወረሰ ሁሉ ኀጢአቱንና ፍርዱንም ወርሷል። አዳም የደረሰበት መጎዳት፣ የጠባይ መለወጥ፣ በኀጢአት ኃይል ቍጥጥር ሥር መዋል፣ ድካምና ውድቀት የመሳሰሉት ጠባያት ሁሉ ለዘሩ ተላለፈዋል።

«ስለዚህ ምክንያት ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኀጢአትም ሞት፤ እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን ስለ አደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» ይላል፤ ሮሜ 5፥15።

## 2.8. የኀጢአት አገባብ

ኀጢአት ወደ ፍጥረታችን እንዴት እንደ ገባ ከማየታችን በፊት፣ ሰው[ፍጥረታችን] ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት እንመልከት ፤ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃት ዘንድ ይጠብቃትም ዘንድ በኤድን ገነት አኖረው። እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፤ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ»፤ ዘፍ. 2፥15-16።

በዚህ ቃል ውስጥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ቃል ኪዳን እናስተውላለን፤ ሆሴ. 6፥7፡፡

ቃል ኪዳኑ ዘፍ. 2፥28-30 ያለው ነው። አዳም የፍጥረት ገዢ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ደግሞ የአዳም ገዢ ነበር። እግዚአብሔር ይህን ዓለም ፈጥሮ ዝም ብሎ አልተወውም። ኀላፊነት ስለሚሰጠው ገዢና የአገዛዝን ሥርዐት መሥርቷል። በአዳምና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት በዚህ በገዢነትና በተገዢነት መካከል ያለው ቃል ኪዳን ነው።
ዛፉ በሁለቱ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ነው። አዳምና ሄዋን በገነት ውስጥ ሲኖሩ ማንኛውንም ዛፍ መብላት ይችላሉ። አንዱን ዛፍ ሲያዩ ግን የእግዚአብሔርን ክብር፣ ገዢነቱን ያያሉ በዚህ ጊዜ አምልኮ ፤ ምሥጋና፣ ስግደት፣ ያቀርባሉ። ዛፉን ሲበሉ ግን የእግዚአብሔርን ክብር ማቃለላቸው ነበርና እግዚአብሔርን ለማክበር ፈቃደኛ አልነበሩም።

## 2.9. ኀጢአት ምንድን ነው?

ኀጢአት ማለት የሰውን ልብና ሕሊና የሚበክል ሐሳብ ማለት ነው። ከምናየውና ከምንሰማው የተነሣ፣ ሐሳብ ወደ አእምሯችን ይመጣል በዚህ ጊዜ መንፈሳችንን ተቈጣጥሮ በተግባር በሕይወታችን ይገለጣል። ነገር ግን አእምሯችን የመጣውን ሐሳብ ክፉ ወይም መልካም መሆኑን የመመርመር ችሎታ አለው። ክፉ ከሆነ «ከሰይጣን የመጣ ነው፤ መልካም ከሆነ ከእግዚአብሔር ነው» ማለት የሚችል አእምሮ እግዚአብሔር

ሰጥቶናል። ልባችንን ከክፉ መጠበቅ ከቻልን ኀጢአትን ልናደርግ አንችልም፤ እግዚአብሔር ግን የምንናገረው እንኳ እውነት ከሆነ ከእግዚአብሔር፣ ከፉ ከሆነ ከሰይጣን የወጣ እንደሚሆን አስተምሮናል፦ "ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህ የወጣ ግን ከክፉው ነው" ብሏል፤ ማቴ. 5፥37። ስለዚህ ኀጢአት ልባችንን የሚበክል ክፉ ሐሳብ ማለት ነው።

ልባችን በኀጢአት ከተበከለ ኀጢአተኛ ጠባይ ይኖረናል የምናስበውና የምንሠራውም ክፉ ይሆናል፤ መጽሐፍ «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት መውጫ ከርሱ ነውና» ያለው ኀጢአት ልብን ስለሚበክል ነው፤ ምሳ 4፥23። በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር እንለያለን፤ ከእግዚአብሔር ከተለየን ደግሞ የዘለዓለም ሕይወት ስለማይኖረን የሞትን ነን ማለት ነው። ይህ ሁሉ ችግር የመጣው ግን ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ስለ ገባ ነው።

## 2.10. ኀጢአት እንዴት ገባ?

ኀጢአት በመጀመሪያ የገባው ወደ ሄዋን ልብ ነው፤ ይህን የኀጢአት ሐሳብ ወደ ሄዋን አእምሮ ያመጣውም በእባብ ተሰውሮ የመጣው ሰይጣን ነው። ሄዋንም የእባቡን ሐሳብ ለአዳም አካፈለችው፤ በዚህ ጊዜ አዳም የሴቲቱን ሐሳብ ተቀበለ። እግዚአብሔር አዳምን «የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና» በማለት የገሠጸው በሄዋን የኀጢአት ሐሳብ መስማማቱን ለመግለጥ ነው፤ ስለዚህ ኀጢአት ከሔዋን ቀጥሎ የገባው ወደ አዳም ነው፤ ዘፍ. 3፥17 1. ጢሞ. 2፥14።

«እባብም ለሴቲቱ አላት፤ ሞትን አትሞቱም ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ»፤ ዘፍ. 3፥4-5 ። በዚህ ቃል ውስጥ

- «ሐሰት፣
- ጥርጣሬ፣
- ክሕደት[እግዚአብሔርን አለማመን]፣
- ትዕቢት፣
- ምኞት፣» ...ወዘተ የመሳሰሉት የኀጢአት ሐሳቦች ወደ ሔዋን ገቡ። ሔዋን ሐሰትን በማመኗ ዛፉን ስትመለከተው፣ የእግዚአብሔርን ክብር ማየት አልቻለችም። በዚህ ፈንታ ሥሥትና መጐምጀት አእምሮዋን ተቈጣጠራት። ከፍሬውም በላች፤ ለባሏም አበላችው።





በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ሐሳብ ሳይሆን፣ የሰይጣን ሐሳብ አእምሮቻቸውን ስለ ገዛው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ክብር ተወሰደባቸው። ሰው ኀጢአት ሲሠራ የመጀመሪያው ውጤት የእግዚአብሔር ክብር ከሕይወቱ መጕደል ነው። «ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል» ተብሎ ተጽፏል ሮሜ 3፥23። ሰው የእግዚአብሔር ክብር ሲጐድለው ባዶነት ይሰማዋል፤ ባዶነቱም ሰላም ስለማይሰጠው ባዶነቱን ለመሙላት ሲል ሌላ ብዙ ኀጢአት ይሠራል፤ ኀጢአት ዕረፍት አይሰጥም፤ ሌብነት፣ ሥሥት፣ ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ ርካታን ማጣት፣ ዝሙት የመሳሰሉት ችግሮች ሰላምን ከማጣትና እረፍትን ካለማግኘት የሚመጡ ናቸው።

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ክብር ሲጐድላቸው ወዲያው ባዶነት፣ ራቁትነት፣ ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ ተስፋ መቍረጥ ተሰማቸው። ከዚህ መጥፎ ስሜት የተነሣ ዛፎችን በመጢጋት፣ ቅጠሎችን በማገልደም ራሳቸውን ከጭንቀት ለመከላከል ሞከሩ፤ ነገር ግን ችግሩ የውስጥ የልብ መበከልና የእግዚአብሔርን ጸጋ ማጣት ስለ ሆነ ነጻነት አልተሰማቸውም። ቅጠሎች በፀሓይ ስለሚደርቁ አስተማማኝ ኑሮን አይመሠርቱም። እግዚአብሔር ግን ከቅጠል የተሻለ ቊርበት በማልበስ ትንሽ ዕረፍት ሰጣቸው፤ ይህም ቢሆን ድሮ የነበራቸውን ጸጋ ስለማይመልስና ኀጢአትን ስለማያስወግድ በቂ ነጻነትን አይሰጥም። ነጻነትን ማጣት የኀጢአት ውጤት ነው። ቊርበቱ የሥጋን ኀፍረት ይሸፍናል እንጂ፣ የሕሊናን ኀፍረት አይከድንም፤ ቊርበቱ አዳምና ሔዋን እንዳይተፋፈሩ ያደርጋል እንጂ፣ እግዚአብሔርና አዳም እንዳይተፋፈሩ አያደርግም፤ ቊርበቱ የውስጥን ገመና ሊሸፍን ለሚችለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር። እግዚአብሔር ቊርበቱን ቢያለብሳቸውም፣ ቍጣውን ግን አላበረደውም።

## 2.11. እግዚአብሔር ተቈጣ

አዳም ቃል ኪዳኑን በማፍረሱ በእርሱና በዘሩ ላይ እንዲሁም አዳም በሚገዛው ፍጥረት ላይ እግዚአብሔር ተቈጣ። እርሱንም ከገነት አስወጣው፤ እግዚአብሔር አዳምን ከገነት ያስወጣው፣ ስለ ተቈጣ ነው። አዳም ከገነት ከወጣ በኋላ ልጆች ቢወልድም ከአዳም ተለይተው ወደ ገነት መግባት ግን አይችሉም ነበር። ምክንያቱም የቍጣ ልጆች ስለ ነበሩ ነው።

አዳም ልጆቹን የወለዳቸው ከሞተ በኋላ ማለት ከእግዚአብሔር ከተለየ በኋላ ስለ ሆነ ልጆቹም ሞተው የተወለዱ ናቸው፤ «በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ» ይላል፤ ኤፌ. 2፥1። ፍጥረቱን ወርሰው

እንደ ተወለዱ ሁሉ ጠባዩን፣ ኀጢአቱን አእምሮዉን፣ እርግማኑን፣ አስተሳሰቡንም በመውረስ ነው የተወለዱት። ስለዚህ እኛም ከፍጥረታችን የቍጣ ልጆች ነበርን፤ ኤፌ. 2፥3።

## 2.12. የቍጣው ቃል

በሦስቱም ማለት በእባቡ፣ በሴቲቱና በወንዱ ድርጊት ምክንያት የፍርድ ቃል ተነግሯል።

ለምሳሌ፤ «በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናዉን ትቀጠቅጣለህ»

ሰኰናን መቀጥቀጥ የፍርድ ቃል ነው። ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስና በተከታዮቹ ላይ የሚያመጣውን መከራ ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በአዳም ላይ የተላለፈውን የፍርድ ቃል እራሱ በመሸከም መከራ ተቀበሏል፤ ተከታዮቹም ይህ መከራ እንደሚገጥማቸው አስቀድሞ አስተምሯል።

«እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል» የሚለው ቃል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመከራው በኋላ በመስቀሉ ኀይል በሰይጣን ላይ የሚቀዳጀውን ድል የሚያመለክት ነው። በሴቲቱ ዘር በኢየሱስ ክርስቶስና በሰይጣን መካከል ትልቅ ጠላትነት አለ። ጠላትነቱ በክርስቶስ ልጆችና በሰይጣን የግብር ልጆች መካከል ዛሬም የሚቀጥል ነው። በሰይጣን ልጆችና በክርስቶስ ልጆች መካከል ፈጽሞ ዕርቅና ሰላም ሊኖር አይችልም፤ ሆኖም ግን አሸናፊዎቹ መስቀሉን ተሸክመው በኢየሱስ ስም የሚዋጉ ልጆች ብቻ ናቸው። ሰይጣን እራሱ የሚቀጠቀጠው በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል [ሞትና ትንሣኤ] ነው።

«የሴቲቱን ቃል ሰምተሃልና ምድር ካንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን»፤ ዘፍ. 3፥15 ፥17። የሚሉትና ሌሎችም የርግማን ቃላት ምድር የሰላምና የደስታ ስፍራ እንዳትሆን አድርጓታል፤ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ጥፋቶችና ሰው ሠራሽ ውድቀቶች በዚህ ርግማን የመጡ ናቸው። ወደ ፊት በክርስቶስ የዳኑት ሕይወት ምድር ላይ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር እንዲሁም ዐዲስ ሥርዐት ይተካል። ያቺ ዐዲስ ምድርና ዐዲስ ሰማይ ጽድቅና ሰላም ያለባት ከርግማን ነጻ የሆነች የዘላለምን ሕይወት የተካፈሉ የክርስቲያኖች መኖሪያ ናት።

«ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፤ ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን» ይላል፤ 2ጴጥ. 3፥13።





## 2.13. ኀጢአት በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ይታያል?

ኀጢአት በእግዚአብሔር ፊት ሲታይ የእግዚአብሔርን ክብር እና ቅድስና የሚነካ ወንጀል ነው። ኀጢአት የሚባለው ደግሞ ድርጊት ብቻ አይደለም ጠባይ ወይም ዐመል ነው። የልባችን ሁኔታ፣ አስተሳሰባችን፣ ዝንባሌአችን፣ ዐቋማችን በእግዚአብሔር ፊት ይታያል። እግዚአብሔር የሚመለከተው የልብን ሁኔታ ነውና ውስጣችንን ይመረምራል፤ የኀጢአት ዝንባሌ ያለው ልብ ጽድቅን ሊሠራ ስለማይችል ርኵሰት ሁሉ ከዚያ ይወጣል። «ከኀጢአተኞች ኀጢአት ይወጣል» ተብሎ ተጽፏል፤ ነሳሙ. 24፥13።

## 2.14. የሰው ልብ በእግዚአብሔር ፊት ምን ይመስላል?

ሰው የሰይጣንን ሐሳብና ፈቃድ ካደረገ በኋላ ሐሳቡ [ልቡ]ተበላሽቷል፡፡ እግዚአብሔር ሲመለከተውም ይህን ይመስላል፤ «እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ የልቡ ሐሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ»፤ ዘፍ. 6፥5።

- የሰው ክፋት
- የልቡ ሐሳብ ምኞትም
- ሁልጊዜ
- ፈጽሞ
- ክፉ እንደ ሆነ አየ፤ የሚሉትን ቃላት በጸጥታ ስናስተውል ኀጢአት የልብ ሁኔታን፣ የልብን ዐቋምና ሐሳብ የሚያመለክት ነው። ኀጢአት የሚባለው የሰው ክፋት ነው፤ አንድን ሰው የኀጢአት ወይም የጽድቅ ዐቋም ያለው መሆኑ የሚታወቀው ሁልጊዜ ከሚመኘው፣ ከሚያስበውና ከሚያደርገው በማየት ነው። እግዚአብሔር የሚመለከተው ዐቋምን፣ ጠባይንና ዐመልን እንጂ በስሕተት የተደረገን ድርጊት ብቻ አይደለም።

«ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች ምድርም ግፍን ተሞላች። እግዚአብሔርም ምድርን አየ። እነሆም ተበላሸች፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና» ይላል፤ ዘፍ. 6፥11፡፡ በዚህ ቃል ውስጥ ደግሞ

- «በእግዚአብሔር ፊት
- ተበላሸች፤
- ግፍን ተሞላች፤
- ሥጋን የለበሰ ሁሉ

- መንገዱን አበላሽቶ ነበር፣» የሚሉትን ቃላት ስናስተውል ደግሞ ኀጢአት፤ መንገድ ወይም የአኗኗር ሁኔታ፣ የተበላሸ ሥርዐት፣ ግፍ፣ ሥጋዊነት መሆኑን እንገነዘባለን። ብልሽት ሁልጊዜ ለሰው አይታይም፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ ስለ ተበላሸ እንኳንስ የሌላውን የራሱንም ብልሽት ማየት አይችልም፤ እንዲሁ የሌላውን ብልሽት እየተመለከተ ለመፍረድ ቢሞክርም በእግዚአብሔር ፊት ግን ሥጋን የለበሰ ሁሉ የተበላሸ ነው። ስለዚህ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ታይቶ ይዳኛል እንጂ ሰው ሰውን መዳኘት አይችልም።

«የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል? እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፣ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ»፤ ኤር. 17፥9-10። በዚህ ቃል ውስጥ

- «የሰው ልብ
- ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ
- እጅግም ክፉ ነው
- ማንስ ያውቀዋል?
- እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ
- ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ
- ልብን እመረምራለሁ» የሚሉትን ቃላት ስናስተውል ፣ የሰው ልብ በእግዚአብሔር እይታ መሠረት የሚለካ ነው፤ ከሰው እይታ ውጭ የሆነ የጠለቀ ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር ዐይን ግን የማይሰወር ነው።

«እኛን በሚቈጣጠር በእርሱ ዐይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው እንጂ፣ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ይላል፤ ዕብ. 4፥13። ልብ በእግዚአብሔር እይታ እጅግ ተንኰለኛ፣ ፈጽሞ ክፉ መሆኑ የታወቀ ነው፤ በውስጡም ሰውን በሚያረክስ ነገር የተሞላ ነው። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልብ ውስጥ ያሉትን ነገሮች እንዲህ ዘርዝሯቸዋል።

«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሐሳብ፤ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርና፣ መጐምጀት፣ ክፋት፣ ተንኰል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው። ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል»፤ ማር. 7፥20-23። እነዚህ ነገሮች ከውስጥ ሲወጡ ቤተ ሰብን፣ አካባቢን፣ መንደርን፣ ሀገርን ይበክላሉ፤ ማለሰብን፣ ባለሥልጣንን፣ ሽማግሌንም ያረክሳሉ።





በዚህ የኀጢአተኛነት ጠባይ ምክንያት የእግዚአብሔር ቍጣ በዐመፀኛው የሰው ዘር ላይ ተገልጧል፤ ዘፍ 7፥1-14፤ ዛሬም በኢየሱስ ክርስቶስ ባላመኑና ከኀጢአታቸው ነጻ ባልወጡ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ያለባቸው መሆኑ የታወቀ ነው።

«በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም» ተብሎ ተጽፏል፤ ዮሐ. 3፥36። ይህ ቍጣ ከጥንት ጀምሮ በሰው ዘር ላይ የነበረና ዛሬም ባላመኑት ላይ ያለ ሲሆን ክርስቶስ ዳግም ሲገለጥ ወደ ፊት ይታያል።

«እውነትን በዐመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኀጢአተኝነታቸውና በዐመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና»፤ ሮሜ 1፥18፤ የሐዋ. 10፥42-43። ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔር ቍጣ በርሱ ላይ ከመገለጡ በፊት ዛሬውኑ ንስሓ ገብቶ የኀጢአት ስርየትን ማግኘት አለበት።

## 2.15. <u>የሰው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ሲታይ</u>

ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት ወይም እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ትክክል የሆነ ኑሮ ማለት ሲሆን፣ ጻድቅ ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ሕግ ፊት ምንም ነውር የሌለበት ሰው፣ አድርግ የተባለውንም ጠንቅቆ የፈጸመ ማለት ነው።

ኀጢአት የሕይወት ዐቋም እንደ ሆነ ሁሉ ጽድቅም እንዲሁ የሕይወት ዐቋም ነው። ጽድቅም በእግዚአብሔር ዐይን ብቻ የሚመዘን፣ ከሰው እይታና አመለካከት ውጭ የሆነ የሕይወት ምስጢር ነው።

ሰዎች ምንም እንኳ ትክክለኛውን ሥራ ቢሠሩም፣ ልባቸው ክፉ በመሆኑ ጽድቃቸው እንደ መርገም ጨርቅ ይቈጠራል፤ ኢሳ. 64፥6። ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር ፊት ነውር የሌለበት ጻድቅ አልተገኘም፤ ይህ ማለት ፍጹም የሆነ በእግዚአብሔር የጽድቅ መስፈርት ልክ የሚመዘንና እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ሰው የለም ማለት ነው እንጂ፣ መልካም የሠራ ሰው የለም ማለት ግን አይደለም። የሚከተሉትን ጥቅሶች እናስተውል፦

«ጻድቅ የለም፤ አንድስ እንኳ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፤ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፤ አንድ ስንኳ የለም»፤ ሮሜ 3፥ 11-12።
አንድ ስንኳ የለም፣

- ሁሉ ተሳስተዋል፤ የሚሉት ቃላት የሰው ሁለንተና በኀጢአት የተበከለ ከመሆኑ የተነሣ፣ ወደ ጽድቅ ያዘነበለ አለመሆኑን፣ መልካም ቢያደርግም እግዚአብሔርን በሚያረካ መልኩ ሊያደርግ አለመቻሉን የሚያመለክቱ ናቸው።

«ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው? እነሆ፤ በቅዱሳኑስ እንኳ አይታመንም፤ ሰማያትም በፊቱ ንጹሓን አይደሉም፤ ይልቁንስ አስጸያፊና የረከሰ፣ ኀጢአትንም እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ»፤ ኢዮ. 15፥14-16።

ሰው [ከሴት የተወለደ] በሥራው ጻድቅ ይሆን ዘንድ አይችልም፤ ምክንያቱም ሥራው ትክክል ቢሆንም እንኳ፣ ያለ ቅድስና የተደረገ በመሆኑ ዋናውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ቅድስናን ማእከል ያላደረገ ነው። «እግዚአብሔር ዐቋማዊ ጠባያችንን እንጂ አደራረጋችንን አይመለከትም» ብለናል።

«ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው»? እንደ ተባለ ምንም ነገር ለእግዚአብሔር ከመሥራታችን በፊት፣ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆነን መገኘት አለብን። በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዐት ዘመን አንድ መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ከመቃጠሉ በፊት ንጽሕናው መመርመር እንዳለበት ሙሴ ታዝዟል፤ ዘሌ. 1፥3። ይህም ምንም ያህል ታላላቅ ወይፈንና በግ ቢቃጠል ንጹሕ ካልሆነ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር የቅድስናን ዐቋም የሚመለከት አምላክ እንጂ ብዙ ማድረግንና ሥርዐት ማሳመርን አይመለከትም። በዚህ የእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ መሠረት ሰው ብዙ ቅድስና የጐደለው ነው። እግዚአብሔር ብዙ ቅዱሳን ቢኖሩትም፣ በእነርሱም የማይታመን መሆኑን ተናግሯል። «በቅዱሳኑስ እንኳ አይታመንም» እንደ ተባለ።

«ልዩነት የለምና ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል»፤ ሮሜ 3፥23።

በእግዚአብሔር የጽድቅ ሚዛን መሠረት፣ በሕዝብና በአሕዛብ በጠቅላላው በሰው ዘር ውስጥ ልዩነት የለም። ልዩነቱ የሚታየው በሰው የጽድቅ መስፈርት ነው። በሰው እይታ አንዱ ሰው ከሌላው የተሻለ መሆኑ ግልጥ ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ምንም ልዩነት ሳይኖር፣ ሁሉም ክብር የጐደለው ነው። ሰው «ጽድቅንና ኀጢአትን» በማመዛዘን ይበይናል። እግዚአብሔር ግን «ጽድቅን» ብቻ ይመዝናል እንጂ ኀጢአትና ጽድቅን በጋራ አይመዝንም፤ ይህን አባባል ግልጽ ለማድረግ «ኀጢአት





የሠራ መልካም በመሥራት ማካካስ አለበት» አይልም። ኀጢአት «ኀጢአት» ስለ ሆነ መቀጣት አለበት፤ ኀጢአተኛው መሞት አለበት፤ የኀጢአት ደመወዝ ሞት እንጂ መልካም መሥራት አይደለም። ጽድቅን ሲሠራ የኖረ ሰው አንድ ቀን ኀጢአት ቢሠራ በቀደመው ጽድቁ ከሞት ሊያመልጥ አይችልም። ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአት በኀጢአትነቱ ብቻ ስለሚታይ ነው። ጽድቅም በጽድቅነቱ ብቻ ይታያል እንጂ ከኀጢአት ጋር አይመዘንም።

«ጻድቁ ግን ከጽድቁ ቢመለስ፣ ኀጢአትንም ቢሠራ፣ ኀጢአተኛውም እንደሚያደርገው ርኵሰትን ሁሉ ቢያደርግ በሕይወት ይኖራልን? የሠራት ጽድቅ ሁሉ አትታሰብለትም ባደረገው ዐመፅና በሠራት ኀጢአት በዚያች ይሞታል» ይላል፤ ሕዝ. 18፥24።

ጻድቃን ኀጢአት እንዲሠሩ አልተፈቀደላቸውም፤ እግዚአብሔር ንጹሕ ዳኛ ስለ ሆነ፣ የጻድቃንን ወንጀል ሳይቀጣ ሊያልፍ አይችልም፤ «እነርሱ ጻድቃን ስለ ሆኑ ኀጢአት ቢሠሩም ምንም አይደለም» የሚል አምላክ አይደለም።

በዚህ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ ምክንያት ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ስለ ሆነ በራሱ ሊጸድቅ የማይችል ክብር የጐደለው ሆኖ ተገኝቷል።

## 2.16. ታዲያ ሰው እንዴት ሊድን ይችላል?

ሰው ሊድን የሚችለው ነውር ባልተገኘበት፣ ፍጹምና ጻድቅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስና በማዳን ሥራው ብቻ ነው። «በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና»፤ ኤፌ. 2፥18።
ስለሴቲቱ ዘር ለማጥናት ለአብርሃምና ለዘሩ የተነገረውን የተስፋ ቃል ከዚህ ቀጥለን እንመርምር፡-

## 2.17. ለአብርሃምና ለዘሩ የተነገረው የተስፋ ቃል

ከሴት የሚወለደውና እባቡን የሚቀጠቅጠው ዘር በአብርሃም በኩል እንደሚመጣ፣ አስቀድሞ የምሥራች ሆኖ ተነግሮ ነበር፡፡ የምሥራቹ ቃል «የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ»፤ (ዘፍ. 12፥3፤22፥18) የሚለው ቃል ሲሆን ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ «ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ» በማለት ያስታውሳል፤ ገላ. 3፥15-20።

ይህ የተስፋ ቃል የሰዎችን ቅድመ ሁኔታ ሳይጠይቅ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሰጠ ኪዳን ሲሆን፣ ነጻ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው። አሕዛብ በእምነት በረከትን የሚያገኙበት ቅድመ ሁኔታ የሌለው ቃል ኪዳን ነው።

ሙሴ በተራራው ላይ እግዚአብሔርን «ስምህ ማን ነው»? ሲል በጠየቀው ጊዜ «የአባቶቻችሁ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብም አምላክ እግዚአብሔር ወደ እናንተ ላከኝ፤ ይህ ለዘለዓለሙ ስሜ ነው እስከ ልጅ ልጅም ድረስ መታሰቢያዬ ይህ ነው» አለው፤ ዘፀ. 3፥15። መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ «የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ» ተብሎ ይጠራል፤ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ከሦስቱ አባቶች በፊት ሌሎች እግዚአብሔርን ያመለኩ ሰዎች እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ነገር ግን ስሙ በእነርሱ አልተጠራም። ለምሳሌ አቤል፣ ኖኅ፣ ሄኖክ የታወቁ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው፤ የእግዚአብሔር ስም ግን በነርሱ አልተጠራም «ለምን?» የሚለውን ስንመረምር፣ እግዚአብሔር ስሙ የተጠራው በሚያመልኩት ሰዎች ሳይሆን የተስፋውን ቃል በተቀበሉ ሰዎች መሆኑን እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር ስሙ የተጠራው በዓለም ሊያደርግ ያሰበውን አጀንዳ በተሸከሙ ሰዎች ነው፤ ይህንንም እንደሚከተለው እንመልከት፦ ለአብርሃም የተነገረው የተስፋ ቃል፦

«ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ አባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን፣ የሚባርኩህንም አባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ»፤ ዘፍ. 12፥ 2-3።

«በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፣ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፣ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፣ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፣ ቃሌን ሰምተሃልና»፤ ዘፍ.22፥17-18

አብርሃም የተጠራው በእግዚአብሔር ከተባረከ በኋላ ለበረከት እንዲሆን ነው፤ ዘሩ የማይቈጠር ነው፤ ዘሩ ጠላቶቹን የሚያሸንፍ ባለ ድል ነው፤ ዘሩ የምድር አሕዛብን ሁሉ የሚባርክ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ሊሠራው ባቀደውና በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት «የአብርሃም አምላክ» ተብሎ ይጠራል፤ የተስፋው ቃል የበረከት ነው ግን ይህ ኪዳን ከአብርሃም ለተወለዱ ሁሉ የተሰጠ ሳይሆን፣ ለአንዱ ዘር ብቻ ለክርስቶስ ነው።





«ለአብርሃም እና ለዘሩ የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፦ ለዘሮቹ አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን ለዘርህም ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ» ነው ይላል፤ ገላ. 3፥16።

## 2.18. የተስፋው ቃል ለይስሐቅ ተነገረ

አብርሃም ከይስሐቅ በፊት እስማኤልን ከባሪያይቱ መውለዱ የታወቀ ነው፤ ሌሎችን ስድስት ልጆችንም ኬጡራ ከምትባለው ሚስቱ ወልዷል፤ ዘፍ. 25፥1-6። የአሕዛብ እናት እንደምትሆን የተነገረላት ሣራ በመሆኗ ኬጡራ እና አጋር በኪዳኑ ውስጥ አልገቡም።

«እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፤ የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፣ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ። እባርካታለሁ፣ ደግሞም ከእርስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ፣ እባርካትማለሁ፣ የአሕዛብም እናት ትሆናለች፣ የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ»፤ ዘፍ. 17፥ 15-16።

አብርሃም ስለ ሣራ ሲነገረው ሣቀ፤ የሣቀበት ምክንያት ሣራ የዘጠና ዓመት፣ እርሱ የመቶ ዓመት ዕድሜ ሽማግሌና ባልቴት በመሆናቸው ነው፤ ስለዚህ «እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር» በማለት ቃል ኪዳኑን ከእስማኤል ጋር እንዲያደርግለት ለመነ፤ ዘፍ. 17፥18። እግዚአብሔር ግን ወደ ፊት በእምነት ከሞት ተነሥተው በሕይወት የሚኖሩትን ብዙ አሕዛብ ስለ ተመለከተ ከሞተው የአብርሃምና የሣራ ሰውነት ከሚመጣው ከይስሐቅ ጋር ቃል ኪዳኑን ማድረግ ፈለገ፤ አብርሃምም ምንም ሰውነቱ እንደ ምዉት ቢሆንም እግዚአብሔር ከሞተ ነገር ሕይወትን ሊያመጣ እንደሚችል አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት፤ ዘፍ 15፥6።

ይህ ምስጢር በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ብዙ አሕዛብን ወደ ሕይወት እንደሚያመጣ፣ በእምነት ጽድቅ እንደሚገኝ የሚገልጥ ነው። እስማኤል በሥጋ ፈቃድ የተወለደ ሲሆን፣ ይስሐቅ ግን በእምነት የተወለደ ነው፤ አሕዛብ በእምነት ከእግዚአብሔር ዳግም እንደሚወለዱ የሚያመለክት ነው።

አብርሃም ስለ እስማኤል እንደ ለመነው አልሆነለትም፤ እስማኤልን በሥጋዊ በረከት እንደሚባርከው፣ ታላቅ ሕዝብም እንደሚሆን ሲነግረው፣ ቃል ኪዳኑን ግን በእምነት ከሚወለደው ከይስሐቅ ጋር እንደሚያደርግ ነገረው፤

«ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ እነሆ ባርኬዋለሁ፤ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ፣ ዐሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፤

ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ። ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ»፤ ዘፍ. 17፥20።

ለምን? ይህ ሆነ ብለን ብናስተውል፣ እስማኤል እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ በስምንተኛው ቀን የተገረዘ፣ የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ነው፤ ነገር ግን፣ እንደ ሥጋ ፈቃድ በመወለዱ፣ ወደ ፊት በእምነት ለሚወለዱት አሕዛብ አባት መሆን አይችልም፤ ስለዚህ የተስፋው ቃል አልተነገረውምና እግዚአብሔር «የእስማኤል አምላክ» ተብሎ ስሙ አልተጠራም። ይስሐቅ ግን ከሞተው የአብርሃም ሰውነትና የሣራ ማሕፀን በእምነት በመወለዱ ወደ ፊት በእምነት ለሚወለዱት ሁሉ አባት መሆን ይችላል።

«ስለዚህ ከሕግ ብቻ ሳይሆን፣ ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተስፋው ቃል እንዲጸና እንደ ጸጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው፤ እርሱም፡- «ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ» ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ፣ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ፣ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው። ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው፤ እንደ ተባለ፣ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ። የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሣራ ማሕፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፣ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፣ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም» ይላል፤ ሮሜ 4፥17-21።

እንዲሁም ይስሐቅ ካደገ በኋላ ለአብርሃም የተነገረው የተስፋ ቃል ተነገረው፤ ዓለም የሚድንበት ዘር በርሱ በኩል እንደሚመጣ ለአብርሃም የማለውን ለእርሱም አጸናለት፤ ስለዚህ እግዚአብሔር «የይስሐቅ አምላክ» ተብሎ ተጠራ።

«በዚች ምድር ተቀመጥ፤ ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፤ አባርክሃለሁም፤ እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁና፣ ለአባትህ ለአብርሃም የማልሁለትንም መሐላ አጸናለሁ፤ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፤ እነዚህንም ምድሮች ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ» ይላል፤ ዘፍ. 26፥3-5።





## 2.19. የተስፋው ቃል ለያዕቆብ ተነገረ

ይስሐቅ ሁለት ልጆችን ከርብቃ ወለደ፤ ስማቸውም ዔሳውና ያዕቆብ ነው። ዔሳው የመጀመሪያ ልጅ ነው፤ እንደ ሰው አስተሳሰብ ኪዳኑን መውረስ ያለበት ዔሳው ነው፤ እግዚአብሔር ግን «ዔሳውን ጠላሁ፤ ያዕቆብን ወደድሁ»፤ ሚል. 1፥2 አለ።

«ጠላሁ» የሚለው ቃል የተስፋው ቃል ለዔሳው አለመሰጠቱን የሚያመለክት እንጂ፣ ጨርሶ መጣሉን የሚያመለክት አይደለም፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ከበረከት ይልቅ ለጊዜው ሆዱን መሙላት የሚፈልግ ሰው በመሆኑ ነው፤ ዘፍ. 25፥29-34። በሌላ በኩል እግዚአብሔር በሰው አእምሮ ሳይሆን፣ በራሱ ፈቃድና ምርጫ የሚሠራ ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ያዕቆብ ተንኮለኛ ነበረ፡፡ የስሙ ትርጓሜም «አሰናካይ» ማለት ነው። ነገር ግን በረከትን አጥብቆ የሚፈልግ ሰው ነበር፤ ሆኖም የእግዚአብሔር ምርጫ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ለአብርሃምና ለይስሐቅ የተነገረው የተስፋ ቃል ለእርሱ ተነገረ።

«ያዕቆብም ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ፤ ወደ አንድ ስፍራም ደረሰ፤ ፀሐይም ጠልቃ ነበርና ከዚያ ዐደረ፤ በዚያም ስፍራ ድንጋይ አነሣ፤ ከራሱም በታች ተንተርሶ በዚያ ስፍራ ተኛ፡፡ ሕልምም ዐለመ፤ እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ፣ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ፣ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፤ እነሆም፣ እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር፤ እንዲህም አለ፤ የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ፤ ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ ይሆናል፤ እስከ ምዕራብና እስከ ምሥራቅ፤ እስከ ሰሜንና እስከ ደቡብ ትስፋፋለህ፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ በዘርህም ይባረካሉ»፤ ዘፍ. 28፥12-14።

እግዚአብሔር በተስፋው ቃል መሠረት «የያዕቆብ አምላክ ተብሎ ተጠራ፤» የዔሳው አምላክ ግን አልተባለም፤ ምክንያቱም ዔሳው ክርስቶስ የሚመጣበት ዘር ባለመሆኑ ነው እንጂ፣ እግዚአብሔርን ሳያመልክ ቀርቶ አይደለም።

ይህ የተስፋ ቃል ለሦስቱ አባቶች ማለት ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ ከተነገረ በኋላ፣ ለማንም አልተነገረም፤ በመጨረሻ ግን፣ ለዳዊት ተነግሯል። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር «የአብርሃም፣ የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ» ይባላል፤ ነገር ግን ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ

ዘሮች ይህን ተስፋ በመያዝና በመማር ለልጆቻቸውም በመንገር ኖሩ፤ በግብጽ በባርነት ሲኖሩም፣ ይህን የተስፋ ቃል አልረሱትም ነበር። ለምሳሌ ሙሴ ከወገኖቹ ጋር ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበልን መርጦ፤ በእምነት ፈርዖንን «እምቢ» ያለበት ምክንያት ይህን የተስፋ ቃል በማመኑ ነው፤ ዕብ. 11፥23-27።

## 2.20. ይህ ዘር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

በዘመኑ ፍጻሜ ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ ዘርዐ ብእሲ የተወለደው፣ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብርሃም የተነገረለት ዘር ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-
«በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም»፤ ዕብ. 2፥15-16።
«ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ፡፡ ስለ ብዙዎች እንደሚነገር:- ለዘሮቹ አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን:- ለዘርህም ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ » ነው፤ ገላ. 3፥16።

ስለዚህ ለአብርሃም የተነገረው ማለት «የምድር ነገዶች በዘርህ ይባረካሉ» የሚለው ተስፋ የተፈጸመው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ገላ. 3፥6-10። ይህን ዘር ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የሚከተለው ነው:-
ተስፋው የተነገረለት ዘር[ኢየሱስ ክርስቶስ] በመጽሐፍ ቅዱስ
- የሴቲቱ ዘር እና ጠላቱ፤ ዘፍ. 3፥15፤ ዘፍ. 22፥17።
- የምድር ነገዶች ሁሉ የሚባረኩበት ዘር፣ ዘፍ. 12፥3፤ 22፥18።
- እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ምድር አሸዋ የሚበዛ ዘር፣ ዘፍ. 13፥16።
- የእሴይ ዘር፣ ኢሳ. 11፥1-5 ።
- ተስፋው የተሰጠው ዘር፣ ገላ. 3፥19።
- በኛ ውስጥ የሚኖር ዘር፣ 1ዮሐ. 3፥9።
- የአብርሃም ዘር፤ ዕብ. 2፥16።
- የዳዊት ዘር፤ 1ዜና. 17፥11-13፤ ኢሳ. 9፥7፤11፥10፤ ራእ. 22፥16

## 2.21. ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ነው ያዳነን?

የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ለመረዳት፣ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን የመሥዋዕት ሥርዐት በመጠኑ እንመልከት፤
በብሉይ ኪዳን የሰዎችን ኃጢአት ለማስተስረይ በጎች መሥዋዕት ሆነው ደም መፍሰስ ነበረበት።





አንድ ኃጢአተኛ በጉን ወደ ካህኑ ይዞ ይመጣና፣ በበጉ ላይ እጁን ይጭናል፤ ካህኑ ከጸለየ በኋላ የሰውየውን ኃጢአት የተሸከመውን በግ አርዶ በእሳት ያቃጥለዋል፤ ከዚያ፣ ኃጢአተኛው ሰው በበጉ ደም ምክንያት የኃጢአትን ስርየት አግኝቶ በሰላም ይሄዳል፤ ዘሌ. 4፥1-35ን ያንብቡ። ነውር የሌለበት በግ የሰውየውን ነውር ተሸክሞ፣ የኃጢአተኛው ሰው ምትክ ሆኖ፣ የኃጢአት ዋጋ ሲሆን፣ በሰውየውና በእግዚአብሔር መካከል ዕርቅና ሰላም ይሆናል፤ ደም ሳይፈስ ግን ስርየት አልነበረምና፤ ዕብ. 9፥22።

ደሙ የሚያስተሰርይበት ምክንያት ከሕይወቱ የተነሣ ነው።
«የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፣ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና፣ በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት»፤ ዘሌ. 17፥11፡፡

የኃጢአት ደመወዝ ሞት በመሆኑ፤ አንድ ሕይወት ያለው ነገር መሞት ነበረበት። ሞት ሁልጊዜ በፍርድ የሚፈጸም ከሆነ፣ ማለት በሕመም ምክንያት ካልሆነ ከደም መፍሰስ ጋር የተያያዘ ነው፤ ደም የሕይወት መኖሪያ ነው፤ ሕይወት የሚኖረው በደም ውስጥ ነው፤ ደም ከፈሰሰ ሕይወት መጥፋቱን ስለሚያመለክት ኃጢአት ሕይወትን የሚጠይቅ፤ ፍርድ የሚያስከትል መሆኑን ያስገነዝበናል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰው ካለው ርኅራኄና ፍቅር የተነሣ በሰዎች ላይ ሊፈጸም ያለው ፍርድ፣ ነውር በሌለባቸው እንስሳት እንዲፈጸም በማድረግ ሰውን ከፍርድ አድኖታል። ከእንስሳት ይልቅ ሰው ክቡር መሆኑንም ገልጧል። የእንስሳት መሥዋዕት ሰውን የመተካት፣ ለሰው ቤዛ የመሆን ሥርዐት ነበር። ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ የቻለው በእንስሳው ሞት ምክንያት እንጂ፣ በራሱ ሥራ አለመሆኑን ልብ እንበል። ይህ ሥርዐት ወደ እብ የምንገባበትን የክርስቶስን ሥራ ያመለክት ነበር።

## 2.22. የእንስሳት መሥዋዕት ኃጢአትን ማስወገድ አለመቻሉ

እግዚአብሔር ግን በእንስሳት መሥዋዕት ደስ አላለውም፤ ምክንያቱም የእንስሳት ደም ሥጋን እንጂ ሕሊናን ሊያነጻ አልቻለም። ኃጢአትን ማስተስረይና ኃጢአትን ማስወገድ ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ኃጢአትን ማስተስረይ ማለት ኃጢአተኛው ሰው ኃጢአትን በድርጊት ከገለጠ በኋላ በእንስሳት ደም አማካኝነት «ይቅርታን ማግኘት» ማለት ነው። ኃጢአትን ማስወገድ ማለት ግን የኃጢአተኝነት ጠባይን

መለወጥ፣ ልብን ማደስ፣ የኀጢአት ሐሳብ የሚያመነጨውን ዋናውን የኀጢአተኝነት ባሕርይ ማስወገድ ማለት ነው በጠቅላላው የሕይወት ለውጥ ማግኘት ነው።

ኀጢአት እስካልተወገደ ድረስ፣ የሰው ልጅ ጽድቅን ሊያደርግ አይችልም፤ እናም ሁልጊዜ ኀጢአትን ከማስተስረይ ይልቅ፣ ኀጢአትን ጨርሶ ማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። የእንስሳት ደም ግን ኀጢአትን ያስተሰርያል እንጂ፣ ኀጢአትን ሊያስወግድ አይችልም። ይህ ማለት ለኀጢአተኞች ምትክ ሆኖ ኀጢአተኛውን ከሥጋ ፍርድ ለጊዜው ያድናል እንጂ፤ የሕይወት ለውጥን ሰጥቶ ንጹሕ ሕሊናን አያጐናጽፍም ማለት ነው። «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኀጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና» ይላል፤ ዕብ. 10፥4።

እግዚአብሔር የኀጢአት ይቅርታ ሲያደርግ ደስ የሚለው አምላክ ቢሆንም፣ ኀጢአት ጨርሶ ከሰው ሕይወት መወገድ እንዳለበት ግን የዘላለም ሐሳቡ ነው። ስለዚህ፣ የመሥዋዕት ብዛት ደስ አላሰኘውም። በዚህ ምክንያት እንዲህ ሲል ተናገረ፤
«የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል! ይላል እግዚአብሔር የሚቃጠለውን የአውራ በግ መሥዋዕትን እና የፍሪዳን ስብ ጠግቤአለሁ የበሬና የበግ ጠቦት የአውራ ፍየልም ደም ደስ አያሰኘኝም»፤ ኢሳ. 1፥11።
«መሥዋዕትንና ቍርባንን አልወደድህም፤ ሥጋን አዘጋጀህልኝ፤ የሚቃጠል እውነተኛ ስለ ኀጢአት በሚቀርበውን መሥዋዕት አልሻህም»፤ መዝ. 39፥6።

ምንም ያህል አምላካውያት ትእዛዛትን ደጋግመን ብንፈጽምም እንኳ፣ እግዚአብሔር ደስ ካልተሰኘ የምናመልከውን ሰዎች በሕሊና ፍጹም ሊያደርገን አይችልም። እግዚአብሔር የልባችንን ዐቋም እንጂ [ሥ]ራረጋችንን አይመለከትምና። የሰው የአምልኮቱ ዐላማ ደግሞ [እግ]ዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና ከእርሱ ደስታ በመካፈል በሕይወት መኖር [ነው]። የሰላማችን፣ የፍቅራችን፣ የደስታችን፣ የኀይላችን ዋና ምንጭ [እ]ግዚአብሔር ደስታ ነው። ሰማይ የሚከፈተው፣ በረከት የሚወርደው፣ [ም]ድር የምትታዘዘው፣ እግዚአብሔር ሲደሰት ነው፤ «የእግዚአብሔርም [ደ]ስታ ኀይላችሁ ነው»፤ ነህ. 8፥10።

## 2.23. ታዲያ እግዚአብሔር በምን ደስ ሊለው ይችላል?

እግዚአብሔር ደስ የተሰኘው በአንድያ ልጁ መሆኑን እንዲህ ሲል መስክሯል።





«እነሆም፣ ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ፣ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ»፤ ማቴ. 2፥16-17።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለቱንም ሥራዎች ማከናወን ይችላል፤ ኀጢአትን ማስተስረይና፣ ማስወገድ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ምትክ በመሆን፣ በሞቱ ኀጢአትን የሚያስተሰርይ፣ ሲሆን በትንሣኤውና በመንፈሱ ደግሞ፣ ኀጢአትን ከልባችን ጠርጎ የሚያስወግድ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ነው።

አብ፣ «በእርሱ ደስ ይለኛል» ያለው ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብና ፍጹም መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲገልጥ ነው። ይህን ምስክርነት የሰማው መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ፣ «የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ» ብሎአል፤ ዮሐ. 1፥29።

ሰው ወደ ቤተ መቅደሱ እየገሠገ፣ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበው የነበረው እንስሳ፣ ከሰው ወደ እግዚአብሔር የመጣ ነውና ኀጢአትን ብቻ ሊያስተሰርይ ችሏል፤ ከራሱ ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የመጣው ግን የእግዚአብሔር በግ በመሆኑ ኀጢአትን ማስተስረይና ማስወገድ የሚችል ነው።

ኀጢአት መወገድ አለበት፤ አለባለዚያ እውነተኛውን የልብ ዕረፍት ልናገኝና በእግዚአብሔር ልንደሰት አንችልም። ኀጢአት የልብ ችግር ነው፤ ልብ ከታመመ ጤና የለም። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጤናማ ግንኙነትና ሰላማዊ ኅብረት ሊኖር የሚችለው፣ የልባችን ኀጢአት ሲወገድ ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር «ዕርቅና ሰላም ከሌለ ደግሞ ምድራዊም ሆነ መንፈሳዊ ሰላም አይኖርም። ይህን ሰላማዊ ኅብረት የመሠረተው በሞቱ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆ፣ ኀጢአታችንን አስተስርዮና አስወግዶ ወደ አባቱ ያቀረበን፣ ነውር የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ስለዚህ አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላማዊ ኅብረትን ማድረግና ደስታውን መካፈል ነው፤ ይህም የሚሆነው ኀጢአት ሲወገድ ነው።

## 2.24. ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በግ ተባለ?

ኀጢአተኞች እጃቸውን ጭንውበት በደላቸውን ተሸከሞ በመስቀል ላይ ስለ ተሠዋ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ በግ በበረት

ተወልዶ፣ እንደ በግ ተሸጦ፣ ስለ ኀጢአታችን ተሠውቷል። ኢሳይያስ ምዕራፍ 53 ስለ ታረደው በግ እንደዚህ ይላል።

«የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል? በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጎአል፤ መልክና ውበት የለውም፤ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ፣ ከሰውም የተጣለ፣ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፤ እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ተጨነቀ፤ ተሣቀየም፤ አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፣ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኀጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር። እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኀጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፤ ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፤ ኀጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኀጢአት ተሸከመ፣ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።»

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከትምህርታችን ርእስ ጋር የሚመሳሰሉትን ጥቅሶች ወስደን እንመልከት፤-

«የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ» እና «እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ» የሚሉትን ቃላት እናስተውል

ተግሣጽ ማለት ቅጣ ማለት ነው፤ ከፍጥረታችን የቍጣ ልጆች እንደ ነበርን ያስታውሱ፤ ኤፌ. 2፥3።

እንግዲህ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሆነው መከራ፣ ግርፋት፣ ሥቃይ ሁሉ በእኛ ላይ ሊሆን የነበረው የእግዚአብሔር ተግሣጽ [ቍጣ]





ነው። በመስቀል ላይ በክርስቶስ የተፈጸመው ሁሉ የደኅንነታችን ተግሳጽ [ቍጣ] ነው። ይህ ሁሉ መከራ በክርስቶስ ላይ ለምን ደረሰ? ብንል መልሱ «እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ስላኖረ ነው» የሚል ይሆናል። ቍጥር 11 ላይ «ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፤ ኀጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል» ይላል።

ኀጢአቱን መሸከም ያለበት ኀጢአተኛው ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የኀጢአተኞችን ኀጢአት ነው የተሸከመው።

## 2.25. ቤዛ ብዙኃን

ቤዛ የሚለውን ቃል ከድነት ጋር ያለውን ምስጢር በሁለት ትርጒም ማጥናት እንችላለን።

አንደኛ ቤዛ «ምትክ» የሚል ትርጒም አለው፤ ይኸውም በአንድ ሰው ፈንታ ሌላ ተተክቶ ዕዳ መክፈሉን የሚያመለክት ነው። በብሉይ ኪዳን ሥርዐት ኀጢአተኛው በጉን በካህኑ ፊት ካቀረበ በኋላ፣ እጁን ይጭንበታል፤ ይህ የሚያሳየው፣ እንዲህ የሚያደርገው «እኔ ሞት ይገባኛል በድያለሁ» ሲል በጉን በራሱ ፈንታ መተካቱን ነበር። በጉም ለኀጢአተኛው ቤዛ ሆኖ ከተሠዋ በኋላ ኀጢአተኛው ነጻ ይሆናል።

«ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?»፤ ማቴ. 16፥ 26። የነፍስ ዋጋ እጅግ ውድ ነው፤ ነፍስ በእግዚአብሔር አስትንፋስ የተቀባች ስለ ሆነች፣ ዋጋዋ እንዲህ ቀላል አይደለም፣ ሰው ያለውን ሁሉ በጌታ ፊት ቢያቀርብ የነፍስ ዋጋ ሊሆን አይችልም።

ሁለተኛ ቤዛ የሚለው ቃል «ጥላ» የሚል ትርጒም አለው፤ ጥላ የፀሓይን ጨረር[ቍጣ] ወይም የዝናብንና የበረዶን ኀይል የሚከላከልና የሚገድብ ነው፤ ከላይ የሚወርደው ኀይል በጥላው ላይ በማረፉ ምክንያት በጥላው ሥር የተጠለለው ሰው ከጒዳት ያመልጣል።

ነገር ግን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት የነፍስ ዋጋ ሆኗል። በእኛ ፈንታ በደላችንን ተሸክሞ በመሞቱ ምትክ[ቤዛ] ሆኖናል። «የሰው ልጅ ሊያገለግል፣ ነፍሱንም ለብዙዎች «ቤዛ» ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም»፤ ማቴ 20፥28 ፤ ማር. 10፥45። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው ስለ ሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ብቸኛ መካከለኛ ነው፤ እኛም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን በእኛ ላይ ሊወርድ ከነበረው የኀጢአት ሞት ተሰውረናል። «በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት

አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም» ተብሎ ተጽፏል፤ ዮሐ. 3፥36። ጥላ የያዘን ሰው የፀሐይ ጨረር እንደማያገኘው ሁሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነን ሰውም የዘለዓለም ኵነኔ አያገኘውም፤ ሮሜ 8፥1። የፀሐዩ ጨረር በጥላው ላይ እንዳረፈ ሁሉ በእኛ ላይ ሊሆን የነበረው ሞትም በቤዛችን በክርስቶስ ላይ ሆኗል። «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን» እንዲል፤ ኢሳ. 53፥5። ለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ «ቤዛ ብዙኃን» የተባለው ስሙ የተመሰገነ ይሁን አሜን!!!

## 2.26. ከቍጣው እንድናለን

ሐዋርያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ቍጣ የምናመልጥበትን መንገድ እንዲህ ሲል ይገልጣል፤ «ይልቁንስ እንግዲህ በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን»፤ ሮሜ 5፥10። በዚህ ትምህርት ሁለት ነገሮችን እናስተውላለን።

የመጀመሪያው፣ እግዚአብሔር በዳኝነቱ የማይወላውል በመሆኑ፣ ፍርዱን በሞት ፈጽሟል፤ ይህም እውነተኛ ፍርዱን ወይም ትክክለኛ ዳኛ መሆኑን ያመለክታል።

ሁለተኛው፣ ፍርዱን በሰዎች ላይ በመፈጸም ፈንታ በአንድያ ልጁ ላይ እንዲፈጸም አድርጓል፤ የሁሉንም በደል በአንድ ልጁ ላይ አድርጎታል። ይህ ደግሞ ፍጹም የሆነውን ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያመለክታል፤ የሰውን ሞት የማይወድ ቸር መሆኑን እንረዳለን።

## 2.27. የእግዚአብሔር ዳኝነት[የእግዚአብሔር ፍርድ] ፍጹም ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ዳኛ በመሆኑ፣ እውነትን ፈራጅ ነው፤ ኀጢአትን የሚጸየፍ፣ ክፋትን ሳይቀጣ የማይቀር፣ ከኀጢአተኞች ጋር የማይተባበር እውነተኛ አምላክ ነው፤ ይህንም የሚያስረዳን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነው። የኀጢአት ደመወዝ ሞት ስለ ሆነ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በክርስቶስ ተፈጸመ፤ እግዚአብሔር ኀጢአትን የማይቀጣ ቢሆን ኖሮ ቅድስናው ባልታወቀም ነበር። ኀጢአትን መጸየፍና ተገቢውን ቅጣት መቅጣት ቅድስና ነው። እግዚአብሔር በፍርዱ ፍጹም ነው። ክፋትን ዝም ብሎ እንዳላየ ሆኖ አያልፍም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ሙስና ስለሌለ፣ ኀጢአተኛው ከነ ኀጢአቱ ወደ መንግሥቱ ገብቶ ከጻድቃን ጋር ኅብረት ማድረግ አይችልም። የኀጢአቱን ፍርድ





ካገኘ በኋላ ይቅርታን አግኝቶ ሊድን ይችላል። ስለዚህ እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ መፍረዱ የማያዳላ ቅዱስ ፈራጅ፣ እውነተኛ ዳኛም መሆኑን ያስተምረናል።

## 2.28. የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም ነው።

እግዚአብሔር ሳይፈርድ የማይቀር እውነተኛ ዳኛ እንደ ሆነ ሁሉ፣ እውነተኛ ወዳጅም ነው፤ ከዳኝነቱ በላይ በፍቅሩ ወደር የሌለው ፍጹም ነው፤ ይህን ፍቅሩን የምንረዳበት ዋና ነገር፣ በኀጢአተኞች ላይ እንዲፈጸም የወሰነውን ፍርድ፣ በአንድያ ልጁ ላይ ማድረጉ ነው። ሞትን መፍረዱ ትክክለኛ ዳኝነቱን ሲያመለክት፤ የሞትን ፍጻሜ በልጁ ላይ ማድረጉ ግን፣ ወደር የሌለው ፍቅሩን ያመለክታል። የሞትን ፍርድ በእያንዳንዱ ኀጢአተኛ ላይ እንዲፈጸም ቢያደርግ ኖሮ፣ ኀጢአትን ያልሠራ ከፍርድ ሊያመልጥ የሚችል ባለመኖሩ አንድም ሰው አይተርፍም ነበር። ነገር ግን የኀጢአትን ፍርድ ሁሉ በልጁ ሞት ፈጽሞ እኛን ከሞት ፍርድ አዳነን። ጌታ «ተፈጸመ» ሲል በመስቀል ላይ ያተናገረው ይህንን የኀጢአት ፍርድ ነው። እንዴት የሚያስደንቅ ፍቅር ነው!

በክርስቶስ ሞት ስለ እግዚአብሔር የምንረዳው ቢኖር እውነተኛ ፈራጅና እውነተኛ ወዳጅ መሆኑን ነው።

«ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል»፤ ሮሜ 5፥8።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው «አንተ ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» የሚለውን የፍርድ ቃል ሲናገር፣ «እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል» የሚለውን የማዳን ቃልም ተናግሯል። ስለዚህ ፍርዱን በመስቀል ላይ ተሸክሞልን ከሞት አዳነን። እግዚአብሔር እራሱ የኛን በደል ተሸክሞ አዳነን እንዴት አስደናቂ ፍቅር ነው? ፍርዱ ትክክል ነው፤ ፍቅሩም ፍጹም ነው፤ «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው ርኅራኄው አያልቅም» ተብሎ እንደ ተጻፈ በምሕረቱ ቤዛ ሆነልን፤ ሰቆ. 3፥22።

በዚህ የክርስቶስ የፍቅር ሥራ፣ የሰይጣን ሥራው ሁሉ ፈርሶበታል፤ ሰይጣን ሰውን ኀጢአት በማሠራት በሰው ላይ ፍርድን አመጣ፤ ክርስቶስ ግን ጽድቅን በመሥራት መዳንን አመጣ፤ ይህ ለሰይጣን ትልቅ ውድቀት ነው፤ ለዘመናት የሠራው ሁሉ በአንዱ የመስቀል ሥራ በአንድ ጀምበር ፈርሶበታልና። «የእግዚአብሔር ልጅ የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ ተገለጠ» እንዲል፤ 1ዮሐ. 3፥19። ክብር፣ ምስጋና፣ አምልኮና ስግደት ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን!!!

## 2.29. መዳን በሌላ በማንም የለም

እንግዲህ ሰው መዳን የሚችለው ስለ ኀጢአቱ ዋጋ ሲከፍል ብቻ ነው፤ የኀጢአት ደመወዝ ሞት ስለ ሆነ፤ ሮሜ 6፥23። እግዚአብሔር ኀጢአትን መቅጣት ባሕርዩ ነው። ኀጢአት ይዘገያል እንጂ ፍርድን ያመጣል፤ ነገር ግን በኀጢአት ከሚመጣ ሞት ያድነን ዘንድ የኀጢአትን ዋጋ [ደመወዝን] በመክፈል ፍቅሩን ሰጠን። በዚህ ፍቅር ካልሆነ በሰው ወይም በሌላ ፍጡር መዳን አይቻልም።

ይህን የኀጢአት ደመወዝ የከፈለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በመሆኑ መዳን በሌላ በማንም የለም።

ይህ ማለት፡-

= እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበት፣
= የደኅንነታችን ተማሣጽ[ቍጣ] ያረፈበት፣
= እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ያኖረበት፣
= ኀጢአታችንን ተሸክሞ በመስቀል የሞተ፣
= ሞቶ የተነሣ፣
= ያረገ፣
= በአብ ቀኝ የተቀመጠ፣ ማንም የለም። መዳን የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

በዓለም ላይ የተመሠረቱ ሃይማኖቶች ሁሉ ከዚህ የመዳን መንገድ ሰው እንዲወጣ ለማሳሳት የተፈለሰፉ ፍልስፍናዎች እንጂ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ መንገዶች አይደሉም።

«ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት፣ ሕይወትም ነኝ። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» አለ፤ ዮሐ. 14፥6።

አብ በክርስቶስ በኩል ያልመጣውን አይቀበልም፤ አብ በወልድ ህልው ስለ ሆነ፣ ከወልድ ተለይቶ አይሠራምና፣ የሥላሴ መለኮታዊ ውሳኔ አለ፤ ይህ መለኮታዊ ውሳኔ፣ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የሰውነት ሥራ ወደ ሥላሴ ኅብረት በመግባት ዘላለማዊ ሕይወትን ተካፍሎ በሕይወት እንዲኖር ነው።

ሰው ይህን ሕይወት የሚያገኝበትን መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ሠርቶታል፤ ከዚህ የክርስቶስ ሥራ የተሻለ፣ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብ የሚችል የለም። ዋናው ጥያቄ ሃይማኖት፡- የመልካም ሰዎች በምድር ላይ መገኘት፣ እውነት መናገር፣ ስጦታ መስጠት አይደለም። እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ





የኀጢአት ስርየት ካገኘ በኋላ የሚመጡ ናቸው፤ ምሕረት የማግኘቱ ምልክቶች ናቸው።

ዋናው የእግዚአብሔር ጥያቄ «የኀጢአት ዋጋ ይከፈል» የሚል ነው። «ኀጢአት ይወገድ» ይላል እግዚአብሔር። የኀጢአት ዋጋ ካልተከፈለና ኀጢአት ተገቢውን ቅጣት ካላገኘ፣ እግዚአብሔር ከወንጀለኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ባሕርዩ አይደለም። ነገር ግን ይህን የኀጢአት ዋጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን ከፍሎታል፤ ይህም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ የሚያፈርስ ነው። በዚህ መለኮታዊ ሥራ የተስማማ ሁሉ፣ ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል፤ ኤፌ. 2፥13-18።

«በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን»፤ 1ቆሮ. 3፥4። በክርስቶስ በኩል ያለው እምነት ወደ እግዚአብሔር ሊያደርስ የሚያስችል ነው፤ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚያስችል ብቃት የለንም፤ ይህን ብቃት እና ድፍረት በኢየሱስ ክርስቶስ አግኝተናል። «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በዐዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን...» ይላል፤ ዕብ. 10፥19።

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሆነው ሥራ ሳይታመኑ በግል ጥረት ወደ አብ ለመድረስ መሞከር ከንቱ ድፍረት ነው። ወይም በአብና በወልድ መካከል ያለውን መለኮታዊ አንድነት አለመረዳት ነው። አብ «በእርሱ ደስ ይለኛል» ያለውን ቃል ማስታወስ ይገባል፤ አብን እንደዚህ ያስደሰተ ሌላ ማን ሊኖር ይችላል?

«መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና»፤ የሐዋ. 4፥12።

ጴጥሮስ ይህን ቃል በሚናገርበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶአል፤ የሐዋ. 4፥8። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተለየ አይደለም። ጌታ «ለኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል» እንዳለ፣ ዮሐ. 16፥13፤ መንፈስ ቅዱስ የአብንና የወልድን መለኮታዊ ውሳኔ ደግሞ ተናግሯል። ይኸውም ከሰማይ በታች ምንም የታወቀ እና የከበረ ስም ቢኖር እንኳ ሊያድን እንደማይችል ነው። «ሌላ የለም» የሚለው ቃል ነገሩ ያለቀና የተጠናቀቀ መሆኑን ያስረዳናል። የኀጢአትን መሥዋዕት ያቀረበው ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ንስሓና የኀጢአት ስርየት የሚደረገውም በእርሱ ስም ብቻ ነው።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» ይላል፤ የሐዋ 10፥43። ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጭ የኀጢአት ስርየት ይገኛል ብሎ የሚመሰክር እና የሚያስተምር ቢኖር ከሰይጣን ወይም ከሰው አእምሮ የተገኘ ብቻ ነው።

**2.30. «በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ቤዛነት በኩል»**

«ልዩነት የለምና ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል፣ በክርስቶስ ኢየሱስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስረያ አድርጎ አቆመው»፤ ሮሜ 3፥23-25።

ቃሉን አስተውለን እንመልከት፤ ቤዛነቱ እንዲያው እንድንጸድቅ የተቈጠረልን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፤ ቤዛነቱ በእምነት የሚገኝ በደሙ የሚፈጸም ማስተስረያ ነው። ይህም ለዘላዓለም የቆመ ኪዳን ስለ ሆነ አይለወጥም። በዚህ ቤዛነት በኩል የመጣ ይድናል፤ ይህን ቤዛነት ረግጦ በሌላ መንገድ ለመዳን የሚሞክር ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ ስለ ናቀ ሕይወትን አያገኝም፤ ዕብ. 10፥29። የኀጢአት ስርየት በደም ስለ ሆነ ደምን በማፍሰስ ዓለምን ያዳነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በመሆኑ ነው። «ያድናሉ» እየተባሉ የሚሰበከላቸው፣ ወይም «አናድናለን» የሚሉ ሰባኪዎች ቢኖሩ «በየትኛው ንጹሕ ደማችሁ? የት አለ ደማችሁ?» ብለን ልንጠይቅ ይገባል፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር መለኮታዊ ውሳኔ ደሙን ስለኛ በማፍሰስ ቤዛ የሆነን ከክርስቶስ ውጭ ማንም የለም።

«እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም»፤ ዕብ. 9፥23።

«በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፣ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፣ እኛስ እንዲህ ዐይነቱን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?» ይላል ዕብ. 2፥2-3 ። የሙሴን ሕግ ያልፈጸመ ሞት ይፈረድበት እንደ ነበረ ሁሉ፡-ከዚህ የእግዚአብሔር መንገድ ውጭ የኀጢአት ስርየት ለማግኘት መሞከርም ከንቱ ድካም ከመሆንም አልፎ የእግዚአብሔርን ልጅ እንደ መርገጥ፣ የጸጋውን መንፈስ እንደ ማክፋፋት እና የኪዳኑን ደም እንደ መናቅ ስለሚቈጠር ከባድ ቅጣት አለው። ቃሉ እንዲህ ይላል፤

«የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው፣ ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቈጠረ፣ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ





እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» ይላል፤ ዕብ. 10፥28-31።

አስቀድመን እንዳየነው እግዚአብሔር ለሰው ባለው ፍቅር ፍጹም ነው፤ ባዳኝነቱም ፍጹም ነው፤ በእነዚህ በሁለቱ ቅዱሳን ባሕርያቱ ምክንያት ኀጢአት በመስቀል ላይ እንዲፈረድበትና የሰው ልጆች ከቍጣው እንዲድኑ ሆኗል። ፍርዱ በመስቀል ላይ የተፈጸመ ሲሆን፣ ፍቅሩም በዚያው በመስቀል ላይ ተገልጧል፤ ይህ እግዚአብሔር ለዓለም የለገሰው ነጻ ስጦታ ነው። እንግዲህ እንዲህ ዐይነቱን መለኮታዊ ስጦታ ቸል ብንል ከፍርድ አናመልጥም። ይህን ክቡር ስጦታ መቀበልና እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል።

## ምዕራፍ ሦስት
## ጽድቅ

### 3.1. ጽድቅ ምንድን ነው?

ጽድቅ በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት እንከን የለሽ ሥራ፣ ብቃት ያልጐደለው፣ ተቀባይነት ያለው፣ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ተግባር ማለት ነው። ጻድቅ ማለትም በዚህ ከላይ በተገለጠው ትርጒም ተመዝኖ የሚያልፍ ሰው ማለት ነው። ሕግም ሆነ ጸጋ ለሰው የተሰጡበት ምክንያት እንዲህ ዐይነቱን ጽድቅ ለማስገኘት ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑ ሥራው ሁሉ የጽድቅ ነው፤ እርሱ ከሰው የሚፈልገውም ጽድቅን ነው። ነገር ግን ከሰው ጠባይ የተነሣ እንከን የለሽ ጽድቅ ከማንም ሰው አልተገኘም። እኛ ሰዎች የምናደርገው ሁሉ ጽድቅ ሊመስለን ይችላል፤ ትክክለኛነቱ ግን አልተረጋገጠም። ምክንያቱም፣ የምናደርገው ትክክል ቢመስለን እንኳ ብቃት የጐደለው ወይም እንከን ያለው ነው። መልካም ለመሥራት በምናደርገው ትግል ውስጥ ክፉ እንሠራለን። ስለዚህ ጽድቃችን እንከን አልባ አይደለም። እግዚአብሔር መልካም ምን እንደ ሆነ ነግሮናል፤ እኛ ሰዎች የምናድርገው ግን እግዚአብሔር የነገረንን ሳይሆን ለኛ መልካም መስሎ የታየንን ነው፤ ስለዚህ ጽድቃችን ብቃት ያለው ጽድቅ አይደለም።

ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ነው፤ ኢሳ. 64፥6።

የመርገም ጨርቅ ማለት ደም የነካው ልብስ ማለት ነው። በተለይም ሴቶች በወር አበባቸው ወቅት የሚለብሱት ልብስ «የመርገም ጨርቅ» ይባላል። በድሮው ዘመን ሴቶች በወር አበባቸው ወቅት ምንም ያህል ቢጠነቀቁ እንኳ የደም ጠብታ በልብሳቸው ላይ ይታይ ነበር፤ በገጠራቱ የኢትዮጵያ ክፍልም ይህ ሁኔታ እስካሁን ይታያል። ሴቲቱ የለበሰችው ልብስ ገላዋን መሸፈን ቢችልም ትንሽ ደም ስለነካው ብቻ በሰው ፊት ያንን ለብሶ ለመታየት ያሳፍራታል፤ ልብሱን ያየ ሰውም ቅር ይለዋል።

እኛ ሥጋ ለባሾች የምናደርገው መልካም ነገር ሁሉ ለጊዜው ከሚከሠት ክፉ ነገር ቢሸፍፍነንም፣ እንከን የለሽ ሥራ ሠርተን ግን አናውቅም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው። ብዙ መልካም ሥራ ሠርተን በሌላ ጊዜ በምንሠራው አንድ ወይም ሁለት ኀጢአት ምክንያት ሥራችን ሁሉ ክብር የጐደለው ይሆናል። ይህ እግዚአብሔርን አያስደስትም፣ ሰው በራሱ ጥረት ጻድቅ ሆኖ እግዚአብሔርን አያስደንቀውም። ቴማናዊው ኤልፋዝ የሰውን ብቃት





አልባነት ሲገልጽ፣ «ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይሆን ዘንድ ከሴትስ የተወለደ ንጹሕ ይሆን ዘንድ እንዴት ይችላል?» ብሏል፤ ኢዮ. 15፥14።

በሰው ልጆች ታሪክ ጽድቅን ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ በመሆኑ በኀጢአት ከወደቀ በኋላ ጽድቅን የሚጠማ ፍጡር ሆኗል፤ ይህንንም ሁልጊዜ አጥብቆ ይፈልጋል፤ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው ጽድቅን የተራቡ ናቸው። ነገሥታት በአገዛዛቸው ጽድቅን አላመጡም፤ ካህናት በአገልግሎታቸው ጽድቅን አላስገኙም፤ ነቢያት በስብከታቸው ጽድቅን አላመጡም። የእንስሳት መሥዋዕት የኀጢአት ዋጋ እየተከፈለበት የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ስላልሆነ፣ ጽድቅን አላመጣም። ሌሎች ከእምነት ውጭ የሆኑ የሰው ልጅ ድርጅቶች እንደ ተባበሩት መንግሥታት ያሉ ታላላልቅ ተቋሞች እግዚአብሔር የሚፈልገውን፣ ሰውም የሚያስፈልገውን ጽድቅ አላመጡም፤ የተቋቋሙት ግን ጽድቅን [ፍትሕን] ፍለጋ ነው።

ሽብርተኞች በሰው ላይ በኀብ የሚያፈነዱት ለመጽደቅ ነው፤ ለመጽደቅ አስበው ተኩነኑ። በዓለም ላይ ያሉ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ጽድቅን እንደሚያመጡ ይናገራሉ፤ የተፈለሰፉትም ለዚህ ጉዳይ ነው፤ በቡድሃ ሃይማኖት ያሉት ከሴት በመራቅ፣ እስላሞች ከምግብ፣ ከክርስቲያን፣ ከቆሻሻ ነገር በመራቅ፤ አይሁዶች ከምግብና ከአሕዛብ በመራቅ ጽድቅን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ጽድቅን አላመጡም። በሀገራችን ረጃጅም መንፈሳውያን ጕዞዎች የሚደረጉት ጽድቅን ፍለጋ ነው። በበረሓ፣ በዱር፣ በገደል እራሳቸውን እየጨቁኑ ቅጠል እየበሉ የሚኖሩ ሰዎችም እንደዚህ የሚሆኑት ጽድቅን ፈልገው ነው። በባዶ እግር የሚሄዱ፣ ከሰው ጋር የማይነጋገሩ፣ ከጋብቻ ርቀው ሴት በዞረችበት የማይዞሩ፣ ብዙ ድግስ በመደገስ ሕዝብ የሚመግቡ ብዙ ቀና ሰዎች አሉ፤ እነዚህ ሁሉ ለምን እንደዚህ እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ ጽድቅን ፈልገው እንደሚያደርጉት ይናገራሉ። የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የሚለይበት አንዱና ዋናው ነገር ጽድቅን መፈለጉ ነው። ጽድቅ ግን እነዚህን በመሳሰሉ ሕጎች፣ በተለያዩ ፍልስፍናዎች፣ በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፤ እስከ ዛሬ ቢፈለግም አልተገኘም። በራሱ መንገድ ወይም በራሱ ጥረት የጸደቀ የሰው ልጅም እስካሁን የለም። አዬ ሰው ምስኪን ፍጥረት ነው! ሰው ጽድቅን ፍለጋ በመንከራተት ላይ ነው፤ ሲንከራተት እየደከመው የወደቀውንማ እግዚአብሔር ይወቀው።

እግዚአብሔር ይህን የሰዎችን ጥረት ያውቃል፤ ነገር ግን፤ የሰው ፍልስፍና፣ አስተሳሰብ፣ ስሜትና ዕውቀት ነውና አይደርስበትም፤ እውነተኛውን የጽድቅ መንገድ የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነውና፤ ስለዚህ ጽድቅ ከራሱ ከእግዚአብሔር የሚመጣ እንጂ ከሰው ጥረት የሚገኝ አይደለም።

እግዚአብሔር ሁሉንም አይቶ ማንም እንደ እርሱ የሚሆን ባለማግኘቱ የራሱ ክንድና የራሱ ጽድቅ፣ ጽድቅን እንዳመጣለት ይናገራል። «እግዚአብሔር አየ፤ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ፣ ሰውም እንደሌለ አየ፣ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ፣ ተደነቀም፤ ስለዚህ፣ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፤ ጽድቁም አገዘው፤ ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፣ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቊር አደረገ»፤ ኢሳ. 59፥16-17።

እስካሁን ያየነውን የሰውን የጽድቅ ጥረት እናቁይና፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ እንይ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን አምጥቷል። ዓለም እስካሁን አጥብቆ የሚፈልገው ጽድቅ በመስቀል ላይ ተገኝቷል። ዓለም እስካሁን በችግር ላይ የሚገኘው በመስቀል ላይ የተገኘውን ጽድቅ ችላ ብሎ የራሱን ጽድቅ ለማቆም ስለሚንከራተት ነው። እውነተኛው ጽድቅ ግን በእውነት ተገኝቷል። እውነተኛ ጽድቅ ትክክለኛነቱና ብቃቱ ወይም አንከን የለሽነቱ የሚረጋገጠው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነውና እርሱን እንየው።

## 3.2. የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ

ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የአብ ቃል ነው። የሚታየውና የማይታየው ሁሉ የተፈጠረው በእርሱ ነው፤ ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም።

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፤ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ አልሆነም» ዮሐ. 1፥1-2።

ኢየሱስ የሕይወት ፈጣሪና የፍጥረት መኖሪያ ነው፤ እርሱ ሕይወት ነው፤ ፍጥረት የሚኖረው፣ የሚንቀሳቀሰውም በእርሱ ሕይወትነት ላይ ተመሥርቶ ነው፤ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል ይደግፋል፤ ዕብ. 1፥2-3። ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ ናቸው፤ ዕብ. 1፥3። ወልድን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር የሚተካከለው የለም። ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ቃል ስለ ሆነ፣ በክብሩ ከአብ ጋር እኩል ነው። እርሱ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ተሰውሮ የሚኖር አምላክ ነው። በመለኮታዊ ሥልጣን





ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሉዓላዊነት [በእግዚአብሔርነት] የሚኖረው ቃል፣ በተለየ አካሉ ወደ ምድር መጣ፤ ቃል ሥጋ ሆነ፤ ዮሐ. 1፥14። ወደ ምድር የመጣው እግዚአብሔርነቱን ስለ ተቀማ አይደለም። ማንነቱ እንዳለ ሆኖ፣ ክብሩን ብቻ ትቶ ራሱን ዝቅ በማድረጉ ነው እንጂ። የሰውን ሥጋ በመልበስ የባሪያን መልክ ያዘ፤ ሰው የኢየሱስ ባሪያ ነው፤ ነገር ግን ይህ የሰው ጌታ ባሪያውን በመሆን ተገለጠ፤ ከዚያ ማንም ሊደርስበት ከማይችል መለኮታዊ ከፍታ፣ እጅግ በጣም ዝቅ ብሎ ሰው ሆነ፤ ሰው ሆኖም በዝቅተኛነት በሚታወቀው የመስቀል ሞት ሞተ። ይህ ነው የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ፤

«እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤ ነገር ግን፣ የባሪያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ»፤ ፊል.2፥6-8።

የመጀመሪያው ዝቅታ የባሪያውን መልክ ይዞ መገለጡ ነው፤ ሁለተኛው ዝቅታ መሞቱ ነው። ሦስተኛው ዝቅታ በመስቀል መሞቱ ነው፤ ታሞ መሞት እና በመስቀል መሞት የተለያዩ ናቸው። ከዚህ የሚበልጥ ጽድቅ የለም፤ ከመለኮታዊ ክብር ወደ ባሪያ ኑሮ መውረድ ከዚህም ወልፎ ለመስቀል ሞት ራስን አሳልፎ መስጠት አስደናቂ ጽድቅ ነው። መላእክቱም እንዲህ ዐይነቱን ጽድቅ አልሠሩትም፤ እነርሱ የኢየሱስን ያህል ዝቅ ቢሉ እንኳ ጽድቃቸው የእርሱን ጽድቅ አይወዳደረውም። እርሱ ፈጣሪ ነው፤ እነርሱ ፍጡራን ናቸው፤ እርሱ ጌታ ነው፤ እነርሱ አገልጋዮች ናቸው። ኀጢአተኛውን የሰው ልጅማ ወደዚህ ውድድር አናስጠጋውም፤ አስደናቂ የሚሆነው ባሪያ ጌታ ሲሆንና ጌታ ደግሞ ባሪያ ሲሆን ነው። ስለዚህ ሰው መጀመሪያውኑ ባሪያ ነውና፣ ራሱን ዝቅ ቢያደርግ አያስደንቅም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መጀመሪያውኑ ጌታ ነውና፣ አሁን ባሪያ ቢሆን እጅግ ያስደንቃል። የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ብቃት ያለው ጽድቅ ነው፤ አብም «በእርሱ ደስ ይለኛል» ሲል የመሰከረው የጽድቁን ታላቅነት ለመግለጥ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ እንደኛ ባሪያ የሆነው የኛን ጉድለት ለመሸፈን ነው፤ ስለዚህ፣ የእርሱ ጽድቅ ብቁና ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ሁላችንንም ለማጽደቅ ይበቃል።

## 3.3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ልጅነቱ ሲታይ

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ቢሆንም ደግሞ ፍጹም ሰውና በምድር ላይ ሲኖር እንዴት እንደ ኖረ እንመልከት።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲኖር ፍጹም ትሑት አገልጋይ ነበር፤ ገና በልጅነቱ በናዝሬት ሲያድግ ለእናቱና ለዘመዶቹ ይታዘዝ ነበር፤ በሰው ፊትና በእግዚአብሔር ፊት በማስተዋል አደገ፤ ሉቃ. 2፥51-52። ይህ ከሰው ጋር ሲኖር የፈጸመው ጽድቅ ነው።

በዚህ ምድር ላይ በሰው መካከል የሚኖሩ ድኾች፣ በሽተኞች፤ ኀጢአተኞች፣ ሰው ያገለላቸውና ፈጽሞ የረሳቸው አሉ። እግዚአብሔር በቃሉ እነዚህን ሁሉ ችል እንዳንል አዝዞ ነበር፤ ዘዳ. 15፥7-11። ነገር ግን ይህን ያደረገ ጻድቅ ሰው አልተገኘም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሁሉም የኅብረተ ሰብእ ክፍል ይልቅ፣ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ሰዎችን እጅግ ይፈልግ ነበር። እነርሱም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለመቀመጥ አይሸማቀቁም ነበር፤ ማቴ. 9፥10። ሰው የረሳቸውን እርሱ ያስባቸዋል፤ ሰው የጣላቸውን እርሱ ያነሣቸዋል፤ ሰው ያገለላቸውን እርሱ ያስጠጋቸዋል፤ ሳምራዊት ሴት ዐምስት ባሎች ነበሯት፤ ከዚህ የተነሣ የኅብረተ ሰቡ መጠቋቆሚያ ነበረች፤ ወደ ወንዝ ውሃ ልትቀዳ የምትሄደው ሴቶች በማይወጡበትና እየሩ በሚሞቅበት የቀትር ጊዜ ነበር፤ ይህን የምታደርገው የሰዎች መጫወቻ ከመሆን ለመሸሽ ነው። በኀጢአተኝነቷ ሰው ሁሉ ስላገለላት ብቸኛ መሆንን የመረጠች ትመስላለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እርሷን ፍለጋ ወደ ሰማርያ ሄዶ አገኛት፤ ለዘላለም የማያስጠማውን የሕይወትን ውሃም ሰጣት፤ ይህች ሴት ሕይወቷ ተለወጠ፡፡ ሌሎችን ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው እንዲያዩ ጋበዘች፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመድ፣ ወንድም እኅትም ለሌላቸው ሁሉ ዘመድ፣ ወንድም እና እኅት ነው። ሰው የተጸየፋቸውን በሽተኞች እርሱ ተጠግቶ ይረዳቸዋል፤ ዮሐ. 5፥1-10። የተራቡትን ይመግባቸዋል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ለሚኖሩ ለነዚህ የተረሱ ሰዎች ሁሉ መድኃኒት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ረጅም ጾም በመጾሙ እጅግ ተርቧል። በዚህ ጊዜ ሰይጣን በተደጋጋሚ ቢፈትነውም፣ በእግዚአብሔር ቃል ድል ነሥቶታል። ቀን ቀን ወንጌልን ይሰብካል፣ ሌሊት ግን በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይጸልይ ነበር። የእግዚአብሔርን በዓላት በቤተ መቅደስ እየተገኘ አክብሯል። እንደ ሙሴ ሥርዐት ሁሉንም ፈጽሟል።

አይሁድ በልዩ ልዩ ምክንያት ይከሱት ነበር፤ እርሱ ግን ማንንም አልከሰሰም፤ ሲሰድቡት አልተሳደበም፤ ሲዝቱበት አልዛተም፤ እርሱ እነርሱን ለመበቀል ኀይል አለው፤ ነገር ግን ሰውን ለማዳን ስለ መጣ አልተበቀላቸውም። ሊወግሩት ድንጋይ ሲያነሡ ኀይል እንደሌለው ይከማ





ሰው ይሸሽ ነበር፤ ዮሐ 8፥59። ከሰው ወገን እንደዚህ ዐይነቱን ጽድቅ የፈጸመ የለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የማያደርገውን አያስተምርም ነበር። ትምህርቱ በሙሉ እርሱ ያደረገው ነው። «ክፉውን በክፉ አትቃወሙ» ብሎ ሲያስተምር እርሱ ክፉ ላደረጉበት በጎ አድርጎ ነው። «ጕንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት» ብሎ ሲያስተምር እርሱ በጥፊ ሲመቱት ዝም ብሎ ነው። «ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ» ብሎ አስተምሮ ነበር፤ ማቴ.5፥43። ይህን ራሱ በተግባር ፈጽሞታል፤ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት መከራ ያመጡበትን ይቅር ብሏቸዋል፤ ለጠላቶቹ መልካም አድርጓል። እንዲህ ዐይነት ጽድቅ ከወዴት ይገኛል?

«የእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ፣ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ፣ የእናንተ ባሪያ ይሁን እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ፣ እንዲያገለግሉት አልመጣም» ብሏል፤ ማቴ. 20፥26-28። ታላቁ አምላካችን ትሑት ሆኖ የሰው አገልጋይ ሆኖ መጣ፤ ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፤ የታላቅነት መንገድ ዝቅ ብሎ ማገልገል ነው፤ ታላቅነት በዘር፣ ቀድሞ በመገኘት፣ በሀብትና በሹመት መሆኑ ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በኋላ ቀርቷል። አሁን ታላቅነት ወደ ላይ በመገሥገሥ ሳይሆን ወደ ታች በመውረድ ሆኗል። ነገሩ ተገላብጧል፤ ይህን ለውጥ ያመጣ ግን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ነው።

## 3.4. ሕግን ልፈጽም መጣሁ፤ ማቴ. 5፥17።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ልጅነቱ ሲታይ ሕግን ያለምንም እንከን ፈጽሟል። «አንድም ጻድቅ የለም» ተብሎ ተከፋ በተቈረጠበት ዓለም ላይ፣ አንድ ጻድቅ ተገኝቷል። ነቢዩ ኢሳይያስ «ቡቃያ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አደገ» (ኢሳ. 53፥2) ያለው አንድም ጻድቅ በሌለበት ዓለም ብቸኛ ሆኖ መገኘቱን ለመናገር ነው። ሥር ብዙ ጊዜ በደረቅ መሬት ውስጥ ሳይደርቅ መቈየት ይችላል፤ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ፈታኝና ክፉ ዓለም ውስጥ በጽድቅና በእውነት የኖረ ብቸኛው ጻድቅ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ ጠንቅቆ የፈጸመም እርሱ ብቻ ነው።

## 3.5. ሕግ በሁለት መንገድ ይፈጸማል

### 1ኛ በሕይወቱ ሕግን ፈጽሟል።

በሕግ «አድርግ» የተባለውን በማድረግ፣ «አታድርግ» የተባለውንም ባለማድረግ ይፈጸማል። ይህን ግን በብቃት ያደረገ ሥጋ ለባሽ አልተገኘም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሥጋ ለብሶ ሕግን ፈጽሟል። ጌታችን «ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሠኝ ማን ነው?» ብሏል፤ ዮሐ. 8፥46። ጲላጦስ «እኔስ አንዳች በደል ስንኳ አላገኘሁበትም» አለ፤ ዮሐ. 18፥38። ነገር ግን ሕዝቡ ኢየሱስን በግፍ ለመግደል ሁከት ሲያበዛ «እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ»፤ ማቴ. 27፥24። ይሁዳም «ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ» ብሏል፤ ማቴ. 27፥4። በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ «ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም» አለ፤ ሉቃ. 23፥41። እንግዲህ ወንበዴዎችም ጌታችን ምንም ክፉት ያላደረገ መሆኑን፣ የመጨረሻው ዳኛ ንጉሥ ጲላጦስም በደል እንዳልተገኘበት፣ ይሁዳም ንጹሕ ሰው መሆኑን በተለያየ ጊዜና ሁኔታ መስክረዋል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የማይገባው ፍጹም ጻድቅ ነው።

### 2ኛ በሞትና በግርፋት ሕግን ፈጽሟል።

ሕግ በሕይወት ካልተፈጸመ በሞትና በግርፋት በእስራት በመሳሰለው ሁሉ ይፈጸማል። ይህን ሲፈጽሙ የኖሩት ሥጋዊ ሕግ የተሰጣቸው እስራኤል ዘሥጋ ሲሆኑ፣ አሕዛብም በኃጢአታቸው ሲሞቱ ኖረዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በእንደዚህ ዐይነቱ የሕግ አፈጻጸም ውስጥ መግባት አይገባውም ነበር። ነገር ግን ይህ አፈጻጸም ሕግን ላልፈጸሙ ኃጢአተኞች ቤዛ የሚሆንበት የሕግ ፍጻሜ ነው።

«ጻድቅ ባሪያዬ በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፤ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል፤ ስለዚህም፣ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና ከዐመፀኞችም ጋር ተቈጥሯልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ ዐመፀኞችም ማለደ» ተብሎ ተጽፏል፤ ኢሳ. 53፥11-12። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአመጸኞች ጋር ተቈጥሮ ተሰቀለ፤ እርሱ ግን ዐመፅ አልተገኘበትም፣ በመከራው ጊዜ የኃጢአተኞችን ኃጢአት ተሸክሞ ስለ ነበረ ምንም ክፉ ቃል አልተናገረም፤ እንዲያውም ስለ ዐመፀኞች ይማልድ ነበር። «ሲሰድቡት አልተሳደበም፤ መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን





በጽድቅ ለሚፈርደው ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ»፤ 1ጴጥ. 2፥23። ታዲያ እንዲህ ዐይነት ልዩ ጽድቅ ከማን ይገኛል?

ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ የሕግን ዋጋ ከፍሏል፤ ይህም ለኃጢአተኞች የከፈለው ነው። «ሕግን ልሽር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ» እንዳለ ሕግን ሳይሽር በሕይወቱና በሞቱ ፈጸመው፤ ማቴ. 5፥17። ስለዚህ የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ኢየሱስ ራሱ የሕግ ፍጻሜ ነው፤ ሮሜ 10፥4።

## 3.6. የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ ሮሜ 3፥21።

«የእግዚአብሔር ጽድቅ» ማለት የራሱ የሆነ እግዚአብሔር የሠራው ጽድቅ ማለት ነው። ሰው ወይም መላእክት ሳያግዙት በራሱ ፈቃድ ሠርቶ ያቆመው የማይፈርስና የማይናወጥ የዘለዓለም ሥራ ነው። ይህ ጽድቅ ለሰው ሁሉ የሚበቃ ለደካማዎችና ዐቅም ለሌላቸው ሁሉ መጠጊያ የሚሆን ነው። ሰው ከሠራው ይልቅ እግዚአብሔር የሠራው ይበልጣልና ሁሉንም ያስጠልላል። እግዚአብሔር ይህን ጽድቅ የሠራው ሰዎችን ከሕግ ክስ ነጻ አውጥቶ ለማጽደቅ ነው። ሕግ ማስገኘት ያልቻለውን ጽድቅ እግዚአብሔር በጸጋው ሠርቶታል። ነቢዩ ኢሳይያስ «አቤቱ ሥራችንን ሠርተህልናልና ሰላምን ትሰጠናለህ»፤ 26፥12።

ይህ የእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ በክርስቶስ ሰው ሆኖ መገለጥ፣ በሞቱና በትንሣኤው የተፈጸመው ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው። እንግዲህ እኛም ኃጢአተኞች የምንጸድቀው በዚህ የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆኑን መጻሕፍት ተስማምተው ይመሠክራሉ። «ያለ ሕግ ተገልጧል» የሚለው ቃል በክርስቶስ ያመኑ ኃጢአተኞች ጉዳይ «በሕግ አይታይም» ማለት ነው። በሕግ ቢታይማ መጀመሪያውኑ ኃጢአተኛ የሆኑት ሕግን ሽረው ነውና ሊጸድቁ አይችሉም። አሁን የኃጢአተኞች ጉዳይ በክርስቶስ ይታያል፤ ጽድቅ በክርስቶስ እንጂ በሕግ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በሕግ ያልተቻለው በክርስቶስ ይቻላል።

«አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው»፤ ሮሜ 3፥21። እግዚአብሔር ያመኑትን ክርስቲያኖች ጉዳይ በሕግ እያየውም ጉዳያችን የሚታየው በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንደ ሆነ ቃሉ ይመሰክርልናል። «በክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው

ይጸድቃሉ» ይላል ሮሜ 3፥23። በሌላ አነጋገር፣ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው በክርስቶስ በኩል ነው። በሕግ ብንቀርብ ከፍርድ አናመልጥም፤ ምክንያቱም፣ ሕግን ሁሉ አልጠበቅንምና። በክርስቶስ ከሆነ ግን እንድናለን፤ እርሱ «የሕግ ፍጻሜ» ሆኗልና፤ ሮሜ 10፥4። በእግዚአብሔር ጽድቅ «መጽደቅ» ማለት እንደዚህ ነው።

ኢሳይያስ በትንቢቱ «እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ» ይላል፤ ኢሳ. 53፥6። ሕግ በደላችንን በእኛ ላይ በማኖር «ይሙቱ» ይላል፤ ክርስቶስ ግን በደላችንን በእርሱ ላይ በማኖር «ይዳኑ» ይላል። እኛ ልንሠራው የማንችለውን ጽድቅ ክርስቶስ በመስቀሉ ሠርቶታል። ስለዚህ እኛን ደካማዎችን በእርሱ ጽድቅ ያለ ሕግ ሊያጸድቀን ይችላል።

ሕግ አሁንም አልተሻረም፤ ሆኖም የሚፈልገውን ዋጋ በክርስቶስ አምነው ንስሓ ከገቡት ላይ ማግኘት አይችልም፤ «ለምን» ቢባል መልሱ እግዚአብሔር በደላቸውን በክርስቶስ ላይ አድርጎታልና ነው ። በክርስቶስ ያመኑ በክርስቶስ ሞተዋል፤ ሮሜ 6፥5። የሞተ ደግሞ በሕግ አይጠየቅም። ሕግ በሕይወት ላለ እንጂ በሞተ ሰው ላይ አይሠራም። በክርስቶስ ያመነ ክርስቲያንም የክርስቶስን ሞት «የራሴ ሞት ነው» ብሎ ሲያምን ከዚህ በኋላ በሥጋዊ ሕይወት እየኖረ አይደለም፤ ሮሜ 6፥2። ሕግም አይገዛውም። ቅዱስ ጳውሎስ፣ «አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፣ ከሕግ ተፈትተናል፤ ስለዚህም በዐዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም» ብሏል፤ ሮሜ 7፥6።

ክርስቲያን በክርስቶስ ይገዛል፤ ሕጉን በክርስቶስ ይፈጽማል፤ ለክርስቶስ ሲገዛ ሕግ በሕይወቱ ይፈጸማል። ለክርስቶስ ያልተገዛ ግን ሕግን መፈጸም አይችልም። ለምሳሌ፣ ሰው ምግብ የሚበላው በሕግ ስለ ተደነገገ ሳይሆን ተፈጥሮው ስለ ሆነ ነው፤ ክርስቲያንም ሕግን የሚፈጽመው ተጽፎ ስላነበበ ሳይሆን፣ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ሕግን መፈጸም የሚችል ሆኖ ስለ ተለወጠ ነው። አሮጌው ማንነት በክርስቶስ መስቀል ሲሞት ዐዲስ ማንነት ይገኛል። ይህ ዐዲስ ተፈጥሮ ከፊደል ሕግ ነጻ ሆኖ በእምነት ሕግ የሚኖር ነው፤ ሮሜ 8፥4።

## 3.7. *<u>ሥራችን ሳይሆን እምነታችን ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረልን</u>*

«ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል»፤ ሮሜ 4፥5። ይህ ቃል አንዳንድ መልካም ነገሮችን በማድረግ በጌታ ዘንድ ጽድቃቸውን ለማስቈጠር





ለሚሞክሩ ኢአማንያን ሁሉ ተስፋ የሚያስቈርጥ ነው። «ለማይሠራ» የሚለው ቃል ዝም ተብሎ የሚታለፍ ቃል አይደለም።

ገና ኀጢአተኛ የነበረ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሲያምን እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል። የኀጢተኞች ጽድቅ በጌታ ፊት እንደ መርገም ጨርቅ ስለ ሆነ፣ ጽድቅ ሆኖ አይቈጠርም፤ ኢሳ. 64፥6። እግዚአብሔር ክፉ ሥራን በመልካም ሥራ ስለማይመዝን የኀጢአተኞች መልካም ሥራ ለጽድቅ አያበቃም። የኀጢአት ደመወዝ ሞት እንጂ መልካም ሥራ አይደለም፤ ሮሜ 6፥23። ስለዚህ ኀጢአተኞች የሚጸድቁበት መንገድ እምነት ነው። እምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልበትና ከመድኀኒታችን ጋር የምንገናኝበት መንፈሳዊ እጃችን ነው። እምነት ጽድቅ ሆኖ የሚቈጠርበት ምክንያት የታመነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን በመፈጸሙ፣ ይህም በሞቱና በትንሣኤው ስለ ተረጋገጠ ነው። እግዚአብሔር አብም «በእርሱ ደስ ይለኛል» ብሏል፤ ማቴ 3፥17። ስለዚህ ይህ የክርስቶስ ጽድቅ እንደሚያድናቸው ለሚያምኑ ኀጢአተኞች እምነታቸው ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርላቸዋል። ይህ ሥራ የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ በመሆኑ «አሜን» ብለን ከመቀበል በቀር ለመከራከር የሚያበቃ እንዳች ዕውቀት የለንምና ዝም እንበል!

«ስለ በደላችን ዐልፎ የተሰጠውን፣ እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው» ይላል፤ ሮሜ 4፥25።

ንስሓ የሚገቡ ኀጢአተኞችን እግዚአብሔር ማጽደቅ እንደሚችል ማመን አለብን። ሰው በሥራው ሁለት ዐይነት ድርጊት ይታይበታል። አንደኛ፣ ጽድቅን ይሠራል፤ ሁለተኛ፣ ኀጢአትንም ይሠራል። ሁለቱ ሥራዎቹ በጌታ ፊት በአንድ ላይ አይመዘኑም፤ ኀጢአቱ በጽድቁ፣ ጽድቁ በኀጢአቱ አይለኩም። ስለዚህ እግዚአብሔር ሁለቱንም የሰው ሥራዎች ትቶ የራሱን ሥራ ይፈጽማል፤ እርሱም አምነው ንስሓ የገቡትን ማጽደቅ ነው። ያላመኑትም በፍርድ ውስጥ ይኖራሉ፤ ዮሐ.3፥16-19፡36።

## 3.8. <u>«በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኀጢአትን በሥጋ ኰነነ»፤ ሮሜ 8፥4</u>።

ሰው በኀጢአተኛ ባሕርይው (በሥጋ ጠባዩ) የሕግን ትእዛዝ ሊፈጽም አይችልም። ኀጢአት የሚባለው ክፉ ኀይል ከሰው እስካልተወገደ ድረስ፣ የእግዚአብሔር ሕግ በሰው ሕይወት ሊፈጸም ከቶ

አይችልም። ጌታ ሰዎች የማይችሉትን ይችሉ ዘንድ አስቀድሞ ኀጢአትን በሥጋ ኩነነ ማለት ኀጢአትን አላደረገም፤ ኀጢአትን አለማድረግ ኀጢአትን መኰነን ነው። ከዚያም በመስቀል ላይ አስወገደው። እንድም ኀጢአትን በሥጋው ኰነነ ማለት ኀጢአት ኀይል እንዳይኖረው በክርስቶስ የቅድስና ሕይወትና የመስቀል ሥራ ተሸነፈ ማለት ነው። «ይህን ያደረገው የሕግ ትእዛዝ በእኛ ማለት በእማኞች ሕይወት ይፈጸም ዘንድ ነው። ሥጋ ለብሶ ኀጢአትን ያሸነፈ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህ በእምነት ከእርሱ የሚወለድ ሁሉ ዘሩ በእርሱ አለና ኀጢአትን ያሸንፋል። ሰው ሁሉ በኀጢአት የተሸነፈው የአሮጌው አዳም ዘር በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ስላለ ነው። እንዲሁም የሁለተኛው አዳም የክርስቶስ አማኝና ተከታይ የሆነ ሰው እርሱ ኀጢአትን በሥጋው እንደ ኰነነ አማኙም በእምነት ኀጢአትን ያሸንፋል። ነገሩ የዘር ጉዳይ ነው። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔርም ተወልዷልና ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም» ይላል፤ ፤ዮሐ. 3፥9። ኀጢአትን ማድረግ የዘር እንደ ሆነ ሁሉ፣ ጽድቅን ማድረግም የዘር ነው።

የእግዚአብሔር ሕግ በኀጢአተኛው ሥጋችን ላይ ለመፍረድ፣ ሥልጣን አለው። ምክንያቱም ሥጋዊ ጠባያችን የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈጸም ኀይል ስለሌለው፣ በዘሩም ደካማ ስለ ሆነ ከፍርድ ወይም ከኩነኔ ነጻ አይሆንም። አሮጌው ዘራችን የኀጢአትና የሞት ሕግ ያለው ነው፤ ማለት በኀጢአትና በሞት ኀይል ሥር የወደቀ ነው፤ ሮሜ 8፥2። ዐዲሱ ዘራችን ግን የሕይወት መንፈስ ሕግ ያለው ነው፤ ማለት የጽድቅን ኑሮ ለመኖር የሚያስችል የሕይወት ኀይል ያለው ነው። በዚህ አጋጣሚ ጳውሎስ «የኀጢአትና የሞት ሕግ» የሚለው የሙሴን ሕግ ሳይሆን ያሮጌውን ዘር የኑሮ ዘይቤ ነው። ከዚህ የኀጢአት ኀይል ከሚገዛው ካሮጌው ኑሮ ነጻ ሊያወጣን የሚችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት ሕግ ነው። ይህ የሕይወት ሕግ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ ያሳየን ኀጢአትን በሥጋ ተገልጦ ድል የነሣበት የጽድቅ ኑሮ ነው።

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ዐርነት አውጥቶኛልና»፤ ሮሜ 8፥1-2።

«በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» የሚለው አረፍተ ነገር ሁለት ሐሳቦችን ያስረዳናል፤ አንደኛው፣ ለሚያምኑ ሁሉ የክርስቶስ ጽድቅ ስለሚቈጠርላቸው፣ የክርስቶስ ጽድቅ ነጻ ያደርጋቸዋልና ከፍርድ ነጻ ናቸው፤ ሁለተኛው፣ በክርስቶስ በሚኖሩ ሁሉ የሕይወት





መንፈስ ሕግ በእነርሱ ስላለ የሕግ ትእዛዝ በሕይወታቸው ይፈጸማል፤ ስለዚህ እነርሱን የሚኰንን ሕግ አይኖርም ማለት ነው። ይህን ቃል ለመረዳት አንድ ምሳሌ እንውሰድ፤ አውሮፕላን ወደ ከፍተኛ ሰፍራ ከመንቀሳቀሱ በፊት ለስበት ሕግ የተገዛ ነው፡፡ በምድር ላይ እርፎ በሚቈይበት ጊዜ ሁሉ ለስበት ተገዝቶ ይኖራል። አውሮፕላኑ ከስበት ሕግ አርነት ለመውጣት ከስበት ሕግ በላይ ኀይል ያለው ወይም የስበትን ሕግ የሚሽር ሌላ ኀይል ያስፈልገዋል፤ አውሮፕላን ምንም ግዙፍ ቢሆን እንዲህ በአየር ላይ ተንሳፎ የምንመለከተው ከስበት ሕግ በላይ የሚያደርገው ሌላ ሕግ ስላገኘ ነው። እኛም ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ የሚያደርገን ኀይል በክርስቶስ አግኝተናል፤ እርሱም የሕይወት መንፈስ ሕግ ነው።

ይህ በክርስቶስ በማመን ያገኘው ኀይል ኀጢአትንና ዓለማዊነትን አሸንፈን በጽድቅና በእውነት ኑሮ እንድንንሳፈፍ ያደርገናል፤ ቲቶ 2፥11። የክርስቶስ ሕግ እንጂ የዓለማዊነት ሕግ አይገዛንም፤ ለዓለም ሳይሆን ለክርስቶስ እንኖራለን። ሐዋርያው «ከኀጢአትም ዐርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» ብሏል፤ ሮሜ 6፥18።

## 3.9. «ጸጋው በእምነት አድኗችኋል»፤ ኤፌ. 2፥10፡፡

ሐዋርያው በፊተኛው ኑሯቸው ኀጢአተኛ ሆነው የኖሩትን፣ በኋላ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑትን የኤፌሶን ክርስቲያኖች፦ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡ እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠረን» አላቸው፤ ኤፌ. 2፥8-10።

እነዚህ የኤፌሶን ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ለመዳን የሚያበቃ መልካም ሥራ አልነበራቸውም፤ እንዲያውም በኀጢአታቸውና በበደላቸው ሙታን የነበሩ ናቸው፤ ኤፌ. 2፥1። በአየር ላይ ሥልጣን ባለው አለቃ (ሰይጣን) ፈቃድ ሲመሩ ኖረዋል፤ ኤፌ.2፥2። ከእግዚአብሔር መንግሥትና ከእስራኤል ተስፋ የራቁ ነበሩ፤ ኤፌ.2፥12 ስለዚህ፣ እነዚህ ሰዎች በኀጢአተኝነታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ቍጣ ሥር የነበሩ ናቸው። በጨለማ ያለ ተስፋ ከእግዚአብሔር ተለይተው ይኖሩ ነበር፡፡

እነዚህ ተስፋ ያልነበራቸው ሰዎች አንድ ቀን የእውነትን ቃል፤ ይኸውም የሚያድነውን ወንጌል ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። እምነውም ከኀጢአትና ከሞት ፍርድ ድነው በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ። «እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፣ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ» እንዲል፤ ኤፌ. 1፥13።

እነዚህ ሰዎች የዳኑት በሥራቸው ወይስ በእምነታቸው? «በሥራቸው ነው» እንዳንል በዲያብሎስ ፈቃድ ሲመሩ የኖሩ ናቸው። ጳውሎስም፣ «ይህም ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ቊ. 8) ብሏቸዋል። ስለዚህ መዳን ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አይደለም። የኤፌሶን ክርስቲያኖች በሥራቸው አልዳኑም። እንዲሁም በወንጌል አምኖ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በእምነቱ እንጂ በሥራው የዳነ አይደለም፤ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋል» የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ነጻ ስጦታና የሰዎችን በጸጋው ማመን የሚያመለክት ቃል ነው።

ሰው በመጀመሪያ የሚድነው ጸጋውን በእምነት በመቀበል ነው፤ ሰው ሥራው ከፉ ነው፤ ወደ ኀጢአትም ያዘነበለ ነው፤ በዚህ ምክንያት ማንኛውም ሰው በፍርድ ሥር ነው። ከዚህ ሊያድነው የሚችለው እምነቱ ነው። ሥራውማ ለፍርድ አቅርቦታል፤ ማለት እንደ ሥራው ቢሆን ሞት ይገባዋል። እንደ እምነቱ ግን ከሞት ይድናል። «እግዚአብሔር ሰዎችን በእምነት የሚያድነው ለምንድን ነው?» ለሚለው ጥያቄ አንደኛ ለማጽደቅ፣ ሁለተኛ ጽድቅንም እንዲሠሩ ነው። አምነው የጸደቁ ሰዎች ጽድቅን እንጂ ክፋትን አይሠሩም «ጸድቀናል» እያሉ ክፋትን የሚሠሩ ከሆነ ግን ገና አለመጽደቃቸውን ያመለክታል። ጽድቅን የምንሠራው ስለ ጻደቅን እንጂ ለመጽደቅ አይደለም፤ ክፋንም የምንሠራው ክፉ ስለ ሆንን እንጂ ክፉ ለመሆን አይደለም።

«ልጆች ሆይ ማንም አያስታችሁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፤ ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፤ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኀጢአትን ያደርጋል» ይላል፤ 1ዮሐ. 3፥7።

መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፤ ኤፌ.2፥10። እግዚአብሔር ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም ነው ያዳነን፤ ገላ. 1፥4። ያሁኑ ዓለም እንደምናውቀው የኀጢአትና የክፋት አሠራር የሞላበት፣ የጥፋት ዓለም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ያዳነን ከእንዲህ ዐይነቱ ዓለም ነው። በዚህ ክፉ በሚሠራበት ዓለም ውስጥ ሆነን





መልካሙን ለመሥራት ተጠራን። ኢየሱስ ክርስቶስ ከክፋው ዓለም ባያድነን ኖሮ እኛ መልካም መሥራት አንችልም ነበር፤ ምክንያቱም እኛው ራሳችን እዚያው ውስጥ ስለ ነበርን መልካም መሥራት አይሆንልንም። ከዚህ ክፉ ዓለም የወጣነው መልካም ሠርተን ሳይሆን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ለመዳናችን የተከፈለ ዋጋ እንደ ሆነ አምነን ነው።

## 3.10. እግዚአብሔር ጽድቁን ማሳየት ይፈልጋል

«እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙ የሆነ ማስተስረያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኀጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፤ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ) አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው»፤ ሮሜ 3፥25-26።

የኀጢአት ስርየት በጥረት ሳይሆን፣ በእምነት የሚገኝ ነው፤ የሰው ጥረት ኀጢአትን ቢያስተስርይ ኖሮ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ባላስፈለገም ነበር። እግዚአብሔር በፊት የተደረገውን ኀጢአት ማለት የሰው ዘር ሁሉ የወደቀበትን ስሕተት በመተው ችሎታውን አሳይቷል፤ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል፤ እግዚአብሔር ይቅር ማለት ይችላል፤ ይቅር አለማለትም ይችላል፤ እግዚአብሔርን «ለምን ይህን አደረግህ?» ብሎ የሚወቅሠው የለም። ሁሉን እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። ሌላው እግዚአብሔር ኀያልነቱን ወይም ፈራጅነቱን ብቻ ሳይሆን ጽድቁንም(ርኅራኄውንም) አሳይቷል። ጽድቁን ያሳየውም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምነውን ኀጢአተኛ በማጽደቅ ነው። እግዚአብሔር የእርሱን መልካም ሥራ ማሳየት ይፈልጋል፤ ሞት የሚገባውን ኀጢአተኛ ማጽደቁ ይህ የራሱ የእግዚአብሔር መልካም ሥራ ነው። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በእኛ ሥራ ሳይሆን በራሱ ሥራ ሊያጸድቀን ይፈልጋል። የእኛው ጽድቅ ብቃት ስለ ጐደለው፣ እግዚአብሔር የራሱን ብቁ የሆነ ጽድቅ ሊያሳየን ይፈልጋል። ኑ የእግዚአብሔርን ጽድቅ እንይ!

## 3.11. በፍቅር የሚሠራ እምነት፤ ገላ. 5፥9።

እምነት ዝም ብሎ በትክክል የታወቀ ሐሳብ፣ የፍልስፍና ትምህርት ወይም የአእምሮ አመለካከት አይደለም። እምነት በሥራ የሚገለጥ ነው፤ እምነት የሚታይና የሚጨበጥ ነገርን ይሠራል። የእምነት ሥራ በልብ ተሰውሮ የሚቀመጥ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው በግልጥ ሊያዩት የሚችሉት ሥራ ይሠራል። እምነት የሚሠራው ግን

በፍቅር ነው። የክርስትና እምነት እና ሌሎች ሃይማኖቶች የሚለዩት በዚህ ነው። ሌሎች ሃይማኖቶች በግድ በጉልበት ወይም በሕግ የሚሠሩ ናቸው። በክርስቶስ ያለው እምነት የሚሠራው ግን በፍቅር ብቻ ነው። የክርስትና እምነት በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ስለ ሆነ፣ አሠራሩም በነጻ ፈቃድ ወይም በፍቅር ነው።

የአብርሃምን እምነት ለምሳሌ ብንመለከት፣ በነጻ ፈቃድ የሚሠራ እምነት ነበር። ከሀገሩና ከወገኑ ተለይቶ የወጣው በእምነት እንጂ፣ በጉልበት አይደለም። ወይም በረኃብና በጦርነት ምክንያት ተሰዶ አይደለም፤ ሚስቱ ሣራና እርሱ አርጅተው መውለድ ከማይችሉበት ዕድሜ ሲደርሱ፣ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚወልዱ ነገራቸው። ይህንም የእግዚአብሔር ቃል አመኑና ይስሐቅን ወለዱ፤ ዘፍ. 18፥10-14 ። ይስሐቅ የተወለደው በአብርሃም እምነት ነው፤ ዘፍ. 21፥1-3 ። አብርሃም ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርበው በእግዚአብሔር ሲጠየቅ፣ አማኝ ነውና በፍቅር ታዘዞ አቀረበው፤ ዘፍ. 22፥9-10። አብርሃም በእምነት እግዚአብሔርን ስለሚወድ ልጁን ለመስጠት እምቢ አላለም፤ የአብርሃም እምነት እየሠራ ነበር ማለት ነው፤ አብርሃም በእምነቱ እግዚአብሔርን ታዘዘ። በዚህ ሁሉ የአብርሃም እምነት ጽድቅ ሆኖ ተቈጥሯል፤ እምነቱ ግን እደዚህ በፍቅር የሚሠራ እንጂ፣ ዝም ብሎ አመለካከት ወይም ዕውቀት ብቻ አልነበረም። ዛሬም «አምነናል» የምንል ሰዎች እግዚአብሔርን የማንታዘዝ ከሆን እምነታችን ከንቱ ነው።

ሙሴ «ባሕሩን በበትሬ መትቼ እከፍለዋለሁ» ብሎ በአእምሮው ቢያስብ የማይቻል ነገር ነው። እምነት ግን ከአእምሮ በላይ የሆኑ ነገሮችን የሚሠራ ኀይል ነውና፣ ለሙሴ እምነት አስፈለገው። ሙሴ እግዚአብሔር የነገረውን ቃል ስላመነ ባሕሩን በበትር መታው፤ ባሕሩም ደረቀ። በእምነት ካልሆነ እንደዚህ ዐይነት አስደናቂ ነገሮችን መሥራት አይቻልም። እንግዲህ ሙሴ በራሱ አመላካከት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ቃል የሚያምን ሰው ነበር፤ ስለዚህ እምነቱ የሚሠራ ነው። የሌሎችንም አማኞች እምነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ብንመለከተው የሚታይና የሚጨበጥ ነገር የሠራ እምነት ነው።

እኛም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን እምነታችን ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረልን ኀጢአተኞች ነን። በእግዚአብሔር ፍቅር ይቅርታን የተቀበልን ኀጢአተኞች እንደ መሆናችን መጠን እንዲሁ እምነታችን በፍቅር የሚሠራ መሆን አለበት። ጌታ «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ… እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» (ማቴ. 5፥13-14) ሲለን፣ እምነታችን





አመለካከት ወይም የአእምሮ ትክክለኛ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን በፍቅር የሚሠራ ሕያው መሆኑን መንገሩ ነው። እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው።
እምነቱ የሞተ ሰው ሥራውም የሞተ ነው፤ ማለት ሥራው ሁሉ የከፋት የተንኰል ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ይላል፤ ያዕ. 2፥26። ከሥራ የተለየ እምነት ትክክለኛ ዕውቀት እንጂ ሕያው የሆነ ኀይል የለውም። ሐዋርያው ያዕቆብና ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጽድቅና ስለ እምነት የጻፉት የተለያየ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን አይለያዩም፤ አገላለጹ ተለያየ እንጂ ሐሳቡ አንድ ነው። ያዕቆብ በመልእክቱ «እምነት አለኝ» ስለሚል፣ ነገር ግን እምነቱን ማሳየት ስለማይችል ሰው እየተናገረ ሲሆን፣ ጳውሎስ ደግሞ መጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ስለምንታረቅበት የመጀመሪያ እምነት ወይም ከእግዚአብሔር ዳግም ስለ ተወለድንበት እምነት ይናገራል። ጳውሎስ «ኀጢአተኞች ይቅርታ የሚያገኙት በክርስቶስ ደም ነው» ይላል። ያዕቆብ ደግሞ «አዎ ይቅርታ አግኝተሃል ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅህን፣ ኀጢአትህ የተወገደ መሆኑን፤ ዳግም መወለድህንና የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን በሕይወትህ አሳየኝ» ይላል። ጳውሎስ በሮሜ 1፥5 ላይ፤ «በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን» ይላል። «ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ» የሚለውና «እምነትህን በሥራህ አሳየኝ» የሚለው አንድ ሐሳብ ያለው ነው። በእርግጥም በክርስቶስ አምኖ በደሙ የጸደቀ ሰው መጽደቁን በሥራው ማሳየት አለበት። ጸድቄያለሁ እያለ ሥራው ክፉ ከሆነ ግን እምነቱ የሞተ ወይም አስመሳይ እንጂ ትክክለኛ እምነት ያለው ሰው አይደለም ወይም ትክክለኛ ዕውቀት ያለው ሰው ብቻ ነው። በደሙ የጸደቀ ሰው ሥራውም የጽድቅ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስም፣ «ዐውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም» በማለት ያረጋግጣል፤ 1ዮሐ. 2፥4። «ልጆች ሆይ ማንም አያስታችሁ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው። ኀጢአትን የሚያደርግ ግን ከዲያብሎስ ነው»፤ 1ዮሐ. 3፥7።

እምነት በተግባር የሚታይ እንጂ፣ ዝም ብሎ የሚነገር ብቻ አይደለም። ነገር ግን ወደዚህ ሕይወት መግባት የሚቻለው መጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመንና ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ነው። አለበለዚያ ሰው በባሕርዩ ኀጢአተኛ ስለ ሆነ በራሱ ጥረት ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ አይችልም። የሞተ መንፈስ ሕያው ሊሆን

የሚችለው በክርስቶስ ነው፤ በጥረት ሕያው መሆን አይቻልም። ነገር ግን ሕያው የሆነ ሰው ወደ ክርስቶስ ለመድረስ እጅግ መጣር አለበት።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት መንገድ በእምነት መሆኑን ሲናገር ያዕቆብ ደግሞ «ይህ የታረቅንበት እምነት የሚሠራ አንጂ፣ ዝም ብሎ ዕውቀት አይደለም» ይላል። ሁለቱም ሐዋርያት ትክክል ናቸው። ዛሬ «አምኛለሁ ድኛለሁ» እያሉ ነገር ግን የመዳን ምልክት የማይታይባቸው ክፍሎች ራሳቸውን እንደ ገና ቢመረምሩ መልካም ይሆንላቸዋል። «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ» ተብሏል፤2ቆሮ.13፥5።

### 3.12. አራቱ የእግዚአብሔር የፍርድ መንገዶች

1ኛ በሥራ ይፈርዳል
2ኛ በሕሊና ይፈርዳል
3ኛ በሕግ ይፈርዳል
4ኛ በወንጌል ይፈርዳል

### 3.12.1. በሥራ ይፈርዳል

«እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል»፤ ሮሜ 2፥6።
ይህ ቃል ከሮሜ ም 1፥18-32 ላይ ካለው መልእክት ጋር የተያያዘ ነው። እንደ ሥራቸው የሚፈረድባቸው ምን ዐይነት ሰዎች እንደ ሆኑ፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተዘርዝረዋል። እነርሱም፥ እውነትን በዐመፃ የሚከለክሉ፤ እግዚአብሔር በፍጥረት ምክንያት የተገለጠላቸው ነገር ግን የማያምኑ፤ እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን የማያከብሩት፤ «ጥበበኞች ነን» የሚሉ፤ ነገር ግን ደንቆሮ የሆኑ፤ የእግዚአብሔርን ክብር በሰውና በእንስሳ ምስል የለወጡ ናቸው። በዚህ ምክንያት የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር የተዋቸው ሰዎች ሁሉ እንደ ሥራቸው ይፈረድባቸዋል።

እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሰዎች ብዙ ናቸው። ይህ ዓለም እንዴት ተገኘ? ተብለው ሲጠየቁ እንዲሁ ተገኘ የሚል ዐጭር መልስ በመስጠት ራሳቸውን የዘጉ ናቸው። ሕሊናቸው ግን በትክክል በእግዚአብሔር የተሠራ በመሆኑ እውነቱን ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል፤ በቃሉ ደግሞ ይታመናል። አሁን በዐይናችን በግልጥ የምናየው ዓለም ሰማይና ምድር፣ በውስጣቸው ያለው ፍጥረት አሠራርና ሥርዐት ሁሉ እንዲሁ ዝም ብሎ የተዘረጋ አይደለም። ከዚህ የፍጥረት ሥርዐት በስተ ጀርባ አንድ ኀይል መኖሩ ለማንኛውም አእምሮ ላለው ሰው ግልጥ ነው። ያ ኀይልም እግዚአብሔር ብለን የምንጠራው





የሕይወት መሠረትና መገኛ የሆነ አምላክ ነው። «ዐዋቂዎች ነን» የሚሉ ሰዎች ይህን አምላክ ያውቃሉ፤ ነገር ግን እንደ አምላክነቱ ማክበርና ማመስገን ስለማይፈልጉ፣ ሀልዎቱን ይክዳሉ። ያወቁ መስሏቸው ደንቆሮ ሆኑ። ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ፍላጎታቸው ይሆኑ ዘንድ ስለ ተዋቸው፣ መለኮታዊው እውነት ተሰወረባቸው። የጽድቅና የፍትሕ፣ የቅድስናም ምስጢር ተለያቸው፤ በዚህ ምክንያት ጾታቸውን እስከማይለዩ ድረስ ማለት ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከሴት ጋር ግብረ ሥጋ እስኪፈጽሙ ድረስ ደነዘዙ። እግዚአብሔርንም ለማወቅ፣ ስሙን ለመጥራት፣ ለማምለክና እርሱን ለመቅረብ ባልወደዱት መጠን፣ ለማይረባ አእምሮ ተላልፈው ተሰጡ። ኀጢአት ተብሎ የሚታወቀው ሁሉ በእነርሱ ውስጥ ይገኛል። ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት፣ቅናት፣ ተንኰል፣ ውሸት፣ ትምክሕት፣ ትዕቢት ሁሉ ስለ ሞላባቸው ዓለምን ከፉ አድርገዋታል። ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ሰዎች እንደ ሥራቸው ይፈረድባቸዋል፤ ራእ. 22፥11-13።

### 3.12.2. በሕሊና ይፈርዳል

እግዚአብሔርን የማያውቁ፣ ወንጌልንም ያልሰሙ፣ ሕግም የሌላቸው አሕዛብ ደግሞ በሕሊናቸው ይፈረድባቸዋል። በዚህ አቅጣጫ የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቁ፤ ያልተማሩና ያላነበቡ ሁሉ ከሕሊና ፍርድ ነጻ አይደሉም። ማንኛውም በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ሰው ሁሉ ክፉና በጎን የሚያውቅበት ሕሊና አለው። የተጻፈ ሕግ ባይኖረውም «ሕገ ልቡና» የሚባል የሕሊና ሕግ አለው። አሕዛብ ክፉ ሲያደርጉ ክፉታቸውን የሚነግራቸው ሕግ ባይኖራቸውም፣ ሕሊናቸው ግን ትክክል አለመሆናቸውን ይነግራቸዋል። በክርስቶስ አምነው ካልዳኑ በስተቀር፣ ከፍርድ የሚያመልጡበት መንገድ የለም።

«ሕግ የሌላቸው አሕዛብ፣ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፣ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ» ይላል፤ ሮሜ 2፥14-15። ሕግ በድንጋይ ጽላት ተጽፎ ከመሰጠቱ በፊት፣ በልብ ውስጥ ነበር። እግዚአብሔርን የሚያምኑ ሰዎች በሕገ ልቡና እየተመሩ የጽድቅ ኑሮ ይኖሩ ነበር። ለምሳሌ፦ አቤል፤ ሄኖክ፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ በሕገ ልቡና የኖሩ ናቸው። በኋላ ግን በሙሴ አማካኝነት ሕግ በድንጋይ ተጽፎ ሲገለጥ፣ አፈጻጸሙም ዐብሮ ተገለጠ፤ የሕግ አፈጻጸም ሞትና ቅጣት ነው፤ ዘሌ. 20፥9-10። እንዲሁ አሕዛብ

በድንጋይ ላይ ወይም በመጽሐፍ የተጻፈ ሕግ ከነአፈጻጸሙ ባይኖራቸውም፣ በልባቸው የተጻፈው ሕግ ትክክል አለመሆናቸውን ይነግራቸዋል። አፈጻጸሙ ግን በመጽሐፍ ከተጻፈው ጋር ልዩነት የለውም፤ ይኸውም ሞት ነው፤ ዘሌ. 20፥9። «ያለ ሕግ ኀጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉ» ይላል፤ ሮሜ 2፥12። ይህ የሕሊና ፍርድ ይባላል። ማንኛውም ሰው ከሕሊና ፍርድ ነጻ አይደለም።

### 3.12.3. <u>በሕግ ይፈርዳል</u>

«ያለ ሕግ ኀጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና ሕግም ሳላቸው ኀጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል»፤ ሮሜ 2፥12። እግዚአብሔርን በማወቅ ሕግን የተቀበሉና ሕግን የሰሙ ሁሉ በሰሙትና በተቀበሉት ሕግ መሠረት ይፈረድባቸዋል። ሕግን ተቀብለው በሕግ የኖሩ አይሁድ ናቸው። ነገር ግን የሚመኩበትን ሕግ ራሳቸው ስላልፈጸሙት ሕጉ ራሱ ይፈርድባቸዋል።

«አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል፣ በሕግም ብትደገፍ፣ በእግዚአብሔርም ብትመካ፣ ፈቃዱንም ብታውቅ፣ ከሕግም ተምረህ የተሻለውን ፈትነህ ብትወድ በሕግም የዕውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ የዕውሮች መሪ፣ በጨለማም ላሉ ብርሃን፣ የሰነፎችም አስተማሪ፣ የሕጻናትም መምህር እንደ ሆንህ በራስህ ብትታመን፤ እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? «አትሥረቅ» ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? «አታመንዝር» የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን?» ይላል፤ ሮሜ 2፥17-23። የሕግ ፍርድ ግልጽና አሻሚነት የሌለው ፍርድ ነው። አይሁዳዊ ሕግ አለኝ ወይም ሕግን ዐውቃለሁ እያለ መመካት አያድነውም። ሕግን መፈጸም ይጠበቅበታል እንጂ። ግን ማን ሕግን ፈጽሞ ሊጸድቅ ይችላል? ሕግ በሚል ርእስ የዘጋጀውን ምዕራፍ ተመልከት።

### 3.12.4. <u>በወንጌል ይፈርዳል</u>

ወንጌል ማለት ኢቫንጀሊዮን ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጒሙም «የምሥራች» ማለት ነው። ወንጌል እንዴት የምሥራች ሊሆን ይችላል? ቢባል በሕሊናው፣ በሥራውና በሕጉ የተፈረደበት ሰው ከእግዚአብሔር ቍጣ መውጫ ማምለጫ የለውም። ስለዚህ፣ በኀጢአቱ ምክንያት ሞትና ፍርድ ለሚጠብቀው ሰው ከሞት ለመዳን የሚያስችል ማምለጫ መንገድ አለ፤ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው። ወንጌል በሞት ፍርድ ሥር ላለ ሰው የምሥራች ነው።





በኀጢአተኛው ምትክ የሞተውን በማመን ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ስለ ሆነ፣ ወንጌልን የምሥራች ያሰኘዋል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ ማድረግ የሚፈልግ ሰው የወንጌልን ኀይል መቀበል አለበት እለበለዚያ የመዳኛ መንገድ የለውም።

### <u>እግዚአብሔር በወንጌል ሦስት ዐይነት ፍርድ ይሰጣል።</u>

አንደኛው፣ ወንጌልን ሰምተው ባልተቀበሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው ፍርድ ነው። ሁለተኛው፣ ወንጌልን ተቀብለው እንደ ወንጌል ቃል ባልኖሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው ፍርድ ሲሆን፣ ሦስተኛውም ወንጌልን ተቀብለው በወንጌል ቃል መሠረት ለኖሩ ቅዱሳን የሚሰጠው የምስጋና ፍርድ ነው።

#### 1. <u>ወንጌልን ሰምተው ያልተቀበሉ ሰዎች</u>

ከፍርድ ሁሉ የከፋው ፍርድ ወንጌልን ሰምተው ባልተቀበሉ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ፍርድ ነው። ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ክብር የጐደላቸው ኀጢአተኞች ናቸው። ሕግን በመሻር፣ ክፋትንም በማድረግ ሁሉም በድሏል፤ ስለዚህ፣ ሁሉም የኀጢአቱን ዋጋ ሊቀበል ይገባው ነበር። እግዚአብሔር ግን በምሕረቱ ባለጠጋ ስለ ሆነ፣ ሰው ከሞት የሚድንበትን መንገድ በመስቀሉ ላይ አዘጋጅቷል፤ አንድያ ልጁን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል፤ እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁ ወዶታል፤ ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ የተገለጠ ነው። ይህን የእግዚአብሔርን የማዳን ጥሪ፣ ልዩ ፍቅር «አንቀበልም» ያሉና የክርስቶስን ደም የረገጡ ሰዎች የባሰ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። «የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቈጠረ፣ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?»፤ ዕብ. 10፥29።

እንደነዚህ ዐይነቶቹ ሰዎች ወንጌልን ሳይቀበሉ ይችላሉ። እግዚአብሔርን «የለም» የሚሉ፤ «ኩነኔና ጽድቅ የሚባል የለም» የሚሉ፤ በገዛ ጥረታቸውና በሥራቸው ለመዳን ዐጒል ተስፋ የያዙ፤ በሕግና በወጋቸው የሚመኩ፣ የአባት የእናት ሃይማኖታችን የሚሉና በዘር ሃይማኖት የተያዙ፣ ወይም የሆነ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑና «ሃይማኖት ስላለን ሌላ ሃይማኖት አያስፈልገንም» ብለው የሚያምኑ፤ «ኀጢአት የለብንም» ብለው ራሳቸውን የሚያታልሉና የማእዘኑን ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስን የናቁ ናቸው። ከላይ የዘረዘርናቸው ሰዎች በአንድም በሌላም ነገር በወንጌል ለማመንና የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመቀበል ይከብዳቸዋል።

የምሥራቹ የተሰበከላቸው፣ ነገር ግን በተሳሳተ ግምት ከወንጌል ፈቀቅ ያሉ ሰዎች ፍርዳቸው ከባድ ነው። ጌታም ወንጌልን አምቢ አንቀበልም በሚሉ ሰዎች ላይ የሚያመጣው ፍርድ ከሰዶምና ከገሞራ ፍርድ እንደሚከብድ ሲያስተምር፦ «ከማይቀበላችሁም፣ ቃላችሁንም ከማይሰሙ ሁሉ፣ ከዚያ ቤት ወይም ከዚያች ከተማ ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ፡፡ እውነት እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ አገር ይቀልላቸዋል» ብሏል፤ ማቴ. 10፥14-15። ሰዶምና ገሞራ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ሰዎች የነበሩባቸው፣ በኋላ ግን በእግዚአብሔር የፍርድ እሳት ተበልተው የጠፉ ሀገሮች ናቸው። ዛሬም ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙና ክርስቶስን የናቁ ሰዎች መጨረሻቸው እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ ይሆናል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ለወንጌል የማይታዘዙ ሰዎች መጨረሻቸው እስከፊ እንደሚሆን ሲያስብ በአንክሮ እንዲህ ብሏል፤ «ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀምርበት ጊዜ ድርሷልና። አስቀድሞ በእኛ የሚጀምር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?»፤ 1ጴጥ. 4፥17።

## 2. ወንጌልን ተቀብለው፤ እንደ ወንጌል ያልኖሩ

«ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፤ ብዙ ዐደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል»፤ ሉቃ. 12፥48።

በወንጌል ያገኘነው እጅግ ብዙ ነው። ሌላውን ትተን ዋና ዋናዎቹን ብናስተውል የኀጢአት ስርየትን አግኝተናል፤ የእግዚአብሔርን ልጅነት አግኝተናል፤ ከሰይጣን የባርነት አገዛዝ ነጻ ወጥተናል። እኛ ባዶ ሆነን መጥተን በእግዚአብሔር ተሞልተናል፤ የጸደቅነው በእግዚአብሔር ጽድቅ ነው እንጂ፣ እኛ በሳደርግነው ጽድቅ አይደለም። ብቻ እግዚአብሔር እንዲሁ ወዶናል፤ ሞት የሚገባን ስንሆን ሕይወትን አግኝተናል፤ እንግዲህ ክርስቶስን በጽድቅ፣ በቅድስና፣ በእውነትና በታማኝነት እንድንከተለው ተጠርተናል። እኛ በክርስቶስ ከፍርድ ነጻ የወጣን ልጆች ነን፤ ነገር ግን ነጻነታችን ለሥጋ ምክንያትን እንዳይሰጥ የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል።

«ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ ለዐርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ ዐርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፤ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ»፤ ገላ. 5፥13። እግዚአብሔር ነጻ ያደረገን ከተያዝንበት የኀጢአት ፍርድ ነው፤ ነገር ግን ከዚህ ነጻነት በኋላ ኀጢአትን እንደ ፈለግነው ለመሥራት ነጻ አይደለንም። «በክርስቶስ ነጻ ሆኛለሁ





ኀጢአትም ብሠራ አይፈረድብኝም» የሚል አስተሳሰብ ያለው ክርስቲያን ካለ ተሳስቷል። እንዲያውም የእግዚአብሔር የፍቅሩ ዕዳ ያለብን ልጆቹ ነን። በእርሱ መንፈስ እየተመራን ፈቃዱን እንድንፈጽም እንጂ የሥጋን ሥራ እየሠራን እንዳናስመርረው እንጠንቀቅ፤ «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ፣ በሕይወት ትኖራላችሁ» ይላል፤ ሮሜ 8፥12-13።

የሥጋ ፈቃድ ለሰይጣን በር የሚከፍት የመንፈሳዊ ጉዞ ጠንቅ ነው፤ ከሰይጣን ፈተና ይልቅ የሥጋ ፈቃድ ይከፋል፤ የሥጋ ፈቃድ መሞት ያለበት ጠላት ነው። እርሱም በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በተለያዩ የሥጋ ጭቆናዎች የሚሞት አይደለም፤ የሥጋን ፈቃድ በሥጋዊ ሥራ መግደል አይቻልም። ሥጋን መጨቆንም ለመንፈሳዊ ነጻነት አያበቃም። «በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ» ይላልና የሥጋ ፈቃድ የሚሞተው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው።

በወንጌል የሚኖሩ እውነተኛ ክርስቲያኖችንና እውነተኛ ያልሆኑ በወንጌል የሚነግዱ ክርስቲያኖችን የምናውቃቸው በፍሬያቸው ነው። አንድ ተክል «መራራ ነው ጣፋጭ ነው» ለማለት የምንችለው ቅጠሉን አይተን ሳይሆን ፍሬውን ቀምሰን ነው። እንዲሁም እንደ ወንጌል ትምህርት የሚኖሩትን እና የማይኖሩትን ክርስቲያኖች የምናውቃቸው በፍሬያቸው ነው። በሚያስተምሩት ትክክለኛ ትምህርት፣ በሚናገሩት ለስላሳ ቃል፣ በሚያደርጉላቸው ታምራት፣ ወይም በዚህ ዓለም ባገኙት ስኬት እውነተኛ ናቸው ለማለት አንችልም። ጌታ «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» ብሏል። ስለዚህ እኛ ወንጌልን የተቀበልን ሰዎች የምንለካው በፍሬያችን እንጂ በደራረጋችን አይደለምና እንጠንቀቅ። «ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል» ይላል፤ ዮሐ. 15፥2። የእውነተኞች ክርስቲያኖችን ፍሬዎችና የሐሰተኞች ክርስቲያኖችን ፍሬዎች በገላትያ ምዕ. 5፥18-22 ላይ ይመልከቱ።

በወንጌል ቃል መሠረት የማይኖሩ ሰዎች መክሊቱን በቀበረ ሰው፤ ማቴ. 25፥24-30፤ በሰንጼ መሀል በተዘራ እንክርዳድ፣ ማቴ. 13፥37-43፤ ፍሬ በማያፈራ ቅርንጫፍ፣ ዮሐ.15፥2፤ ዕዳውን ይቅር ባለማለት ወንድሙን ወኀኒ ቤት ባሳሰረ ሰው፣ ማቴ.18፥36፤ ቤቱን በአሸዋ ላይ በሠራ ሰነፍ ሰው፣ ማቴ. 7፥26፤ በዐምስት ሰነፍ ቆነጃጅት፣

ማቴ.25፥2፤ በፍየሎችና ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ባለማወቅ እንቅልፍ በተኛ ሰው፣ ሉቃ. 12፥39... ወዘተ ተመስለዋል።

ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መገለጣችን አይቀርም፤ ሥራችንም ለፍርድ ይቀርባል። «መልካም ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል» ይላል፤ 2ቆሮ. 5፥10።

## 3. ወንጌልን ተቀበለው እንደ ወንጌል ቃል የኖሩ

«እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ»፤ ማቴ. 25፥34።ይህ ቃል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለኖሩ ክርስቲያኖች የሚሰጠው የበረከት ቃል ነው። ይህን የፍርድ ቃል የሚሰሙት በክርስቶስ መንግሥት ተልእኳቸውን የፈጸሙት ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በሚገለጥበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ከእርሱ ጋር በክብር ይገለጣሉ፤ «ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ» ይላል ቅዱስ ጳውሎስ፤ ቈላ. 3፥3።

በዚህ ዓለም ክርስቶስን መከተል ሥቃይና መከራ ነው፤ የዓለም፣ የጎረቤት፣ የዘመድ፣ የቤተ ሰብእ ጥላቻ ከባድ ነው፤ ክርስቶስን በእውነት ስንከተለው ሁሉም ያገለናል፤ ወዳጆቻችን የነበሩ ሁሉ ይጠሉናል፤ እንዲህ የሚያደርጉብንም ስለ በደልናቸው ሳይሆን ከጨለማው ገዢ ነጻ ስለ ወጣንና ወደ ልጁ መንግሥት ስለ ፈለስን ነው፤ «እርሱ ከጨለማው ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም እርሱም የኀጢአትን ስርየት ወደ አገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን»፤ ቈላ. 1፥13-14። ክርስቶስንም በታሪክ ሳይሆን በእውነት ስለ ተከተልነው ነው ወዳጆቻችን የጠሉን። ስለዚህ እንደ ክፉ አድራጊ ያሳድዱናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ እንደሚሆንብን አስቀድሞ ባይነግረን ኖሮ እምነታችንን ትተን ወደ ኋላ ባፈገፈግን ነበር። «ዓለም የራሱ የሆነውን ይወዳል ነገር ግን እናንተ ከዓለም ስላይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል፤ ዓለም ቢጠላችሁ አስቀድሞ እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ... እኔን እሳደዱኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል» ብሎናል፤ ዮሐ. 15፥18-20። ስለዚህ ክርስቶስን ያልወደደ ዓለም እኛንም እንደማይወደን ስለ ተረዳን፣ በመከራችን ደስ ይለናል፤ ተስፋችን በሰማይ ነውና፣ አሁን በሚሆነው ወደ ኋላ አንመለስም። ቅዱስ ጳውሎስም፤ «ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም» (ፊል. 1፥29) ይላል። አባቶቻችን ሐዋርያትም ክርስቶስ የነገራቸው ቃል በሕይወታቸው በመፈጸሙ





ከመከራውም በመካፈላቸው ደስ ብሏቸዋል፤ የሐዋ. 5፥41። አዎ ሥቃዩ ከባድ ቢሆንም የሚመጣውን ክብር በማሰብ በእምነታችን እንበረታለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ መከራ የጸናባቸውን የሮም ክርስቲያኖች «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች ክብር መገለጥ ይጠባበቃልና» (ሮሜ 8፥18-19) በማለት አጽናንቷቸዋል። ስለዚህ እኛም የተቀበልነው ወንጌል የመከራ ብቻ ሳይሆን የክብርም ስለ ሆነ፣ ጸንተን በመልካም ሥራ እየተጋደልን መኖር ይገባናል። ከዚህ ወንጌል ፈቀቅ የምንልና ከዓለም ያልተሻለ ሕይወት ካለን ግን ውርደት እንጂ ክብር አይጠብቀንም።

አንድ ሰው በተማረበት ሙያ ድግሪውን ወይም ዶክትሬቱን ሊቀበል ይችላል፤ ተቋሙ የሚሰጠው ወረቀት «በዚህ መስክ ሠልጥኗል»፤ «ሊሠራ ይችላል» የሚለውን ምስክርነት ለመስጠት ነው። ባለሙያው በሠለጠነበት መስክ ቢሠራ አንደኛ፣ ብቃትና ጥራት ያለው ሥራ ይሠራል፤ ሁለተኛ፣ ሰውየው በቂ ደሞዝ ስለሚያገኝ ኑሮው መልካም ይሆናል፤ በሥራውም ለትውልድና ለሀገር ጥሩ መሠረት ያስቀምጣል። እንደዚህ ዐይነት ሰው በመንግሥትና በሕዝብ ዘንድ የተከበረ ነው። ነገር ግን ዕውቀቱንና የተቋም ምስክርነትን አግኝቶ ምንም ባይሠራበት ጉራና ወሬ ብቻ እንጂ፣ ምንም ጥቅም አያገኝም፤ ለራሱም ሆነ ለሀገሩ የሚያበረክተው ሥራ አይኖርም፤ እርሱም አይጠቀምም፤ ለሀገርም ለቤተ ሰብም ሸክም ይሆናል።

ወንጌልም ልንኖርበት የተሰጠን ሕይወት ነው፤ ለእግዚአብሔር ክብር ለወንድም መልካም ሥራ ልንሠራ የተሰጠን ጸጋ ነው። «መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌ. 2፥10) ተብሎ እንደ ተጻፈ ፣ ወንጌልን የተቀበልነው ለመሥራት ነው። ወንጌል ለሰዎች እንዲሁ የተሰጠ የምሥራች ነው። እኛ ይህን የምሥራች ለማግኘት የከፈልነው ዋጋ የለም። ነገር ግን ታላቅ ዋጋ ተከፍሎበት ነው እኛ ዘንድ የደረሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ከፍሎበታል፤ ክብሩን ትቶ ወደ ምድር በመምጣት ተዋርዶበታል፤ ተሰዶ፣ ተገፍቶ፣ ተመትቶ ደሙን እስከ ማፍሰስ ዋጋ ከፍሎበታል፤ ስለዚህ ወንጌል እንዲሁ ቢሰጥም የከበረና ውድ ነገር ነው።

ጌታችን «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ» አለ። ጨው ሁለት ዐይነት አገልግሎት ይሰጣል፤ አንደኛ፣ ምግብን ያጣፍጣል፤ ሁለተኛ፣ ምግብ እንዳይበላሽ ያደርጋል። እኛም በክርስቶስ ያመንን ሰዎች የምድር ጨው ነን፤

ሕይወት የመረረውን ኑሮ የከበደውን ሰው፤ እውነተኛውን ጣፋጭ የክርስቶስ ሕይወት እናካፍለዋለን፤ እኛ ያገኘነውን እናካፍለዋለን፤ የተቀበልነውን እንሰጠዋለን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበልነውን እንድንሰጥ ነው የላከን። ጨው ምግብ እንዳይበላሽ ያደርጋል፤ እኛም በሥነ ምግባራችን ትውልድና ማኅበራዊ ሕይወት እንዳይበላሽ ተግተን መሥራት አለብን፡፡ ወንጀል፣ ሌብነት፣ የፍትሕ ዕጦት፣ ሙስና እንዳይስፋፋ እኛ በታማኝነት መሥራት አለብን። ጨውነታችን አሁን ላለንበት ምድርና ዐብረነው ለምንኖረው ሕዝብ ነው። እንደዚህ ባናደርግ ወንጌልን መስበክ አንችልም፤ ወንጌልን የምንሰብከው እኛ ያገኘነውን ሕይወት ሌሎች እንዲያገኙ፣ እኛ በተጠቀምንበት ጥቅም ሌሎችም እንዲጠቀሙ እንጂ፣ ሃይማኖታችንን ለማስፋፋት አይደለም። እኛ ወንጌልን የተቀበልን ሰዎች ያገኘነው የሕይወት ለውጥ ከሌለ ሌሎችን ምን ብለን ልንሰብክ እንችላለን? ወንጌልን ያልተቀበሉ ሰዎች «እናንተ ምን አገኛችሁ?» ቢሉን ምን አገኘን እንላለን? ስለዚህ ወንጌል የእውነተኛ ሕይወት መኖሪያ እንጂ፤ ዝም ብሎ የሚወራ ዜና አይደለም።

ጌታችን፣ «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሎናል። ብርሃን የተሰወረውን ይገልጣል፤ የማይታየውን ያሳያል። በዚህ ዓለም ውስጥ ሕይወት የተሰወረባቸው፤ በጨለማ አገዛዝ ሥር የወደቁ ተስፋ የሌላቸው ሰዎች ሞልተዋል። ለእነዚህ ሰዎች የማይታየውን በእምነት እንዲያዩ፣ ተስፋ መንግሥተ ሰማያት እንዲኖራቸው፤ የተሰወረውን እውነተኛ ሕይወት በክርስቶስ እንዲያገኙ ብርሃን ልንሆናቸው ይገባል። ብርሃን የምንሆነው ግን እኛ በቅድሚያ ከጨለማ እስተሳሰብ ስንወጣ ነው። «እናንተ ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ» እንደ ተባለ (ኤፌ. 5፥8) በዚህ ዓለም በጨለማው ገዢ ላይ ወንጌልን በማብሠር ሥራውን እናፈርስበታለን፤ በጽድቅና በቅድስና ኖረን የክፋትንና የርኵሰትን ኀይል እንቃወማለን፤ በሰላም ወንጌል ለዓለም ጸጥታንና ዕረፍትን እንሰብካለን። በዚህም ሁሉ ላይ ለከፉዎችና ለዐማፅኞች እየጸለይን፣ ለተቸገሩና ለወደቁ መልካም እያደረግን የክርስቶስን ዐላማ በምድር ላይ ለመፈጸም እንጋደላለን። በዚህ ሁኔታ መንፈሳዊ ሩጫችንን ከጨረስን የሚጠብቀን የክብር አክሊል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም» ብሏል፤ 2ጢሞ. 4፥8፡፡ ጌታም፣ «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፤ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ» የሚል ቃል ኪዳንን ሰጥቷል፤ ራእ. 2፥10።





## 3.13. ማጠቃለያ

«ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው» ፤ ሰቆ. 3፥26፡፡ ለሰው ያልተቻለው ሁሉ በእግዚአብሔር ተችሏል፤ የክርስቶስ ጽድቅ ለኀጢአተኛው ዓለም የሚበቃ ሥራ ነው። «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» (ሮሜ 7፥24) ለሚል ኀጢአተኛ እግዚአብሔር መልስ አለው፤ እርሱም «ለሰው የተሠራ ዘለዓለማዊ ጽድቅ በክርስቶስ አለ» የሚለው ነው። እግዚአብሔር ለጽድቅ የሚያበቃውን አስፈላጊውን ሁሉ ሥራ በመስቀሉ በመፈጸም ምስጋናውን ጠቅልሎ ለራሱ አድርጓል። በዘመን ፍጻሜ ሊያደርግ ያለው ሐሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለመጠቅለል ነው፤ (ኤፌ.1፥10)፡፡ ይህን የሚያከናውንበትን ሥራም በመስቀሉ ላይ ሠርቶ ሁሉም በክርስቶስ እንዲጠቀለል እየጠበቀ ነው።

እንግዲህ የራሳችንን ጽድቅ ለማቆም በፀሓይ የሚደርቅ ቅጠል ማገልደማችንን ትተን ጠንካራውንና የማይቀደደውን የእግዚአብሔርን የጸጋ ቁርበት እንልበስ፤ እርሱ ራቁትነታችንን የሚሸፍንና ኀፍረታችንን የሚከድን ነው። እኛ ከምናቆመው ጽድቅ ይልቅ እግዚአብሔር ያቆመው ጽድቅ የላቀ ነውና ወደ እርሱ እንጠጋ።

«እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር፡፡ እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆናል፤ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም፡፡ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና»፤ ገላ.3፥23-26፡፡

«አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ ይህም ***የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤*** ኀጢአት በሕግ ይታወቃልና፡፡

አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፣ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ ***በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ***

***ነው*** ፤ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ ***በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው*** ***<u>በጸጋው</u>*** ***ይጸድቃሉ፡፡» ፤*** ሮሜ3፥19-24፡፡

# ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ

ተፈጸመ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!
በተከሥተ ሜኔ አልማው





<u>ምንጭ</u>


1ኛ. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1953) <u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

2ኛ. <u>ሃይማኖተ አበው</u> (1986) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

3ኛ. <u>የቤተ ክርስቲያን ጸሎት</u>፡፡ (1936) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

4ኛ. <u>ግብረ ሕማማት፡፡</u> አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

5ኛ. አባ አበራ በቀለ /ሊቀ ጉባኤ/ (1996) <u>ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት</u> ፤አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

6ኛ. የተለያዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስተማሯቸው ያልታተሙ ማስተማሪያ ጽሑፎች

ሕግ፣ጸጋና ጽድቅ የክርስትና መሠረተ ሐሳብ የሚተነተንባቸውና የሚጸናባቸው ዐበይት የቅዱስ መጽሐፍ ቃላት ናቸው፡፡ የእነዚህን ቃላት የተናጠል ምንነትና የእርስ በርስ ተያያዥነት በተገቢው መንገድ መረዳት የሚቻለው፣ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹበት ትክክለኛ ይዘት በጥንቃቄ እየተገናዘበ ሲነበቡ ነው፡፡ ደራሲው ይህን ታላቅ መንፈሳዊ ጥቅም በማየት ይመስለኛል ቃላቱ ሳይነጣጠሉ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እየተጣጣሙ በዚህ መሠረት እንዲቀርቡ ያደረገው፡፡ ከተመረጠው የአቀራረብ ባሕርይ የተነሣ፣ በእነዚህ ቃላት ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጅ ያከናወነው የፍጹም ፍቅር ተግባር በግልጽ ይታያል፡፡ ከዚህ በፊት እነዚህን ቁልፍ ቃላት በተናጥል ካልሆነ በቀር፣ እንደዚህ በአንድነት ተቀራርበውና ከሚገኙበት የቃለ እግዚአብሔር ክፍል ጋር በሚገባ ተገናዝበው እምብዛም አልታየም፡፡ ይህ አቀራረብ ግን አንባቢን ስለሚረዳና በዚህ ረገድ የተሟላ ግንዛቤን ስለሚያስጨብጥ መጽሐፉን ሁሉም የራሱ ቢያደርገውና ቢያነበው ምኞቴ ነው፡፡

መሪጌታ ልሳኑ ጥዑም

ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 18 በአንድነት የተጠቀሱ ቃላት ናቸው፡፡ ሕግ ከሙሴ፣ ጸጋና ጽድቅ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተዛምደው ተጠቅሰዋል፤ ጸጋና ጽድቅ የክርስቶስ ገንዘቦች ናቸው፤ ይህን ስንል ሕግ የክርስቶስ አይደለም ማለታችን ሳይሆን ሕግ ጸጋና ጽድቅን ሊሰጠን አልቻለም፤ በክርስቶስ ግን ሁለቱን አገኘን ለማለት ነው፡፡ መምህር ተከሥተ ሜኔ «ሕግ፣ጸጋና ጽድቅ» በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ይህ መጽሐፍ ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀታችንን የሚያዳብር፣ ሕይወታችንን የሚያጸና ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ እግዚአብሔር ይባርክህ

መምህር ላዕከ ኢየሱስ

ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ የተሰኙት ቃላት የሚያስተላልፉት መንፈሳዊ መልእክት ሰፊና ጥልቅ ከመሆኑም በላይ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚሻ ሁሉ የእነዚህን ቃላት መንፈሳዊ መልእክት በሚገባ መረዳት ያስፈልገዋል! የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የእነዚህን ቃላት ምስጢር በማብራራት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አዘጋጅቶ አቅርቦልናል፡፡ ጽሑፉ ለሁላችን አስፈላጊ ትምህርት ስለያዘ ሁሉም እንዲያነቡት እጋብዛለሁ፡፡

ከመምህራን አንዱ

ዋጋ 20.00 ብር
U.S.D 10 $

እለኔ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ.

ሕግ፣ጸጋና ጽድቅ የክርስትና መሠረተ ሐሳብ የሚተነተንባቸውና የሚጸናባቸው ዐበይት የቅዱስ መጽሐፍ ቃላት ናቸው፡፡ የእነዚህን ቃላት የተናጠል ምንነትና የእርስ በርስ ተያያዥነት በተገቢው መንገድ መረዳት የሚቻለው፣ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹበት ትክክለኛ ይዘት በጥንቃቄ እየተገናዘበ ሲነበቡ ነው፡፡ ደራሲው ይህን ታላቅ መንፈሳዊ ጥቅም በማየት ይመስለኛል ቃላቱ ሳይነጣጠሉ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እየተጣጣሙ በዚህ መሠረት እንዲቀርቡ ያደረገው፡፡ ከተመረጠው የአቀራረብ ባሕርይ የተነሣ፣ በእነዚህ ቃላት ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጅ ያከናወነው የፍጹም ፍቅር ተግባር በግልጽ ይታያል፡፡ ከዚህ በፊት እነዚህን ቁልፍ ቃላት በተናጥል ካልሆነ በቀር፣ እንደዚህ በአንድነት ተቀራኝተውና ከሚገኙበት የቃለ እግዚአብሔር ክፍል ጋር በሚገባ ተገናዝበው እምብዛም አልታየም፡፡ ይህ አቀራረብ ግን አንባቢን ስለሚረዳና በዚህ ረገድ የተሟላ ግንዛቤን ስለሚያስጨብጥ መጽሐፉን ሁሉም የራሱ ቢያደርገውና ቢያነበው ምኞቴ ነው፡፡

መሪጌታ ልሳኑ ጥዑም

ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 18 በአንድነት የተጠቀሱ ቃላት ናቸው፡፡ ሕግ ከሙሴ፣ ጸጋና ጽድቅ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተዛምደው ተጠቅሰዋል፤ ጸጋና ጽድቅ የክርስቶስ ገንዘቦች ናቸው፤ ይህን ስንል ሕግ የክርስቶስ አይደለም ማለታችን ሳይሆን ሕግ ጸጋና ጽድቅን ሊሰጠን አልቻለም፤ በክርስቶስ ግን ሁለቱን አገኘን ለማለት ነው፡፡ መምህር ተከሥተ ሜኔ «ሕግ፣ጸጋና ጽድቅ» በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ይህ መጽሐፍ ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀታችንን የሚያዳብር፣ ሕይወታችንን የሚያጸና ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ እግዚአብሔር ይባርክህ

መምህር ላዕከ ኢየሱስ

ሕግ፣ ጸጋና ጽድቅ የተሰኙት ቃላት የሚያስተላልፉት መንፈሳዊ መልእክት ሰፊና ጥልቅ ከመሆኑም በላይ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚሻ ሁሉ የእነዚህን ቃላት መንፈሳዊ መልእክት በሚገባ መረዳት ያስፈልገዋል! የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የእነዚህን ቃላት ምስጢር በማብራራት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አዘጋጅቶ አቅርቦልናል፡፡ ጽሑፉ ለሁላችን አስፈላጊ ትምህርት ስለያዘ ሁሉም እንዲያነቡት እጋብዛለሁ፡፡

ከመምህራን አንዱ

ዋጋ 20.00 ብር
U.S.D 10 $

እሰኔ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ.